ሥነ- ስብከት

ሊድስታር ቲዮሎጂካል ኮሌጅ

የዲግሪ መርሀ ግብር መማሪያ ሞጁል

የተለወጡና የበቁ መሪዎችንና
ሚሲዮናዊያንን ለኢትዮጵያ
ቤተክርስቲያንና ለምድራችን
ማብቃት ራዕያችን ነው።

የትምህርቱ መግለጫ

ይህ ትምህርት በዋንኛነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ስነ መለኮታዊ መሰረት ስለያዘ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት እና ስለ መሰረታዊ ገላጭ ስብከት ክህሎት ማለትም ከዝግጅት እስከ መልዕክት ማቅረብ ድረስ ያለውን ሂደት ይዳስሳል። በተወሰነም ደረጃ የተለያዩ የስብከት አይነቶችን በማንሳት ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ከትንታኒያዊ ስብከት አንፃር ይቃኛል። እንዲህም ስለሰባኪ ባሕርያት እና ሐላፊነት የተወሰኑ ሀሳቦችን እንመለከታለን።

የትምህርቱ ዓላማ፡-

የኮርሱ አላማ፡ *ተማሪዎች በአገልግሎታቸው (በስብከታቸው) ወቅት ውጤታማ እንዲሆኑ ሊወስዱ የሚገባቸውን የቅድመ-ስብከት፣ የስብከት ጊዜና የድህረ-ስብከት ሁኔታን እንዲረዱ ለማድረግና በሚያገለግሉበት አጥቢያም ለሚሰብኩ አገልጋዮች ምሳሌ እንዲሆኑ ብሎም በስብከት ዙሪያ የምክክር መድረክ መፍጠር እንዲችሉ ለማበረታታት ነው።*

ይህን ትምህርት ስናጠናቅቅ የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች መረዳት እንችላለን፡-

- መሰረታዊ የትንታኔያዊ ስብከትን መመሪያ መገንዘብ
- ስለ ስብከት አይነቶች እና አወቃቀራቸው ግንዛቤ መጨበጥ
- ትንታኔያዊ ስብከትን በምናዋቅርበት ግዜ ልንከተላቸው የሚገቡንን መሰረታዊ ደረጃዎችን በመረዳት በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ እንድንተገብራቸው ማስቻል
- ተማሪዎችን ለመፅሐፍ ቅዱሳዊ; በመንፈስ ለተሞላ እና በአውዱ መሰረት ወቅታዊ ስብከት የመስበክን ፍላጎት ማነሳሳት
- የአንድን መልዕክት ትክክለኝነት; ግልፅነት እና ወቅታዊ (አግባባዊነት) በክፍል እና ከክፍል ውጪ መመዘን እና ለስህተቶች ቅንነት ያለው ማስተካከያ ማድረግ
- ተማሪው የተማረውን መፅሕፍ ቅዱሳዊ ስነስብከት በግል ሕይወት እና በአገልግሎት እንዲተረጉም ማበረታታት

የትምህርቱ ማውጫ

የትምህርቱ መግለጫ 0
መግቢያ 4
ምዕራፍ አንድ፡ ስነ-ስብከት ምን ማለት ነው? አላማውስ ምንድን ነው? 5
1.1 የስብከት ሥነ-መለኮታዊ መሠረት 8
1.2 የስብከት ታሪካዊ ቅኝት 9
1.3 የቃላት ብያኔ 13
1.4 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ስብከቶች ዳሰሳ 14
በብሉይ ኪዳን ስብከት ምን ይዘት ነበረው? 15
በአዲስ ኪዳን ስብከት ምን ይዘት ነበረው? 15
ምዕራፍ ሁለት፡ የስብከት አይነቶች 16
2.1 ገላጭ ስብከት (Expository Sermons) 17
ትርጉሙ 17
ጥቅሙ 18
ገላጭ ስብከት ስናዘጋጅ ልናየው የሚገባ ጉዳይ 19
የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ደረጃዎች 19
2.1 አንድ ክፍል ላይ የተመሰረተ ስብከት (Textual Sermons) 33
ትርጉሙ 35
ጥቅሙ 35
ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች 35
2.3 ርዕሳዊ ስብከት (Topical Sermons) 36
ትርጉሙ 37
ጥቅሙ 37
ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች 37
2.4 ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት (Biographical Sermon) 37
ትርጉሙ 38
ጥቅሙ 38
ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች 38
2.5 ምሳሌያዊ ስብከት (Allegorical Sermon) 39
ትርጉሙ 39
ጥቅሙ 40
ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች 40
ምዕራፍ ሦስት፡ የተሳካለትና ውጤታማ ሰባኪ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቁልፍ ነገሮች ምን ምን ናቸው? 40
3.1 የሰባኪ ሕይወት 41
3.2 የሰባኪ መልዕክት 41
3.2.1 ስብከትን እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል? 41
3.3 የመልዕክቱ ባለቤት (መንፈስ ቅዱስ) 42
መልዕክትን ማዘጋጃ መንገዶች 46
3.4 ንባበ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ማድረግ 46
3.5 የስነ-አፈታት ሕጎችን ተግባራዊ ማድረግ 46

3.6 መልዕክትን በሚገባ ለአድማጭ (ለአንባቢ) ለማድረስ የሚረዱ መርሆች 47
3.7 የቃላት አነባበብ (Pronunciation) 47
3.8 ግልጽነት (Articulation) 47
3.9 የሰዋሰው ዕግን ማክበር (Grammar) 48
3.10 ድምጸት- ድምጽ አወጣጥ (The Voice) 48
3.11 የአይን እንቅስቃሴ (Eye Contact) 48
3.12 የሰውነት እንቅስቃሴ (Gestures) 49
3.13 አሳምሮ መግለጽ (Dramatizations) 50
3.14 በምልከታ መሳሪያዎች መጠቀም (Visual Aid) 50
ማጠቃለያ 51
ምዕራፍ 4፡ የሰባኪው ህይወት 51
4.1 ሰባኪ / የእግዚአብሔር ሠው/ 52
4.2 የሰባኪነት ጥሪ 53
4.3 ክርስቲያን ሰባኪ 54
4.4 የስብከት ተግባር 55
4.5 የወንጌል ሰባኪያን አላማ 56
4.6 የሰባኪ ባህርይ 56
4.6 የማስተምር ፀጋ እና የእረኝነተ አገልግሎት ተጓዳኝነት 61
4.7 የማስተማርና የመማር መርሆዎች/ሕጎች/ 62
4.7.1 የአስተማሪው ሕግ 62
4.7.2 የተማሪው ሕግ 62
4.7.3 የቋንቋ ሕግ 64
4.7.4 የትምህርት ሕግ 65
ምዕራፍ አምስት፡ መልክቱን ማዋቀር 78
መልዕክት የማቅረቢያ መንግዶች /ዘዴዎች/ 90
መንፈሳዊ መመሪያ 91
በስብከት ሂደት ውሰጥ የማይነጣጠሉ ሦስት ነገሮች 92
ማጠቃለያ 93
Bibliography 95

መግቢያ

የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ለሰው ልጅ ከተሠጡት ኃላፊነቶችና መልካም ዕድሎች ዋንኛው ነው፡፡ «አለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል፡፡» 1ኛ ቆሮ 1፡21 እግዚአብሔር ስብከትን ለሰው ልጆች እንጂ ለመላእክት አልሰጣቸውም፡፡ የስብከት አገልግሎት በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት ከትርጓሜው በመሆኑ መስበክ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ጥሩ አድርጎ ማስተላለፍ የሚያስችል ችሎታ ያለንበትን ማህበረሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ፣ ለመገሰጽ እና ለማበረታታት የሚደረግ ጥረት ነው፡፡

ሰባኪነት የሰዎችን ለጊዜያዊ ችግራቸው የሚሆን መፍትሄ ብቻ ሣይሆን የእግዚአብሔር መልእክት በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ማቅረብ ሲሆን ሰባኪው ይህን እውነት በመረዳት አገልግሎቱን ፍሬያማ ማድረግ አለበት፡፡ ሰባኪነት በአንድ ቦታ የማይወሰን ለሚጠፉ ሰዎች የሚገደውና ደህንነትን መልእክት የሚያቀርብ ሰዎችን በስልጣናዊ ቃል በእግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጡ የማድረግ ችሎታ በመሆኑ ሰባኪ ስልጣኑን መጠቀም አለበት ሰባኪነት መሠረታዊ ነገሮች ፀሎት ዝግጅትና ጥንቃቄ የሚያስፈለጉ ሲሆን የዚህን የ21ኛውን ክፍለ ዘመን ሰው በማገልገል የሚገባውን የእግዚአብሔር ቃል በመሞላትና የጊዜው ሁኔታ በማጤን መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ ሰባኪነት በጥሪ የሚገኝ ሲሆን ይህንንም ጥሪ ያለሰባኪ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በቃልሙላትና በፀሎት በብዙ ዝግጅት ማገልገል የሚገባ አገልግሎት ነው፡፡

ጳውሎስ በሮሜ 10፡14-15 ላይ እንዲህ ይላል፡- “እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? ይህ ማለት ደግሞ ሰዎች በክርስቶስ አምነው እንዲድኑ ሰባኪዎች እንደሚያስፈልጋቸው ሰባኪዎች ደግሞ በጌታ መጠራት እና የምስራች ተኮር ስብከት ሊሰብኩ እንደሚገባቸው ይነግረናል። ለዚህም አይደል ጳውሎስ ለጢሞቴዎስም ቃሉን ስበክ ብሎ የሚያዘው! ዳሩ ግን ሰባኪ ምን ማለት ነው? ስብከትስ እንዴት ያለ ነው? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በዘመናችን ሊነሱ ግድ ይላል። ምክንያቱም የአንዳንድ ሰባኪዎችን ስብከት ለመስማትና ለመረዳት ሰዎች ሲቸገሩ ይታያል፣ አንዳንዶች ሁለትና ሶስት ሰዓት ሰብከው ምነው ባላለቀ ሲባልላቸው አንዳንዶች ደግሞ 20ደቂቃ ሰብከው ሰሚዎቻቸው ከመሰላቸታቸው የተነሳ ዕንቅልፍ አለም ውስጥ ሲነጉዱ ይታያሉ። ለምሳሌ፡ ጆናታን

ኤድዋርድ የተባለው ታዋቂ ሰባኪ 1758 ዓ.ም ላይ በተደጋጋሚ ለሁለት ሰዓታትና ከዛም በላይ ይሰብክ እንደነበርና ታዳሚዎቹ ከምኔው አለቀ ይሉ እንደነበር ይነገራል። ስለቄስ ሙሬ አሰባበክ እና የስብከት ጣፋጭነት አንድ ጸሐፊ ሲናገር፡- “በአንድ እሁድ ላይ ሙሬ ሲሰብክ ሶስት ተከታታይነት ያላቸውን መልዕክቶቹን በሚያቀርብበት ወቅት አንድ ሰው እንኳን ሳይወጣ መልዕክቱን ሲከታተሉ እንደነበርና ከሶስተኛው መልዕክቱ በኋላ ቄሱ መቆም ስላቃተው ታዳሚውን ይቅርታ ጠይቆ ስብከቱን እንዳቆመ” ተናግሮ ነበር። በዚህ ላይ አንድ ወዳጄ ስለስብከቱ ሌላ ወዳጁን ሲጠይቀው ያለውን ነገር ሲያጫውተኝ ያለኝ ላጋራችሁ፡- ስብከቱን እንዴት አገኘከው ቢለው ተጠያቂው ሰው እንዴት መስበክ እንደሌለብኝ ያየሁበት ስብከት ነው ብሎ ነበር። ስለዚህ ስብከታችንን ከማቅረባችን በፊት ልናውቃቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮች አሉ ማለት ነው። የተሳካላቸው ሰባኪዎች እንዴት ሰበኩ? እንዴት የአድማጮቻቸውን ልቦና ለረዥም ጊዜ ሊቆጣጠሩ ቻሉ? እነዚህንና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ይህ ስነ-አሰባበክ የሚባለው ኮርስ መልስ ያሳየናል። በዚህ ትምህርት ስለ ስነ-ስብከት ትርጉም፣ በታሪክ ውስጥ ስብከት ምን ይመስል ነበር፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያሉ ስብከቶች እንዴት ይታያሉ፣ የስብከት አይነቶችን፣ እንዴት የተዋጣለት ሰባኪ መሆን እንደሚቻል፣ የሰባኪ መልዕክት ዝግጅት እና ስብከትን ለአድማጭ ለማድረስ የሚረዱ ነገሮችን በዚህ ትምህርት እንመለከታለን።

ምዕራፍ አንድ፡ ስነ-ስብከት ምን ማለት ነው? አላማውስ ምንድን ነው?

የምዕራፍ አንድ ትምህርት ዋና ዓላማዎች፡

- ስብከት ምን ማለት እንደሆነ ስርወ ቃሉን በማጥናት መረዳት
- በተለምዶ በየምስባኮቻችን የምናያቸው ስብከቶች ሁሉ በስብከት ትርጓሜ መሰረት ትክክለኛነታቸውን መለካት
- ስብከት የሆኑና ያልሆኑትን መለየት
- የስብከትን ታሪካዊ ትንታኔን መረዳት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ነጥቦች

- ስብከት ለተፈለገው ሰዓታት በመድረክ ላይ በንግግር ቆይታ ከማድረግ ያለፈ ነው፡፡
- ስብከት ከልማዳዊ ተግባር ይልቅ ሳይንሳዊ ክንዋኔ ነው፡፡

- ስብከት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ለጊዜው የሆነውን የእግዚአዚአብሔርን ሐሳብ በተገቢው ቦታ በተገቢው መንገድ ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡
- ስብከትን አስፈላጊ የሚያደርጉ አያሌ ምክንያቶች ሲኖሩ አለመስበክን ለድርድር ማብቃት የሚቻልበት ምንም መንገድ ሊኖር አይችልም፡፡

መግቢያ

እንደማንኛውም ፍች የሚያሻው አርዕስት ጉዳዮች ስብከትም ፍች ያለው ክስተት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስሆነም የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ፍች ይሰጡታል፡፡ በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ መንገድ ለመስበክ ይመረጣል የሚባል ገላጭ ስብከት አፈታት መሠረት በሚከተለው ምልኩ ይገለጻል፡፡ ሮብንሰን የተባሉ የሥነ መለኮት አዋቂ ስለ ስብከት በጻፉት መጽሐፋቸው የሚከተለውን ብለዋል፡ "ገላጭ ስብከት በትረካዊ ስዋስዋዊ እና ሰነጽሑፋዊ ዓውዱ የተጠና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክትን በሰባኪው ሕይወት እና ልምምድ መንፈስ ቅዱስ ዕውን ያደረገውን ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

የዚህ ፍች ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉትን እውነቶች ያካትታል፡- ስብከት ማለት በጥሩ የመተርጎም ዘዴ የተደረሰበትን መልዕክት እንጂ እያንዳንዷን ዐረፍተ ነገር መመልከት አለመሆኑን፤ መልዕክቱ በመጀመሪያ በሰባኪው ሕይትና ልምምድ ከታየ በኂላ ለሌሎች የሚተላለፍ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ስብከት ምን እንደሆነ ከማየታችን በፊት ስብከት ምን እንዳልሆነ ማየት ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ስብከት የማመስሉ ነገር ግን ያልሆኑ ብዙ ነገሮች የሚታዩበት ዘመን ነውና፡፡

1. ለመነሻ ያህል አንድ ቃል አንብቦ ያንን ማብራራት ሲገባ ሌላ ሃሣብ ማስተላለፍ አይደለም
(It is not a spring board)

ለምሣሌ ከትንቢተ ሶፎኒያስ ላይ እናነባለን ብሎ አንብቦ በመዝጋት ፈፅሞ ከተነበበው ክፍል ጋር የማይገናኝ ጉዳይ ተናግሮ መጨረስ ማለት ነው፡፡

ዋና የሚዋኙ ሰዎች ተወርውረው ወደ ውሃው ተስፈንጥረው ለመግባት የሚጠቀሙበት ስፕሪንግ ቦርድ እንደሆነ ሁሉ እንዲህ ያለ ሰባኪዎችም መፅሃፍ ቅዱስን ለመንደርደሪያ ብቻ ይጠቀሙበታል፡፡ አንድ ቃል ስለተነበበ ብቻ ስብከት ተሠበከ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በስብከት መጨረሻ የሠዎች ህይወት ካልተለወጠ ቃሉ አልተሠበከም ማለት ነው፡፡

ብዙ ጊዜ በየመድረኮቻችን ስብከት የሚያቀርቡ ሰዎች ስብከታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ሲጀምሩ ይስተዋላሉ፡፡ ነገር ግን በአንተ/ቺ ትዝብት ሊሰብኩት ያነበቡትን ጥቅስ ምን ያህሉ ሰብከውት እንደሚያውቁ በራስህ/ሽ ውጤት በመስጠት ግለጹ፡፡

2. የግል ምሥክርነት መሥጠትም ስብከት አይደለም

የግል ዋምምዳችንን በስብከታችን መካከል ከምንሰብከው ጋር የሚሄድ ከሆነ በጥቂቱ ልንጠቀምበት እንችላለን እንጂ ሙሉውን ምስክርነት ከሆነ ስብከት አይባልም፡፡ አንዳንዴ የአገልግለት ሪፖርት ይሁን ስብከት መለየት እስኪያዳግት ድረስ ይቸግራል፡፡ ተጀምሮ እስኪያልቅ ሥለራሳችን ተናግሮ መወረድ ስብከት ሣይሆን ራሰን ማስተዋወቅያ መንገድ ነው፡፡ ከአገልግሎታችን በኋላ አንተ/አንቺ በጣም ትገርማለህ ወይም ትገርሚያለሽ ካሉን መልዕክት ሣይሆን ራሣችንን አስተዋውቀን ወርደናልና እንጠንቀቅ

ስላገኘናቸው ምድራዊ በረከቶች ስናወራ ምናልባት የሰዎችን ልብ እናነሣሣው ይሆናል ሆኖም ግን ተፈላጊውን የህይወት ለውጥ አያመጣም፡፡

3. የጥቅስ ጋጋታም አይደለም

ለምሣሌ፡- ስለ «ፍርሃት» ነው የምስብከው ብሎ ከብሉይ ኪዳን 5 ጥቅስ ከአዲስ ኪዳን 5 ጥቅስ አንብቦ እነዚህን ደግም ቤታችሁ አንብቧቸው ብሎ ሌሎችን ጨምሮ ማቅረብ ስብከት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነቱ አቀራረብ ከዝግጅት ማነስ የሚመጣ ነው፡፡ ይኼኛው አይነቱ አቀራረብ ብለራሱ የሚሠብከው በጥቂቱ ይሻላል ቢሆንም ግን ቃሉ ተነበበ እንጂ አልተብራራም፡፡ ስለዚህ ስብከት ሣይሆን ኮሜንተሪ ወይም ኮንኮርደንስ አንብባ የቀረበ ንግግር ነው፡፡ ይህ ልክ እንደ Fast Food ነው፡፡ (በበቂ ሁኔታ አልበሠለምና ለጤና ያሠጋል) በቂ ጊዜ ወስዶ በቂ ዝግጅት በማድረግ ስብከትን ማዘጋጀት ከዚህ አይነቱ ስህተት ይጠብቀናል፡፡

4. የመድረክ ላይ ድራማም ብቃት ማሣያ አይደለም

ገና ሰባኪው ቃል ሣይናገር በእንቅስቃሴው ብቻ ከጉባኤው ጭብጨባና እልልታ ይሥተጋባል፡፡ «አጠገብህ ያለውን ሰው እንዲህ በለው እንደያ በለው» የሚሉ ተደጋጋሚ ትዕዛዛት ይንጋጋሉ፡፡ እንደ ሰባኪ ይህንን ስናደርግ ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ማን ከማን ጐን እንዳለ ሣናውቅ ትዕዝዝ ማብዛት ተገቢ አይደለም፡፡ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ከመድረክ ማስተላለፍ ተገቢ አይደለም ይልቅስ በተገቢው ቦታ ተገቢ እንቅስቃሴ ማድረግ እንጂ (እግዚአብሔር ትልቅ ነው ሰንል በእጃችን መግለፅ) እና የመሣሠሉት ማለት ነው፡፡ እንዲህ ይለው ድርጊት በተለይ በአዳዲስ ቤተክርስቲያናት ይታያል፡፡ ስብከት ሰዎችን ማሟሟቅያ ወይም ሰዎችን ለማስደሰት

የምናደርገው ነገር አይደለም በክርስቶስ ፍፁም የሆነን ሰው መሥሪያ መንገድ እንጂ (ቆላስያስ 1፡28)

አሁንም መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ከስብከታችን በኋላ ማነው ከፍ ብሎ የታየው የሚለውን ነው፡፡ እኛ ወይም እግዚአብሔር? በስብከት መድረክ ላይ ስንሆን ሰዎችን ለማዝናናት ሣይሆን የሚለወጡበትን መልዕክት ለማቅረብ መቆማችንን አንዘንጋ፡፡ ብዙ ጊዜ የመፅሃፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ራሣችን በተማርነው መሠረት እንሰብክም ምክንያቱም አያነቃቀም ሰው የሚወደው አይነት አይደለም ብለው ስለምናምን ነገር ግን በሚገባ የተዘጋጀበት ስብከት ሰዎችን ሊለወጥ ይችላል፡፡

1.1 የስብከት ሥነ-መለኮታዊ መሠረት

የስብከትን ሥነ-መለኮታዊ መሠረት አስመልክቶ ጆን ስቶስ የተባሉት እውቅ ሰባኪና ጸሐፊ በሚከተለው መልኩ ያስቀምጡታል፡፡ ስብከት ከተግባራዊ ሥነ-መለኮት ተርታ የሚመደብ የሥነ-መለኮት ቅርንጫፍ ነው፡፡ ደርዘዊ ሥነ-መለኮት ከሆነው የሥነ-መለኮት ክፍል የሚለው በአብዛኛው ስብከት የሚቆራኘው ከዕለት ተዕለት የአመኙ ጉዞ ጋር በመተሳሰሩ ነው፡፡ ስለሆነም ስለ ስበከት አዘጋገጅትና ስለ ጥሩ ስብከት የጠብራራ ነገር ከማለታችን በፊት ለስብከት መነሻ የሆነን መሠረታዊ ምክንያት ልብ ብሎ ማጤን የተገባ እርምጃ መሆኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን፡፡ ስለሆነም ለስበከት ሥነ-መለኮታዊ መሠረት ከሆነ ሃሳቦች ጋር ትውውቅ በማድረግ ጥናታችንን እንጀምራለን፡፡

ስለ ስነ-ስብከት ከመነጋገራችን በፊት ስብከት ና ሰባኪ ምን ማለት እንደሆኑ ማየት ያስፈልገናል። ከዛ በመቀጠል የስነ-ስብከት ትርጉምን እና ስነ-ስብከት ሊይዝ የሚገባውን ነገሮች እና የስነ-ስብከትም ሆነ የስብከት አላማ ምን ሊሆን እንደሚገባው እንመለከታለን።

ስነ-ስብከት ማለት የስብከት ጥበብን የምናጠናበት የጥናት ዘርፍ ነው ማለትም ስለስብከት ማወቅ ያለብንን አስቀድመን አውቀን ጥሩ ስብከት መስበክ የምንችል ሰዎች ለመሆን የሚረዱንን ስልቶች ማወቅ ማለት ነው። ስነ-ስብከት ከእንግሊዘኛው ሆሚሌቲክስ (Homiletics) ከሚለው ቃል የተተረጎመ ሲሆን የዚህ ቃል ስርወ ቃል ደግሞ የግሪኩ ቃል ሆሚሊያ የሚለው ነው (*Homilia)* ትርጉሙም “መናገር” ወይንም “መነጋገር” ማለት ነው።

ስብከት ማለት

ሀ) ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል የጊዜው የሆነውን ቃል በንግግር መግለጽ ማለት ነው። ስብከት ሳይንስ ነው፣ ጥበብ ነው በተጨማሪም ስጦታ ነው።

- ሳይንስ ነው የምንለው መርህ ስላለው እና ይህን መርህ ተግባራዊ ስናደርግ ስብከታችን ይበልጥ ውጤታማ ስለሚሆን ነው።
- ጥበብ ነው ምክንያቱም መርሆቹን ተግባራዊ ማድረግ በእያንዳንዱ ሰባኪ ክህሎት ላይ የተመረኮዘ ስለሆነ ነው።
- እና ስጦታ ነው የምንለው ደግሞ በሰባኪ ውስጥ ተነሳሽነት፣ ጥሪውና ችሎታው የሚመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው።

- ስነ-ስብከት ማለት መርሆችንና ዘዴዎችን በመጠቀም በተደረገ ጥንቃቄ የሞላበት የስብከት ዝግጅት የሚደረግ ውጤታማ ስብከት ነው።

ለአንተ/ቺ ስብከት የሚያመዝነው ሳይንስነቱ፣ ጥበብነቱ ወይንስ ስጦታነቱ ነው

ስነ-ስብከት በውስጡ የሚያካትታቸው ነገሮች፡-

ሀ) ዝግጅትና መልዕክትን ማቅረብ

ለ) የሰው ድርሻና የመለኮት ተጽዕኖ

ሐ) የሰባኪውና የአድማጩ ግንኙነት

1.2 የስብከት ታሪካዊ ቅኝት

__*ለምንድነው ስብከት ዋንኛ መሆን ያለበት?*__

1. **እግዚአብሔር ከሠው ጋር የሚገናኘው በቃሉ ስለሆነ**

   መዝ (115) ፡2-5፣ ኢሳ 55፡10-11

2. **ስብከት የጌታ ትእዛዝ ስለሆነ /የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ በመሆኑ/**

እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ዋንኛ መንገድ አድርጎ የመረጠው ስብከትን ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዋንኛ አገልግሎት በሌላ አገልግሎት ስትተካ አንመለከትም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ይህን አገልግሉት በዋንኛነት እንድትይዝ ያደረጋት ዋንኛ ምክንያት የኢየሱስ ትእዛዝ ነው /ማር16፡15/፡፡ ጌታችን እንድንሰብክ በማር16፡15 ላይ ትእዛዝ ከሰጠ በኂላ የስብከትን ውጤት በቁጥር 16 ላይ በግልጽ ያስቀምጠዋል፡፡ /ሮሜ10፡14-17’ 1ቆሮ1፡21-24’ 2ጢሞ4፡1-2/

3. **መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሣሌዎች ስላሉን**

ስለ ስብከት አስፈላጊነት መጽሐፍ ቅዱስ ምሣሌ አድርጉ የሚያስቀምጣቸው ሰዎች አሉን። በጣም በርካታ ምሳሌ ሊሆኑን የሚችሉ ሰዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማንሳት ስብከት ከፍተኛ ስፍራ /ዋጋ/ የተሰጠው አገልግሎት መሆኑን ከእነርሱ ህይወት እና አገልግሎት መረዳት እንችላለን።

- **ታላቁ ምሳሌያችን ኢየሱስ ሰባኪ ነበር**

ኢየሱስ አገልግሎቱን በሚጀምርበት ጊዜ ለመስበክ እንደተቀባና እንደመጣ በሙክራብ ውስጥ በማወጅ ነበር የጀመረው። /ሉቃ 4፡18፣ ማር.1፡38-39/ የኢየሱስም የስብከት ውጤት ላመኑት ነጻ መውጣት፣ መፈወስ፣ እና የተትረፈረፈ ሕይወት ሲያስገኝላቸው ያላመኑት ግን በከፍተኛ ሁኔታ በሐጥያቻው ቀጥለው በመንፈሳዊ እውርነት ለመኖር ተዳርገዋል። በኢየሱስ አገልግሎት ስብከት ዋንኛ ስፍራ ነበረው ውጤቱም ከፍተኛ ነበር ማለት ነው። እኛም ዋንኛ ሞዴላችን የሆነውን የኢየሱስን የአገልግሎት መርህ መከተል ይገባናል።

ማቴ10፡7-8፣ ማቴ28፡19-20፣ ማር16፡15-18፣ ሉቃ24፡46-48’ ዮሐ20፡21-23 እና የሐዋ1፡8 ስናነብ የኢየሱስ ትኩረት አማኞች በዋንኛነት በስብከት እንዲያገለግሉ ሲሆን ሌሎቹ ተከታይ እንዲሆኑ ከአቀማመጣቸው መረዳት እንድንችል ያግዘናል።

- **ሀዋርያ ጳውሎስ**

ሀዋርያው ጳውሎስ ስብከት ከሌሎች አገልግሎቶች ሁሉ ዋንኛው አገልግሎቱ እንደሆነ በግልጽ ጽፈዋል። /1ቆሮ1፡17፣ 1ጢሞ1፡12’ 1ቆሮ9፡16/ ሀዋርያው ጳውሎስ የስብከትን በጣም አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት በሚገባ ስለተረዳ እና ስላመነ በሕመም በመከራ ውስጥ ሁሉ ያለማቋረጥ ይሰብክ ነበር። /2ቆሮ11፡23-31/። በቁጥር 28 ላይ እንደምንረዳው ሀዋርያው ሰፊ አስተዳደራዊ ሀላፊነት ቢኖርበትም ወንጌልን ለመስበክ ግን ለአፍታም ወደኋላ አላለም። ከዚህም የምንማረው ሀዋርያው ጳውሎስ የነበሩበት ሌሎች አገልግሎቶች የስብከን ቀዳሚነት ከሕይወቱ አልወሠዱበትም። እኛም ዛሬ ሌሎች አገልግሎቶች የስብከትን ቀዳሚነት እንዳያስጥሉን መጠንቀቅ አለብን። ከዚህም ባለፈ ጳውሎስ የስብከትን ቀዳሚነት /አንገብጋቢነት/ በሚገባ ስላመነ አገልጋዮችን እንዲሰብኩ በማዘዝ እና በማበረታታት የወንጌል ስብከት ከሁሉ እንደሚልቅ አመላክቷል። /2ጢሞ4፡2’ ቆላስ4፡17/

በብሉይ ኪዳን ዘመን በነብያቱ በኩል ስብከት ይተላለፍ ነበር። በነህምያ ዘመን ደግሞ በአምልኮ ጊዜ ቃሉ ይሰበክ ጀመር። ነህምያ 8፡6-8

በኢየሱስ አገልግሎት

- በሙክራቦቻቸው ማቴ. 9፡37 ማር. 1፡14፣39
- የመጣበትም ዓላማ አንዱ ይኸው ነበር ሉቃ. 4፡18
- ደቀመዛሙርትንም አዟቸዋል

በሐዋርይት አገልግሎት

- ሐዋርያት ስብከዋል ሐ.ሥራ 4፡31 ፣ 6፡2 ፣4

ከአንደኛው እስከ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን

- ስብከት በዚህ ዘመን እያሽቆለቆለ መጣ
- የሮማው ቀልሜንጦስ ርዕሣዊ ስብከቶችንና ግብረገባዊ መልዕክቶችን ያስተላልፍ ነበር
- የአሌክሣንድሪያው ቀልሜንጦስ አሌጐሪካል ዘዴን ይጠቀም ነበር

ከሦስተኛው እስከ አምስተኛው ክ/ዘመን

- ስብከት ለቀሳውስት ብቻ የተፈቀደ ነበር፡፡
- የዮሃንስ አፈወርቅ ስብከቶች (John Chrysostom) ተዋቂ ሰባኪያን ነበሩ፡፡ ስብከቶቻቸውም፡-
    - Biblical (መፀሃፍ ቅዱሣዊ)
    - Simple (ቀለል ባለ መልክ የተዘጋጁ)
    - Applicable (ሊተገበሩ የሚችሉ)
    - Bold (በድፍረት የተሞሉ ነበሩ)፡፡

ከስድስተኛው እስከ ተሃድሶ ዘመን 1517 ዓ.ም.

- በዚህ ዘመን ስብከት አሽቆልቆሎ ነበር

- በካቶሊኮች በተለይ ከጳጳሱ ውጪ ማንም አይሠብክም ነበር

Reformers (ተሃድሶ ያመጡትን ስናይ)

- John Wicliff (የሃገሬውን ቋንቋ ተጠቅሟል)
- Martin Luther Sola Scriptura (መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ)
- John Wesley አሜሪካንና እንግሊዝን ለወጠ የለወጠ ሰባኪ
- George Whitfield ለ34 ዓመታት በሣምንት 20 ስብከት ሰብኳል Spergeon የሰባኪዎች ንጉስ ተብሏል፡፡

ስብከት በኢትዮጵያ

9 ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በ6ኛው ክፍለ ዘመን ስብከት መል ያዘ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ13ኛው ክፍለ ዘመን በደብረሊባኖስ ይሰብኩ ነበር፡፡ ከዚያም እስጢፋኖስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ በሚሲዮናወያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ስብከት መልኩን ለወጠ፡፡

4. **ሰባኪዎች እንደ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን መስጠታቸው**

ሌላው የስብከትን ከፍተኛ አስፈላጊነት የምንረዳበት መንገድ አንዱ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ስጦታ የሰባኪነት ስጦታ መሆኑ ነው /ኤፌ 4፡11-13/ የዚህ ክፍል ትኩረት በሠዎች ላይ ሲሆን ሠዎቹም መንፈሳዊ ስጦታን የተቀበሉ ናቸው፡፡ ስለ ሰባኪነት የሚያወሩ ሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በርካታ ናቸው፡፡ /1ቆሮ12፡28፣ ሮሜ 12፡6-8/
ሰባኪነት ጥሪ ሲሆን ጥሪውም በውስጣችን ከፍተኛ የሆነ የመስበክ ፍላጉት እና መነሳሳን ያሳድራል፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ ከጥሪው ጋር በማያያዝ የተናገራቸውን ቃላቶች እንመልከት /ሮሜ 1፡1፣1ቆሮ 1፡17፣ 1 ቆሮ 9፡16/

5. **ስብከት ሠዎችን ሊቀይር መቻሉ/ውጤቱ ከፍተኛ ስለሆነ/**

ስብከት ሁሉም በትክክል ሊያየው እና ሊረዳው የሚችለውን ግልፅ መንፈሳዊ፣ ስነልቦናዊ፣ እና ማህበራዊ ወዘተ ለውጥ ማምጣት ይችላል፡፡ ታሪክ የስብከትን አስፈላጊነት ከቤተክርስቲያን ልደት እስክ አለንበት ጊዜ ድረስ ያረጋግጥልናል፡፡ የመጀመርያው ስለ ክርስቶስ የሰበከው ሠባኪ / መጥመቁ ዩሐንስ / በርካታ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መርቷል፡፡ የኢየሱስ ስብከት ብዙ ሠዎችን ወደ ትክክለኛው መንገድ መልሥአል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ስለ ስብከት

አላማ አሰተመሮአል። የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ የስብከትን ከፍተኛ ውጤትን በግልፅ አስቀምጦልናል። /የሐዋ 2፡14-17፣ 4፡4፣ 6፡7፣ 8፡4፣ 17፡6፣ ሮሜ 1፡8፣ 10፡18/

6. የቤተ ክርስቲያን ልማድ መሆኑ

ቤተ ክርስቲን ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ወንጌልን ስብከት እያከናውነች ትገኛለች። የስብከትን አገልግሎት ሳታቋርጥ በመስበክ እንድትቀጥል ዋና ምክንያት የሆናት ትእዛዙን የተቀበለችው ከኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ነው። /ማር16፡15/ ከዚህ በመቀጠል በተለያዩ ዘመናት ስለተነሱ ታላላቅ ሰባኪዎች እንመለከታለን።

የተሟላና ጠለቅ ያለ የአሰባበክ ታሪካዊ ጥናት በዚህ ትምህርት ላይ ማንሳት አንችልም ኮርሱም ይህን ያህል ሽፋን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንድናነሳ አይፈቅድልንም። ነገር ግን በጥቅሉ በአሰባበክ ጽንሰ-አሳብና ዘይቤ፣ በታሪክ እንዴት እንዳደገና ወደፊትም ምን አቅጣጫ ይዞ እንደሚሄድ ውስን ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል አጭር ማብራሪያ በዚህ ክፍል ላይ እንመለከታለን።

1.3 የቃላት ብያኔ

"ቃሉን ስበክ" የሚለው አስገዳጅ ጥሪ በአመዛኙ የሚሰነዘረው ከአዲስ ኪዳን ስለሆነ "መስበክ" ተብለው የሚተረጎሙትን አራት የግሪክ ግሶች እንመለከታለን። እነርሱም፡-

ኬሩሶ (KERUSSO)፡ በ2ጢሞ.4፡2 ላይ ያገለገለ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም ማሳወቅ ወይንም ማወጅ ማለት ነው። በማርቆስ 1፡46 ላይ በNKJV "ማወጅ" የተባለው ወይንም በNIV ላይ "ዜናውን የሚያሰራጭ" ተብሎ በአመዛኙ በሕዝብ ፊት እንደሚነገር ሆኖ ቀርቧል። ማቴ.24፡24 ወንጌል እንደሚሰብክ ወይም እንደሚነገርና መጨረሻው እንደሚመጣ ያወሳል። ይህ ውጤትን ወይም እንዲሰማ ታስቦ የሚተላለፍን መልዕክት እንጂ እምብዛም የንግግርን አቀራረብ የሚያመለክት አይደለም።

ኢዋንጂሊዞ (EUANGELIZO) ፡ ይህ ቃል "መስበክ" ወይንም "ማወጅ" ተብሎ ተተርጉሟል። ሆኑም ግን የሚታወጅ ነገር የምስራች ቃል ስለመሆኑ ተጨማሪ አሳብ ይሰጣል። አብዛኛው ግልጋሎቱ በወንጌል የተነገረለትን የእግዚአብሔር ልጅ የሚያመለክት ነው። ከዚህ ቃል evangelize እና evangelism የሚሉትን ቃላት እናገኛለን። ሉቃስ 4፡ቀ8 "ወንጌልን እሰብክ ዘንድ" ይለዋል። የሓዋ.8፡4 "ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ" ይላል።

ፐሮኬሩሶ (PEROKERUSSO) ፡ ይህ ቃል ትርጉሙ እንደማስታወቂያ አስቀድሞ ማወጅ ወይንም "መጀመሪያ መስበክ" ማለት ነው።

ፓርሄሲያዞማይ **(PARRHESIAZOMIA)** ***፡ የሐዋ.9፡27ን ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ እንዴት ያለፍርሃት በድፍረት እንደሰበከ ለመግለጽ ይጠቀምበታል።***
ከነዚህ የቃላት ዳራ በመነሳት የሚደርሱባቸው በርካታ ድምዳሜዎች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ቃሉን መስበክ ማለት ከምስባኩ በስተኋላ መቆም ማለት ሳይሆን ቃሉን የማወጅ ተግባር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ስብከታችን እንደ የመስራች ዜና መስማት እንዳለበት በአጽንኦት ያስቀምጣል። ይሄ ደግሞ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ይዘት እንዳለውና ለሰዎች ችግር የሚናገር መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል። በመጨረሻም መልዕክቱ ተሰብኳል የሚባለው ተደማጭነት ወይንም ግንዛቤ ሲያገኝ ነው።
እንደ ሪቻርድ ራሚሽ ስበከት ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በመግለጽ ሰዎችን ከተዘፈቁበት ችግር ነጥሎ የሚያወጣ ህይወት ለዋጭ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን እውነት ለራሱ ተረድቶ ይዘቱን ሣይለውጥ በመንፈስ ቅዱስ ተደግፎ ለሰዎች የሚቀርብ የእግዚአብሔር መልክት ነው፡፡ «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን ስብከት ደግሞ እኛ ከእግዚአብሔር ቃል የምናዘጋጀው መልእክት ነው፡፡»

በአጠቃላይ ስብከት ማለት፡- የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ማብራራት ዓላማውም በሰዎች ህይወት ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ስብከት አዋጅ ስለሆነ ፋታ የማይሠጥ አጣዳፊ መልዕክት ነው ስብከትና ሪፓርት ማቅረብ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሣሌ፡- ዮናስ_ለነነዊ ህዝብ መልዕክት ሲሰጠው በአፋጣኝ ማቅረብ ነበረበት ምክንያቱም አጣዳፊ ነውና፡፡ ከሦስት ቀን በኂላ ትጠፋለችሁ የሚልን መልዕክት ለዘብ ብሎ ማወጅ የማያስኬድ ነውና፡፡

ስንሰብክ በተለያዩ መልክ ስሜታችንን ልንገልጥ እንችላለን ምክንያቱም አስተያየት ሣይሆን አዋጅ (ብቸኛ አማራጭ) የሆነውን ነገር እየተናገርን ነውና፡፡ ኢየሱስ ጮክ ብሎ ተናግሮ ነበር ዛሬም እንደዚያ ቢደረግ ሊደንቀን አይገባም፡፡

ከመድረክ ለምናስተላልፈው መልዕክት ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን በትክክል እንድናቀርብ ይፈልጋልና መድረክ ስናገኝ አንቀልድ፡፡ ቃል ይልተገለጠበት ጨኸት ባደ ነው፡፡

1.4 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ስብከቶች ዳሰሳ

መቼም መጽሐፍ ቅዱሳችን ያላሳየንን ከየትም አምጥተን ስብከት እንዲህ ያለ ነው ማለት አንችልም ምክንያቱም የምንሰብከው የተሰበከበትን መጽሐፍ ቅዱስ ነውና። ስለዚህ በብሉይ

ኪዳን፣ በአዲስ ኪዳን እንዲሁም በቤተክርስቲያን ዘመን ስብከት እና ሰባኪነት እንዴት ይታዩ እንደነበር በወፍ በረር እንቃኛለን።

በብሉይ ኪዳን ስብከት ምን ይዘት ነበረው?

የብሉይ ኪዳን ስብከት የመጣው የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ወይንም አስተርጓሚ ከነበሩት ነቢያት አገልግሎት ነው። ነህሚያ 8፡6-8 ስለ ጸሐፊው ዕዝራ "መጽሐፉን ገለጠ… እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር።" ይላል። ይህ ሕዝብ በተሰበሰበበት አምልኮ ላይ ስለመስበካቸው ምሳሌ የሚሰጥ ይመስላል።

የኢየሱስ ትምህርት ከግማሽ የሚልቀው በጥያቄ ወይም "በሕይወት ጉዳይ" የተቀሰቀሰ ነው። ይህ ማለት እርሱ የጀመረው ችግርን መነሻ በማድረግ እንጂ መጽሐፍን አይደለም። ብዙ ጊዜ እንደ ጭውውት ዓይነት ቃለ ምልልስና አንዳንዴ ደግሞ ንግግርን (ለምሳሌ የተራራው ስብከት) ተጠቅሟል። በእርሱ ዘመን የነበረ የምኩራብ አምልኮ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ ንግግር፣ ጥያቄና የአሳብ ልውውጥ ጊዜን ያካተተ ነበር።

በአዲስ ኪዳን ስብከት ምን ይዘት ነበረው?

በአዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጨምሮ ብዙ ሰባኪዎችና ስብከቶች ያሉ ሲሆን የስብከታቸው ማዕከል "የእግዚአብሔር መንግስት መጥታለችና ንስሃ ግቡ" የሚል ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ይህንን አጽንኦት ሰጥቶ የሰበከ ሲሆን ሃዋሪያቶችና እነ ጳውሎስ ደግሞ ኢየሱስን የምስራች ብለው ሰብከው አልፈዋል። የጳውሎስ ስብከት በአመዛኙ በወንጌል ስርጭት ላይ ያተከረ ነበር። ከሰዎች ችግር ጋር ማዛመድን የሚያውቅ አድማጩን የሚያገናዝብና (ለምሳሌ 1ቆሮ.9፡22 በአቀራረቡ ደግሞ አመክኖአዊነትን - ለምሳሌ የሐዋ.17 የተከተለ ነበር። ምንም እንኳን ራሱን ብርቱ ሰባኪ አድርጎ ባይቆጥርም ከንጉስ አግሪጳ ምላሽ እንደምንገምተው አግባቢም ነበር። የጴጥሮስና የእስጢፋኖስ የአሰባበክ ስልት የሚያሳየን የአንድን ሰው ለረጅም ጊዜ የመተረክ ምሳሌን ነው። ሁለቱም ግን ስብከታቸው በጣም በአመክንዮአዊነት (logical) የበለጸገና ገላጭነትን የተላበሰ ነበር።

ለሚከተሉት ጥያቄዎች የግል ግንዛቤንና ከዚህ ጥናት ያገኛችሁትን በማነጻጸር ምላሽ በመስጠት የራሳችሁን ግንዛቤ ፈትሹ።

1. የራስህን/ሽን የስብከት ሂደት በማሰላሰል ከየትኛው የስብከት ትርጓሜ ጋር ይዤዳል (ስብከት ከሚመስሉት ወይንስ ስብከት ከሆኑት)

2. ሌሎች ተጨማሪ ጥናቶችን በማካሄድ በስብከታቸው አንቱ የተባሉ ሰባኪዎችን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመፈተሽ ለራስህ/ሽ ዕድገት የሚሆነውን ያገኘሽውን ትምህርት በአጭሩ ለመተንተን ሞክር/ሪ
3. ለዚህ ዘመን ሰባኪያን ከዚህ የስነ ስብከት ትርጓሜ አንጻር የምታስተላልፈው መልዕክት ምን መሆን አለበት

በየክፍለ ዘመኑ የነበሩ የስብከት የትኩረት አቅጣጫዎችን የተለያዩ ተጨማሪ ጥናቶች በማከናወን በሁለት ገጽ በመግለጽ በአሁኑ ዘመን ያለው የስብከት አትኩሮት ምን ሊሆን እንደሚገባ ግለጽ፡፡

ምዕራፍ ሁለት፡ የስብከት አይነቶች

መግቢያ

የተለያዩ የስብከት አይነቶች ሲኖሩ የተለመዱት አምስት አይነት የስብከት መንገዶች አሉ። እነርሱም፡ -ምሳሌያዊ ስብከት (Allegorical Sermon)፣ ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት (Biographical Sermon)፣ ርዕሳዊ ስብከት (Topical Sermons)፣ አንድ ክፍል ላይ የተመሰረተ ስብከት (Textual Sermons) እና ገላጭ ስብከት (Expository Sermons) ናቸው። እነዚህን የስብከት አይነቶች በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

 የምዕራፍ ሁለት ዋና ዓላማዎች/ግቦች

- ስብከት ብዙ መገለጫ እና ዓይነት እንዳለው ተረድተው ስብከቶቻቸውን እንዲወስኑ ለመርዳት
- በስብከት ዓይነቶች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት እንዲገነዘቡ ማድረግ
- የራሳቸውን የስብከት አቅጣጫ በመረዳት በዛ ላይ ጥቅ ጥናት እንዲያደርጉ ለማበረታታት
- በየስብከት አይነቱ ያሉትን ጠንካራ ጎኖችና ደግሞ ጥንቃቄ የሚያሻቸውን ጉዳዮች እንዲያውቁ ለማድረግ

2.1 ገላጭ ስብከት (Expository Sermons)

ትርጉሙ

ገላጭ ስብከትን አስመልክቶ ብዙ መልካም ትርጉሞች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን እንመለከታለን። አንደኛው፡ ገላጭ ስብከት ማለት የአንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ትክክለኛ የአተረጓጎምን ስርዓት ተከትሎ በማግኘትና ማዕከላዊ አሳቡን ከወቅቱ ጋር በማዛመድ ወይም በማገናዘብ ውጤታማ በሆነ የአሳብ ግንኙነት የአማኞችን የአህምሮ መረዳት ለማሳደግ ልባቸውን ለማቅናትና ባህሪያቸው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንዲያድግ መርዳት ነው ይላል።[1] ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ፡ ገላጭ ስብከት ማለት ይብዛም ይነስ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስዶ በጊዜው ለነበሩ ምን ማለት እንደነበር ለእኛ ድግሞ ምን ማለት እንደሆነ የምንሰብክበት የስብከት አይነት ነው።[2] በዚህ ትርጉም መሰረት ገላጭ ስብከት መሰረት የሚያደርገው፡

1. ይህ ገላጭ ስብከት በጥቂት ቁጥሮች ላይ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ጠቅላላ ምዕራፉን አልያም ከዛም በሰፋ ሁኔታ የሚደረግ ዝግጅት እንደሆነ ያሳየንል።

2. ይህ የገላጭ ስብከት ዋና አሳቡን በማይለቅ ሁኔታ ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ ሰዋሰውን፣ ጊዜውን …ወዘተ ከግምት በማስገባት ሰፋ ያለ ገለጻ በክፍሉ ላይ መስጠት ማለት ነው።

3. የገላጭ ስብከት ማብራሪያዎች በሙሉ ከአውዱ ሳይወጡ የሚደረጉ ሲሆን ክፍሉ የሚለውን አሳብ ለማዳበር እስካልሆነ ድረስ ከሌላ ክፍል ላይ አሳብን ማንሳት የሚያስደፍር አይደለም ማለት ነው።

ምሳሌ፡ መንፈሳዊ ውጊያ (ኤፌ.6፡10-18)

I. የክርስቲያኖች ወኔ ቁ.10-13

1. ከፍተኛ መሆን አለበት ቁ.10

2. ጽኑ መሆን አለበት ቁ.11-13

II. ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ጦር መሳሪያዎች ቁ.14-17

1. ለማጥቃት የሚጠቅሙ መሳሪያዎች ቁ.14-17ሀ

2. ለመከላከል የሚረዱ መሳሪያዎች ቁ.17ለ

---

[1] በዶ/ር ራሚሽ ሪቻርድ (ትርጉም በገበየሁ አየለ)፣ ***የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት፣*** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡ በላፕሰሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን የታተመ፣ 1995 ዓ.ም.

[2] አርኤል ሞዝ፣ ***ሕይወት ለዋጭ ስብከት፣*** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡ አሳታሚ- አይ ኢ ሲ በስ አይ ም ማተማያ ቤት የታተመ፣ 1999 ዓ.ም.

III. የክርስቲያኖች የጸሎት ሕይወት ቁ.18

1. በትጋት የሚደረግ ጸሎት ቁ.18ሀ

2. በምልጃ ቁ.18ለ

ማጠቃለያ፡ ገላጭ ስብከት ማለት

- አንድን መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስዶ ማብራራት ማለት ነው
- ይህ ክፍል ደግሞ ረዥም ወይንም አጭር ሊሆን ይችላል
- ምን አልባትም እንደአስፈላጊነቱ ተለያዩ ተመሳሳይ ክፍሎችን ሊያካትት የሚችል የስብከት አይነት ነው

ጥቅሙ

የገላጭ ስብከት በጎ ተጽዕኖ

ገላጭ ስብከት በሕይወትዎ ላይ ልዩ በጎ ተጽዕኖ ሊያደርግና ቀጥሎ ባሉት ነገሮች ሊረዳዎ ይችላል።

- ስርዓት ባለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት፣ በዕውቀትና በታዛዥነት እንዲያደርጉ
- ለእያንዳንዱ ሳምንት የሚሆን ስብከት ሲመርጡ የሚያባክኑትን ጊዜና ጉልበት እንዲቆጥቡ
- በሚገባ በሚያውቋቸውና በሚመርጧቸው ችእሶች ብቻ ላይ ከማተኮር ይልቅ ሰፊ ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል እንዲሰብኩ።

ገላጭ ስብከት ለጉባኤው መንፈሳዊ ሕይወትም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ምክንያቱም እርስዎን በሚከተሉት መንገዶች ይረዳዎታልና።

- በዕለት ተዕለት አገልግሎትዎ ለቃሉ ታማኝ እንዲሆኑ እንዲሁም ላሉበት ሁኔታ ወይም አካባቢ የሚጠቅም መልእክት እንዲያስተላልፉ
- ለሕዝብዎ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔርና ለአገልግሎቱ ታማኝ ይሆን ዘንድ ቃሉን የማስታጠቅና ብርቱ የማድረገህ ዘዴን በስራ ላይ እንዲያውሉ
- ስብከትዎን በተለየ ሰው ወይም ቡድን ላይ ያተኮረ እንዲሆን የማድረግ ዝንባሌዎን ለማስወገድና ከሚቀርብብዎም ወቀሳ እንዲድኑ

- በስብከትዎ ዕለት ካሉበት ስሜት ጋር ወይም ከምርጫዎ ጋር የማይሄዱ የሚመስሎዎትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በዝምታ እንዲያልፉ ወይንም እንዳይዘሏቸው
- በሚሰብኩበት ጊዜ የሚቆሙት በእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ስር ስለሆነ ለመጋቢነት ስራዎ ሞገስን በመስጠት
- ጉባኤው የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እንዲኖረው በመርዳት
- ባጠቃላይ ገላጭ ስብከት ሰባኪው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን አጀንዳ ያሳውቅ ዘንድ ይረዳዋል።

ሲጠቃለል የሚከተሉት በጎ ጎኖችን ከገላጭ ስብከት ማየት ይቻላል።

- መንፈስ ቅዱስ በሚያመለክተን መንገድ ክፍሉን እንድንረዳ ማድረጉ
- በጥልቀት መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንድንመረምር ስለሚያደርገን
- ለሰባኪው ደስ በሚለው ነገር ብቻ እንዳይወሰድ ስለሚያደርገው
- ሰባኪው እንዳፈቀደለት ያልገባውን ጉዳይ ከክፍሉ እንዳይዘለው ማድረጉ

ገላጭ ስብከት ስናዘጋጀ ልናየው የሚገባ ጉዳይ

- እርሳችንን እንደሚገባ እንዳናብራራ ይገድበናል
- ሰባኪው በሚፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በነጻነት እንዳይናገር መገደቡ

የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ደረጃዎች

የገላጭ ስብከት አዘገጃት ደረጃዎች አስር ሲሆኑ እነርሱም፡-

1. የምንሰብከውን ክፍል መምረጥ

አንድ ሰባኪ ምንድን ነው የምሰብከው ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት። ምናልባት አልፎ አልፎ ሰባኪዎች ምንም አይነት ዝግጅት ሳያደርጉ ወደምሳብኮቻቸው ከወጡ በኋላ ሕዝቡን ካዩ በኋላ አልያም ፕሮግራም መሪው ከሚነሳበት ጥቅስ ጋር ግንኙነት ያለውን ክፍል መርጠው የያዙትን ክፍል እግዚአብሔር እንደሰጣቸው አድርገው እንደሚናገሩት አይነት ልምድ ላለን ሰዎች የሚከበድ ቢሆንም የምንሰብከውን ክፍል ወስነን መምረጥ ግን የግድ

ነው። የምትሰብከውን ክፍል ለመመርጥ የሚከተሉትን መንገዶች ከግንዝቤ ማስገባት አለብህ። እነዚህም፡-

- ለጉባኤው እግዚአብሔር ሊናገር የሚፈልገውን ነገር ለመረዳት በጸሎት አምላክህን መጠየቅ (የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ሰምተህ ክፍሉን መወሰን)
- ጉባኤውን የምታውቀው ጉባኤ ከሆነ ለሕዝቡ ካሉበት ሁኔታ አንጻር ምን መስበክ እንዳለብህ አስበህ መወሰን
- የተለያዩ የቤተክርስቲያን ባህላትና ክንዋኔዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍሎች መምረጥ (አንዳንድ ቤ/ክ እንደሚያደርጉት ለምሳሌ የገና በአል፣ የፋሲካ፣ የሽማግሌ ምርጫ የሚከናወንበት ወቅት…)
- ምናልባት ደግሞ ተጋባዥ ሰባኪ በምትሆንበት ጊዜ ደግሞ የተጋበዝክበት ቤ/ክ የሚሰጡህ ርዕስ ወይንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካለ በእርሱ ላይ ለመናገር ራስህን ማዘጋጀት ይኖርብሃል።

2. የምትሰብከውን ክፍል ማጥናት

ለመስበክ የወሰንከውን ክፍል ማጥናት አለብህ። የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከዚህ በፊት ስለሰበክንና ስላነበብን ሙሉ ለሙሉ ተረድተነዋል ማለት አይደለም ይልቁንስ የእግዚአብሔር ቃል ዕለት ዕለት አዲስ መረዳትን የምናገኝበትና መንፈስ ቅዱስም ከክፍሉ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን እንድናይ ስለሚያደርገን ራሳችንን በመንፈሱ ስር በማድረግ ክፍሉን በጥንቃቄ ማጥናት አለብን። በጥንቃቄ ማጥናት ማለት አስፈላጊ የማጥኛ መረጃዎቻችን (የማጥኛ መረጃዎች ማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ኮንኮርዳንስ፣ ኮመንታሪ፣ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እና ወዘተ ናቸው) በመጠቀም ከክፍሉ ጋር ራሳችንን ማቆራኘት ማለት ነው። በምናጠናበት ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ማስገባት አለብን። እነርሱም፡-

- የመፅሐፍ ቅዱስ ሥነ-አፈታት ሕጎችን መከተል

መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንዳፈቀደልን ለማለት የፈለግነውን እንዲልልን ልናስገድደው አይገባንም ይልቁንስ መጽሐፍ ቅዱሳችንን መረዳትና መፍታት የምንችልበት የስነ-አፈታት መርሆችን አይተን በትክክል ልንጠቀምባቸው ይገባናል።

- የቃላት ፍቺና አተረጓጎም መከተል

ከዚህ በፊት በሄርምኒዩቲክስ ትምህርት ዘርፍ ላይ እንደተነጋገርነው ቃላት እጅግ ትልቅ ሚና እንዳላቸው እናውቃለን። ቃላትን በትክክል ላኩበት አውድ ሳናወጣቸው ያላቸውን ፍቺ ማወቅ አለብን። ስለዚህም የአተረጓጎም መርህዎችን ተጠቅመን መፍታት አለብን።

3. የምትሰብከውን ዋና ሀሳብ መምረጥ

ክፍሉን ከወሰንክ እና ካጠናህ በኋላ የምታደርገው ነገር ቢኖር ክፍሉ ምን አይነት ዋና አሳብ የሚንሸራሸርበት ነው የሚለውን መለየት እና ዋና አሳቡን መያዝ አለብህ። በያዝኩት ክፍል ላይ ለመስበክ የሚገባኝ ዋና አሳብ ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ ለይተህ አውጣና ያዝ።

4. የስብከቱን ዓለማ መወሰን

ይህንን ዋና አሳብ ለማስተላለፍ ዓላማህን ማወቅ ማለትም የምሰብከው ለምን አላማ ነው የሚለውን ጥያቅ መመለስ መቻል ማለት ነው። ይህ የሚጠቅመው ዓላማ ይዘህ ወደምስባኩ እንድትወጣ ነው። ያለአላማ የምታደርገው ንግግር ፍሬ አልባ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ዋና አላማዬ ከያዝኩት ዋና አሳብ አንጻር ምን መሆን አለበት? የሚለውን ጥያቄ ለያዝከው ክፍል ታማኝ ሆነህ መለየት አለብህ ማለት ነው።

5. የስብከቱን መግቢያና መደምደሚያ ማዘጋጀት

አሁን ዋና አሳብ ከክፍሉ ላይ አውጥተሃል ያንን አሳብ ለማንጸባረቅ ስብከትህ መያዝ ያለበትን ዋና አላማ ለይተህ አውቀሃል። አሁን በመቀጠል ይህንን አላማህን ከግብ ለማድረስ ከምን ንግግርህን እንደምትጀምርና በምን እንደምትጨርስ ማዘጋጀት አለብህ። ይህን መግቢያና መደምደምያ ለማዘጋጀት ማወቅ ያለብህ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

i. መግቢያህ መያዝ ያለበትን ማወቅ

መግቢያ የሙሉ ስብከትህን ተደማጭነት የሚወስን መሆኑን መረዳት አለብህ። ምክንያቱም “ነገር ካያያዙ ያስታውቃል” እንደሚል ብሂል ከምን እንደምትጀምር ሰሚዎችህ ሲያዩ ወዴት እንደምትሄድ መገመት ይችላሉና ነው። ስለዚህ ለመግቢያ እጅግ መጠንቀቅ አለብህ። መግቢያህን በምታዘጋጅበት ወቅት፡-

ሀ. ሙሉ የመልዕክትህን አሳብ በአጭሩ መግቢያ ውስጥ መክተትህን አትዘንጋ

ለ. መግቢያ ሰሚዎችህን ለሚቀጥለው ዋና ስብከትህ የሚያዘጋጃቸው መሆኑን ተረድተህ በተቻለህ መጠን አጓጊና የሰውን ልብ የምታገኝበት እንዲሆን አድርግ

ሐ. መግቢያ ወደአንድ ነገር መተላለፊያ እንደመሆኑ መጠን ሀሉንም ጉባኤ ይዘህ የምትገባበት በር እንደሆነ አስበህ ሁሉንም ያማከለ ለማድረግ ጉባኤው ያለበትን የት/ት

ደረጃ ወይንም የጾታ ልዩነት ባማከለ መልኩ ሁሉንም ሊያሳትፍ እንዲችል አድርገህ ቅረጸው

መ. መግቢያህ ላይ አጽንኦት የምትሰጠው ነገር ምን እንደሆነ ግልጥ አድርገህ አስቀምጥ

ሠ. መግቢያ ከጉባኤው ጋር የምትግባባበት ስለሆነ ጥሩ ተግባቦት የምትፈጥርበት አድርገው

ii. መደምደሚያ መሆን ያለበትን ማወቅ

ብዙ ጊዜ ሰው በንግግሩ የተነሳበት እና ወደ ድምዳሜ የሚመጣበት መንገድ ለየቅል ይሆንና አድማጩን ስብስብ ያለ መልእክት እንዳይዝ ያደርጋል ስለዚህ የተነሳህበትንና የምትደርስበትን አስቀድመህ ማመሳሰል ወይንም ማገናኘት አለብህ። ይህንም ለማድረግ የሚከተሉትን ስለመልዕክት መደምደሚያ ያሉ እውነታዎችን ከግምት ውስጥ አስገባ። እነዚህም፡-

ሀ. መደምደሚያ ፈጽሞ አዲስ አሳብ የሚያንጸባርቅ መሆን የለበትም ይልቁንስ በመግቢያህና በዝርዝር አሳብህ ውስጥ ይንሸራሸሩ የነበሩ አሳቦችን በአጽንኦት የምትደመድምበት መሆን አለበት

ለ. መደምደሚያህ የተባለውን ሁሉ የምታስርበት የመጨረሻ ማሰሪያ ንግግር ስለሆነ አስረህ ቋጥረህ ለአድማጮችህ የምታስጨብጥበት ማቋጫ ነው ስለዚህ የነገርህ መቋጫ እንደመሆኑ መጠን ያልካቸውን ሁሉ ያልክበትን ምክንያት በማሰብ የምትዘጋበት መንገድ ማድረግ አለብህ ማለት ነው።

ሐ. መደምደሚያህ አድማጮችህን የመልዕክትህን ዋና አሳብ ይዘው የሚወጡበት የመጨረሻ ስራ የምትሰራበት ጊዜ ስለሆነ መደምደሚያህን ሰዎች ለጸሎት፣ ለተግባር እና ለውሳኔ በሚያበቃቸው መንገድ ማቅረብ አለብህ።

6. የምትሰብከውን ክፍል ማዳበር (ቅርፅ ማስያዝ) አስተዋፅዖ ማበጀት

አሁን መግቢያ አለህ መደምደሚያም አለህ ስለዚህ በስብከትህ ውስጥ ምን ምን ነገሮችን እንደምታነሳ ስብከትህን ቅርጽ የማስያዝ ስራ መስራት ትችላለህ ማለት ነው። ይህን ማደራጀት ስራ በምትሰራበት ወቅት የዋና አሳብህ ዝርዝር አሳቦችን ማውጣት፣ ዝርዝር አሳቦችህን የምታንሸራሽርበትን አውት ላይን ማዘጋጀት እና በሚገባ የአሳብ ፍሰት በመካከላቸው እንዲኖር ማድረግ አለብህ።

7. ለምትሰብከው ክፍል ምሳሌዎች ተጠቀም

ምሳሌ ሰዎች የምትናገረውን ነገር ግልጽ እንዲሆንላቸው የሚያደርግ ሲሆን አይዘነጌነትን በሰሚዎች ልብ የመፍጠር ሃይል ስላላቸው ምሳሌዎችን መጠቀም አለብህ። ይህንም

ለማድረግ ምሳሌ ማዘጋጀት አለብህ ግን የምትሰጣቸው ምሳሌዎች በትክክል ከምትናገረው ፍሬ ነገር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።

8. የምትሰብከውን ሕዝብ (ጉባዔ) እወቅ

አሁን ሁሉን ጨርሰሃል ምን እንደምትሰብክ፣ እንዴት እንደምትሰብክ፣ ከምን እንደምትጀምር፣ ለጥቆ ምን እንደምትል፣ በምን እንደምትቋጭ እና ምን አይነት ምሳሌዎችን መልእክትህን ለማዳበር እንደምትጠቀም አውጥተሃል አውርደሃል። ነገር ግን ለነማን ነው የምሰብከው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይቀርሃል። ይህ የሚጠቅምህ የስብከት ጊዜህን ለመወሰን፣ በሚገባቸው መንገድ ስብከትህን ለማቅረብ፣ እና ከመሄድህ በፊት ስለአለባበስህ እና የአነጋገር ይዘትህ እንድታስብ ያደርግሃል። ምናልባት ሁሉን ጨርሰህ ስለምትሰብከው ሕዝብ አታውቅ ይሆናል ነገር ግን ማወቅ እስከቻልክ ድረስ ሕዝቡን ልታውቅ ይገባል።

9. የተዘጋጀኸውን ስብከት በደንብ ስበክ

ይህ ከስብከት ዝግጅትህ የመጨረሻው ስራህ ሲሆን ዝግጅትህን ሁሉ የምትደመድምበት የምስባክ ስራ ነው ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰባኪዎች በደንብ ከተዘጋጁ በኋላ በደንብ የተዘጋጁትን ያህል ሰብከው አይወርዱም ለዚህም ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በጉባኤው ውስጥ በዕለቱ የሚያዩት የፕሮግራም ይዘት ማለተም ፕሮግራም መሪው የሚመራበት ሁኔታ፣ የዘማሪዎች ሁኔታ፣ የሕዝቡ ሁኔታ የተዘጋጀውን ያህል እንዳይናገር ያደርገዋል።
- ስብከቱን ከጉባኤው ካለበት ሁኔታ አንጻር አይመጥንም ወይንም ለእኔ ስብከት የሚሆን መንፈስ ማግኘት አልቻልኩም ብሎ ማሰቡ። አንዳንድ ጊዜ “ለተነቃቃ” ጉባኤ ብለን አስበን እንሄድና ጉባኤው በአንጻሩ “የተኛ” ያህል በሚመስልበት ወቅት የተዘጋጀነውን ያህል ሳንሰብክ እንወርዳለን
- ሌላው ለራሱ የሚሰጠው ግምት እና ለጉባኤው የሰጠው ግምት የተለያየ በሚሆንበት ጊዜም ይህ አይነት ችግር ሊገጥመው ይችላል ሰባኪውን።

ስለዚህ የተዘጋጀውን ያህልና በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ሆኑ በሚገባ መልዕክቱን ማስተላለፍ እንዲችል የሚከተሉትን ግንዛቤዎች መያዝ አለበት።

✓ ለሰባኪው ስብከት መሠረት መሆን ያለበት በጉባኤው ውስጥ የሚያየው ሳይሆን ከመንፈሱ መስማቱ ላይ መሆን አለበት።

- ✓ የምታየው ነገር በምን መልኩ ብታስተላልፈው በመልዕክት ውጤታማ ትሆናለህ የሚለውን እንጂ ከመልዕክትህ ይዘት ጋር አይሄዱም ብለህ ቆንጆል አሳብ እንድታካፍል ሊያደርግህ አይገባም።
- ✓ ልትሰብክ የተዘጋጀህበት መልዕክት ከሰጪው እንጂ ካንተ ማንነት ጋር ስለማይነጻጸር መልእክትህን በታማኝነት ማቅረብ እንዳለብህ መወሰን ምክንያቱም ጉዳዩ ተባልከውን ብለሃል እንጂ ሰውን አስደስተሃል የሚለው አይደለምና!

10.ስብከትህን ገምግም

አሁን ሰብከህ ጨርሰሃል እግዚአብሔር ይመስገን! ነገር ግን ጳውሎስ እንደሚል "ከሰበኩ በኋላ የተጣልኩ እንዳልሆን…" እንደሚል አንተም ከስብከትህ በኋላ ምን እንደሰበክ እንዴት እንደሰበክ ቁጭ ብለህ በማሰላሰል ለነገ ደካማ ጉንህን የምትቀርፍበት ጠንካራ ጎንህን የምታጎለብትበት ግምገማ ያስፈልግሃል። ይህን የግምገማ ስራ በሶስት መንገድ ልታደርግ ትችላል። እነሱም፡-

ሀ. በመቅረጸ ድምጽ የመያዝ ልምድ ካለህ መልሰህ በመስማት

ለ. ከተለያዩ ስበከትህን ከሰሙ ወገኖች (በታማኝነት ሊነግሩህ ከሚችሉ) በመስማት እና

ሐ. በግልህ በማሰላሰልና መንፈስ ቅዱስ በስብከትህ ዙሪያ እንዲመክርህ በመጸለይ ስብከትህን ልትገመግም ይገባል።

ገላጭ ስብከትን ለማዘጋጀት መሰረታዊ መርሆች

1. ማንኛውም ክፍል በጥንቃቄ እና በማስተዋል ሊጠናና ትክክለኛውን ትርጓሜ እና ማዕከላዊ አሳቡን ልናገኝ ይገባናል
2. በምናጠናበት ወቅት ማስታወሻ መያዝ
3. እስከታወቀ ድረስ ታሪካዊውን የክፍሉን አውድ ልንረዳ ይገባናል
4. ዝርዝር አሳቡ ሊገለጽ ይገባል ነገር ግን አላስፈላጊ የሆነ ጊዜ እንዳናጠፋ ልንጠነቀቅ ይገባናል
5.በክፍሉ ላይ ያለው እውነት ለጊዜው ለነበሩ ሰዎች እና አሁን ላለነው ክርስቲያኖች ያለውን መልዕክት በሚገባ ማስተላለፍ የምንችል መሆን አለብን።

ገላጭ ስብከቶችን ለማዘጋጀት መደረግ ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. መርጃ መሳሪያዎችን አስቀድሞ ማዘጋጀት ፡ መጽሐፍ ቅዱስ (ቢቻል ከሁለትና ከሶስት በላይ ትርጉሞችን)፣ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ ኮንኮርዳስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ

ቃላት፣ከመንታሪስ እና ሌሎች ተመሳሳይ መጽሃፍት ቅደመ-ዝግጅት ውስጥ የሚገቡ የጥናት መርጃዎች ናቸው። እነዚህን መረጃዎች ለምን እንጠቀምባቸዋለን? ምክንያቱም፡-

a. ተናጋሪው ወይንም ጸሃፊውን ለማወቅ

b. ተናጋሪው ወይንም ጸሃፊው ከየት ሆኖ እንደጻፈው ለመረዳት

c. ተናጋሪው ወይንም ጸሃፊው መቼ እንደጻፈው ለማወቅ.

e. ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበር ለመረዳት በተጻፈበት ወቅት

f. ጸሃፊው ምን አላማ ነበረው የሚለውን ለማወቅ

2. የምንናገርበትን ክፍል እንደሚገባ ማንበብ እና ማሰላሰል

3. የክፍሉን ቁልፍ ቃል በጥንቃቄ መምረጥ

4. የክፍሉን እና የስብከትህን ዋና አሳብ ለይቶ መገንዘብ

5. ዋና አሳብህን የሚዘረዝሩልህን ክፍፍሎች በጥንቃቄ ማውጣት

6. መግቢያን መደምደሚያ መስራት

7. አሳብህን የሚያብራሩልህን ምሳሌዎች ወይንም ተፈጸሙ ታሪኮችን ማዘጋጀት

8. ጸልየህ ዝግጅትህን መቋጨት

የገላጭ ስብከት ናሙና

አሁን ደግሞ በገላጭ ስብከት መሠረት የተዘጋጁ ከብሉይ ኪዳን አንድ ክፍል እና ከአዲስ ክፍል አንድ ክፍል ወስደን ለናሙና እንመለከታለን። በዚህ የናሙና ስብከት ላይ ሁለት አይነት አቀራረቦችን እንመለከታለን። **ማሳሰቢያ፡** ይህ አቀራረብ ግን ከብሉይ ለሆኑት እዚህ ጋር በምናየው ለአዲስ ኪዳን ደግሞ እዚህ ጋር በምናየው ብቻ እንሰብካለን ማለት ሳይሆን ኩለቱም ኪዳኖች እንዳመቸን አይነት አቀራረብ ማቅረብ እንደምንችል ለማሳየት ነው።

- ❖ **ናሙና አንድ፡** ከብሉይ ኪዳን አንድ የገላጭ ስብከት ምሳሌ የሚሆነን ክፍል ከመዝሙር መጽሐፍ እንመልከት።

የምንሰብከው ክፍል፡- መዝ.23፡1-6

ርዕስ- “በደስታ የተሞላ ሕይወት”

መግቢያችንን በሚከተሉት መልኩ ልናቀናጅ እንችላለን። እነርሱም ዋና የስብከታችን ፍሬ አሳብን በመግለጥ እና በዚህ ክፍል መሰረት የሚመለስልን ጥያቄ ምን እንደሆነ አድማጮቻችን በጥያቄ ውስጥ ሆነው ስብከታችንን እንዲከታተሉ ማድረግ እንችላለን።

በዚህ መሰረት ለዚህ ክፍል ዋና አሳብ እና በክፍሉ ስብከታችን ላይ የምንመልሰውን ጥያቄ እንደሚከተለው እናዘጋጅ።

- ዋና አሳብ- አማኞች የእግዚአብሔር በጎች መሆናቸውን ለማሳየት
- መመለስ ያለብን ጥያቄ- እንደ ጌታ በጎች ዛሬ ለአማኞች ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?

እነዚህን አሳቦች ከስብከታችን በፊት ካስቀመጥን በኋላ ዋና አሳባችንን የምናሸራሽርበትን የዋናው አሳብ ክፍሎችን በሶስት መክፈል ማስቀመጥ እንችላለን። እነርሱም፡-

I. እግዚአብሔር የበጎች እረኛ ነው- ቁጥር 1

1. እረኛችን ሁሉን ቻይ ነው - ቁ.1

2. እረኛችን በጅማላ ሳይሆን የየግል ጠባቂያችን ነው - ቁ.1

II. ለበጎቹ እረኛው የሚያደርገው - ቁ. 2-5

1. ዕረፍትን መስጠት- ቁ. 2

2. መምራት- ቁ. 3

3. ማጽናናት- ቁ. 4

4. ማርካት- ቁ.5

III. ለበጎቹ ያለው ተስፋ- ቁ. 6

1. በብርሃን የተሞላ ተስፋ አለው - ቁ. 6

2. የተባረከ ተስፋ አለው- ቁ. 6

ይህን ካልን በኋላ ወደ ዝርዝር የስብከት ክፍሎቻችን ገብተን ከምንለው ጋር የሚዛመዱልን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማጣቀስ መልዕክታችንን እናዳብራለን ማለት ነው።

በመጨረሻም ያልነውን ዝርዝር አሳብ እግዚአብሔር እረኛችን እንደሆነ እኛም የእርሱ በጎች እንደሆንን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብናልፍ እርሱ እንደሚረዳን በትላንት ሕይወታችን፣ በዛሬ ላይ እና በነጋችን ላይ ኃላፊ እንደሆነ ገልጸን ስብከታችንን በጸሎት እንዘጋለን ማለት ነው።

- **ናሙና ሁለት፡** ከላይ ለምሳሌ የተጠቀምንበትን ክፍል እንደናሙና እንውሰድና እንዴት ገላጭ ስብከት እንደሚዘጋጅ እና እንደምንሰበክ እንነጋገርበት።

የምንሰብከው ክፍል፡- ኤፌ.6፡10-18

ለዚህ ክፍል የምንሰጠው ርዕስ፡ መንፈሳዊ ውጊያ

መግቢያ ላይ ልንናገረው የሚገባ ነገር፡

- ✓ የምትሰብከው ክፍል ምን እንደሆነ
- ✓ ማን የጻፈው መልዕክት እንደሆነ
- ✓ ለስብከትህ የሰጠኸው ርዕስ
- ✓ ከዛ በኋላ አስፈላጊ መስሎ ከታየህ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከገጠሙህ ገጠመኞች አንዱን በመናገር በዚህ ስብከትህ ላይ የምታነሳቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ትናገራለህ ማለት ነው።

ከመግቢያ በመቀጠል የስብከትህ ዋና ዋና ክፍሎችን በሚከተለው መንገድ ለሰሚዎችህ ታስተዋውቃለህ

I. የክርስቲያኖች ወኔ ቁ.10-13

1. ከፍተኛ መሆን አለበት ቁ.10

2. ጽኑ መሆን አለበት ቁ.11-13

II. የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ጦር መሳሪያዎች ቁ.14-17

1. ለማጥቃት የሚጠቅሙ መሳሪያዎች ቁ.14-17ሀ

2. ለመከላከል የሚረዱ መሳሪያዎች ቁ.17ለ

III. የክርስቲያኖች የጸሎት ሕይወት ቁ.18

1. በትጋት የሚደረግ ጸሎት ቁ.18ሀ

2. በምልጃ ቁ.18ለ

ይህን ካደረክ በኋላ በእያንዳንዱ ርዕስ ላይ ከርዕሱ ሳትወጣ ማብራሪያ ትሰጣለህ። በዚህ ጊዜ የምትናገረውን ነገር ይበልጥ የሚገልጥልህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካለ አውዱን ሳይለቅ ባለው ትርጉሙ መሰረት እየጠቀስክ መልዕክትህን ታዳብራለህ ማለት ነው።

ቀጥሎ ወደመደምደሚያ ትመጣለህ። ይህን ማሳረጊያ በምታደርግበት ወቅት ፈጽሞ ከላይ ካልከው ውጪ አዲስ አሳብ አለመሰንዘርህን ልትጠነቀቅ ይገባል። ለምሳሌ እንዲህ ብለህ መደምደሚያ ልትሰጥ ትችላለህ። ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ትጉህና ጽኑ መሆን አለባቸው ይህንም ለማድረግ ጠላትን በመቃወም እና አሳቡን ወደ እነርሱ እንዳያስገባ በመከላከል ለራሳቸውና ለሌሎች ሊጸልዩ ይገባል ብለህ ማጠቃለያ አሳብ መስጠት ትችላለህ። ይህን ካደረክ በኋላ ክርስቲያን ወገኖች በምድር ላይ ሲኖሩ ከሚገጥማቸው

ፈተና ማለፍ እንዲችሉ እና ጠላታቸውን ዲያብሎስን መቃወም እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሁሉ በመለመን በጸሎት ታሳርጋለህ ማለት ነው።

✓ **የገላጭ ስብከት አዘገጃጀትና አሰባበክ መመሪያዎች**

1. ከስብከት ቀን በፊት

   1. አስቀድማችሁ ጸልዩ፤ ስብከት ማለት እንደው ይመስለናል እንጂ በሰው ብቃት ጨርሶ ሊከናወን የማይችል ነገር ነው። ምክኒያቱም

      - ሰዎች ስለ ሃጢአታቸው በስብከታችን ሊወቀሱ የሚችሉት እግዚአብሔር በስብከታችን ውስጥ ካለ ብቻ ነው።
      - ሰዎች ከአጋንንት እስራት እና ከጨለማው አገዛዝ ተመንጥቀው ነፃ መውጣት የሚችሉት እግዚአብሔር በስብከታችን ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው።
      - አማኞች በጌታ ተተክለው የሚቀሩት እና በስብከታችን ታንፀው ወደ ክርስቶስ ሙላት ልክ ለመሄድ ቅድስናን የሚላበሱት በስብከታችን እግዚአብሔር ሲኖር ብቻ ነው።
      - ስለዚህ ስንፀልይ መጀመሪያ ነገር እግዚአብሔር መልዕክት እንዲሰጠን፣ ቀጥሎ ለመልዕክቱ መግቢያ የሚሆን ነገር እንዲሰጠን፣ የምንናገረው ኃይል ያለውና በሰው ልቦና ውስጥ ገብቶ ትክክለኛ ስፍራውን የሚይይዝ እንዲሆን፣ ሰዎች ለስብከቱ በጎ ምላሽ እንዲሰጡ እና የሰበክነውን በተግባር እንድንኖረው እንጸልይ።

   2. የሰይጣን ክሶች ወደ ህይወታችሁ ሊመጡ እንደሚችሉ ገምቱ ደግሞም ከጸሎት ጋር ተቃወሙት

      - ብዙ ጊዜ ከየትኛውም አገልጋዮች በላይ ሰባኪዎች እና አስተማሪዎች የሰይጣን ክሶች የሚበዛባቸው አገልጋዮች ናቸው።

- ብዙ ጊዜ ሰይጣን "አንተ መስበክ አትችልም!"፣ "አንተ ግብዝ ነህ!"፣ "አንተ ያልኖርክበትን ለሌላው እንዴት ትሰብካለህ?" በማለት ክሶችን ሊደረድር ይችላል፡፡

- እንዲህ አይነት ነገር በሚገጥምበት ጊዜ በራሳችን ጽድቅ ከምንኩራራ ይልቅ በእግዚአብሔር ጸጋ መታመን ያስፈልገናል (2 ቆሮ 12፡9-10)፡፡

3. ሁሉንም አውራ የስብከት ነጥቦች በእግዚአብሔር ቃል እውነት እያጣቀሳችሁ እና እያስረገጣችሁ በመፃፍ ተዘጋጁ፡፡

    - ለእያንዳንዱ ለምትሉት ነገር ከየትኛው የቃሉ ክፍል (ቁጥር) እንዳገኛችሁ "ቁጥር 5 እንደሚለው" ወይም "ቁጥር 5ን ከእኔ ጋር ተመልከቱ" እያላችሁ አድማጮችሁ ከቃሉ እንዲያመሳክር አድርጉ፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻላችሁ ከገዛ ስልጣናችሁ እየሰበካችሁ ነው ማለት ነው

    - ገላጭ ስብከት በባህሪው አንድ የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ወይም ምንባብ ላይ ተመስርቶ የሚሰበክ እንደመሆኑ ፈጽሞ እዚህም እዚያም እየጠቀሳችሁ አያሌ ክፍሎችን በስብከታችሁ ውስጥ አትጠቀሙ፡፡ ከዋናው የመልዕክቱ ክፍል ውጪ ሌሎችን ክፍሎች ደጋግሞ መጠቀም ገላጭ ስብከት ሳይሆን ርዕሳዊ ስብከት ሊሆን ይችላል፡፡ በጣም አስፈላጊ ከሆነ አንድ ወይም እጅግ ትንሽ ክፍሎችን በራሳችሁ ጥቅል ሃሳብ ከዋናው የገላጭ ስብከት ክፍላችሁ ጋር አያይዛችሁ ለማስረዳት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን እዚህም እዚያም በምትጠቅሷቸው ጥቅሶች አድማጮቻችሁ አንዱን ሳይጨብጡ ወይም እንደተበታተነባቸው አሊያም ግራ ተጋብተው እንዲሄዱ ታደርጋላችሁ፡፡

    - በገላጭ ስብከታችሁ ውስጥ ፈጽሞ "ያንን ክፍል አሁን ማንበብ የለብንም" አትበሉ፡፡ ይህንን ማለታችሁ አድማጮቻችሁ የማያስፈልግ መጠርጠር ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይልቅ አስፈላጊ መስሎ የተሰማችሁን ክፍል የት እንደሚገኝ በደፈናው አሳውቃችሁ ጠቅለል ያለ ሃሳባችሁን በራሳችሁ ቋንቋ ግለፁላቸው፡፡

- በገላጭ ስብከታችሁ ውስጥ "ሙቀቱም" (ያልቀዘቀዘና በቂ የሆነ የተግባራዊ ህይወት ተዛምዶ ይኑረው) እንዲሁም ደግሞ "ብርሃንም" (በቂ የሆነ ትርጉም እና ማብራሪያ ይኑረው)። ከእነዚህ ሁለቱ የትኛውን እንዳላሟላችሁ መለስ ብላችሁ በመመርመር ለማሻሻል ሞክሩ።

- ዘና የሚያደርጉ ቁም ነገር አስጨባጭ ምሳሌዎችን በየመሃከሉ በመጠቀም የስብከታችሁን ተሰሚነት የበለጠ ተፈላጊ አድርጉት፤ ኢየሱስም ብዙ ጊዜ እንደዚሁ አድርጓል (ማቴ 7፡3-5፣ ሉቃ 15…)።

4. መላውን የስብከታችሁን መልዕክት በአስተዋፅዖ መልክ ቀደም ብላችሁ ጻፉት

- ይህ የስብከታችሁን ቅደም ተከተል ለይቶ ለማወቅና ለመከታተል ይረዳችኋል።

- ይህም ብቻ ሳይሆን የስብከታችሁን የሃሳብ ተፋሰስ ጠብቃችሁ ያልተዘበራረቀ ነገር ለማቅረብ ይረዳችኋል።

- አስተዋፅዖ ማዘጋጀት በስድ ንባብ መልክ ከተዘጋጀ ስብከት ይልቅ እየሰበክን ያለንበትን ቦታ ለይተን እንድናውቅ ይረዳናል።

- ከአስተዋፅዖቻችን ጋር እያንዳንዱ ነጥቦቻችን ምን፣ ምን ያክል የሚብራራበት ደቂቃ እንደሚኖረው እናቅድ፤ ይህ ደግሞ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ብዙውን ደቂቃ እንዳንወስድ ይረዳናል።

5. ለብቻችሁ እና ከሌሎች ልምድ ካላቸው ጋር ስብከቱን ተለማመዱ

- ከዋናው የስብከት ቀን በፊት ስብከትን ለራስ ወይም ለቅርብ ሰው እየሰበኩ መለማመድ ነውርም ሐጢአትም አይደለም።

- አዳዲስ አስተማሪዎች እና ሰባኪዎች ያዘጋጁትን ስብከት ወይም ትምህርት ብዙ ልምድ ላላቸው ሰዎች ሰጥተው ማሳየት እና ማስገምገም ቢችሉ የበለጠ መልካም ነው።

2. <u>በስብከት ወቅት</u>

1. ከአድማጮቻችሁ ጋር ቀጥተኛ የአይን ግንኙነት ይኑራችሁ፡፡ ፈጽሞ ጣራ ጣራውን አሊያም አንድ ቦታ ብቻ እያያችሁ አትስበኩ፡፡ በአይናችሁ ዝውውሮች ውስጥ ምላሽ ሰጪ አድማጫችሁን አግኙ፡፡ ነገር ግን ሌሎች ያልተፈለጉ መስሎ እንዳይሰማቸው አብዝታችሁ በዛ ሰው ላይ ብቻ ትኩረት አታድርጉ፡፡

2. ድምጻችሁን በአግባቡ እንደየሁኔታው ለዋውጡ፡፡ ድምፃችሁ ጀምራችሁ እስክትጨርሱ ድረስ ፈፅሞ አንድ አይነት አይሁን፡፡ እጅግ በጣም አነስተኛ በሆነ ድምፅ አትናገሩ፡፡ እንዲሁም ደግሞ እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነ ድምፅም አትናገሩ፡፡ ሁለቱም (ማለትም የድምፅ ማነሱም ሆነ መብዛቱ) እጅግ በጣም ምቾት የሚነሳቸው አድማጮች በጉባዔው ውስጥ እንደሚኖሩ አትርሱ፡፡ የተመጣጠነ ድምፅ ሆኖ እንደየ ስብከቱ መልዕክት ስሜት መለዋወጥ ጥሩ ነው፡፡

3. የተመጣጠነ የሰውነት እንቅስቃሴ ያለበት ስብከት ይኑራችሁ፡፡ ፈፅሞ አንድ አይነት የእጅ አወራጫጨት ተጀምሮ እስኪያልቅ አታድርጉ፡፡ ወይም ፈፅሞ አንድ ቦታ ብቻ ሳትንቀሳቀሱ ቆማችሁ አትስበኩ፡፡ የምትሰብኩ ሳይሆን ድራማ የምትሰሩ እስኪመስል ድረስ እጅግ በጣም የተጋነነ የሰውነት እንቅስቃሴም አታድርጉ፡፡

4. በስብከታችሁ ላይ መታየት ያለባቸው ስሜቶቻችሁን አትሸሽጉ፡፡ የሚታዩት ስሜቶቻችሁ እውነተኛ እንጂ የማስመሰል አይሁኑ፡፡ ማበረታታት ባለባችሁ ሰዓት አትገስጹ፡፡ መሳቅ በሚኖርባችሁ ጊዜ አታልቅሱ…

5. አለባበሳችሁ ፈፅሞ የተጋነነ ወጪ የወጣበት ወይም በጣም ያሸበረቀ ወይም በጣም ደግሞ ደረጃውን ያልጠበቀ አይሁን፡፡ ሁለቱም አድማጮቻችንን ሊያሳጣን ይችላል፡፡

6. በስብከታችሁ ጅማሬ ወይም መሃከል ላይም ሆነ በስተመጨረሻ ምንም አይነት ሰበቦችን አትደርድሩ፡፡ ለምሳሌ “በበቂ ሁኔታ አልተዘጋጀሁም፤ ነገር ግን የምችለውን አደርጋለሁ…”፣ “እንድሰብክ የተነገረኝ በቅርብ ስለሆነ ጥሩ ላልሰብካችሁ እችላለሁ…”፣ “በጣም ታምሜ(ያለሁ) ነበር ግን እንደምንም…” እና የመሳሰሉትን መናገር የለብንም፡፡ አድማጭ የምንሰብከውን ትቶ በሰበባችን ላይ ሲያወጣና ሲያወርድ መልዕክቱን ሳይሰማ ይቀራል፡፡

7. ስለራሳችንም ጥሩ ያልሆኑ ማጣጣሎችንም አንናገር፡፡ ለምሳሌ “በዚህ ጉዳይ ላይ ጥሩ ተናጋሪ አይደለሁም”፣ “እኔ ጥሩ ሰባኪ ባልሆንም … ”፣ “ጥሩ አድርጌ በምሳሌ ማስረዳት ባልችልም…” ወዘተ፡፡ እናንተ ስለ ራሳችሁ እና ስለ ምትሰብኩት ነገር በቂ በራስ መተማመን ሊኖራችሁ የሚገባ የእግዚአብሔር ቃል አቀባዮች መሆናችሁን አጥብቃችሁ ልታምኑበት ይገባል፡፡

8. በስበከታችሁ ውስጥ “እናንተ” ከማለት ይልቅ “እኛ” የሚለውን በመጠቀም ስብከቱ የሁላችንም እንደሆነ እንጠቁም፡፡ ደጋግሞ “እናንተ” እያሉ አድማጭን መስበክ ራስን እንደማጽደቅ ሊቆጠርብን አሊያም ሌላ ጥሩ ያልሆነ ትርጉም ሊያሰጥብን ይችላል፡፡

9. በስብከታችን ላይ ስንሆን በጌታ ያልሆኑ ነገር ግን አዳዲስ አማኞች መሆን ፈልገው የመጡ ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት ጭራሽ የሚያሰናክላቸውን የሌሎችን እምነቶች ጥላቻ፣ አላስፈላጊ ትምክህቶችን፣ ስጋዊ የሆኑ ድርጊቶችን/ንግግሮችን በማሳየት ይልቁንም እንዳናርቃቸው እንጠንቀቅ፡፡

10. ሊሳለቁብን እና ሊገመግሙን ወይም በሌላ ዓላማ የሚመጡ ፅንፈኞችም ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት በጥንቃቄ፣ በብዙ ትህትና እና በጨዋነት እናገልግል፡፡

11. ጉባዔው ትርጉማቸውን ላያውቃቸው የሚችሉትን የተለያዩ የግሪክኛ፣ የዕብራይስጥኛ፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ቃላትን በጭራሽ አትጠቀሙ፡፡

12. ጉባዔው የማይረዳቸውን የነገረ-መለኮት ሙያዊ (technical) ቃላቶችን (jargon) ፈጽሞ አትጠቀሙ፡፡

13. “ይህንን እንደምታውቁት እርግጠኛ ስለሆንኩ አላነሳውም” አትበሉ፡፡ የትኛውንም ነጥብ ለማብራራት ምሳሌ ካላችሁ ቀጥታ ምሳሌያችሁን ተናገሩ እንጂ “ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው … ነው አትበሉ”፡፡

14. በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ከዋናው የመልዕክታችሁ ክፍል ውጪ ፈፅሞ ወደ ሌሎች በመሄድ እዚህም እዚያም እየጠቀሳችሁ አታስተምሩ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጉባዔው ምናልባትም አንዱንም ሳይጨብጥልን ሊበተን ይችላል፡፡ አሊያም ስብከታችንን የሚያስታውሰው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ይሆንና ወዲያው ይረሳዋል፡፡

3. <u>ከስብከት በኋላ</u>

1. ጌታን ሊቀበሉ የሚሹ እንዳሉ፣ ወይም ከጌታ ቤት የጠፉ እምነታቸውን ግን ማደስ የሚፈልጉ እንዳሉ ትሁት ጥያቄ በጉባዔው መካከል አቅርቡ፡፡

2. ስለ ትምህርቱ የበለጠ መስማት የሚሹ ወይም ያልገባቸውንና ጥያቄ የፈጠረባቸው እንዳሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ እንጂ የሽሽት መሽሎክሎክ አይታይባችሁ፡፡ መመለስ የማትችሉት ጥያቄ እንኳን ቢነሳ በቂ ጊዜ ወስዳችሁ ድጋሚ ልታነሱት እንደምትችሉ በመንገር ቀጠሮ ወይም ስልክ ተለዋወጡ፡፡ ነገር ግን ቃላችሁን በማጠፍ መልካም ምሳሌነታችሁን እንዳታጡ ተጠንቀቁ፡፡

3. ስብከታችሁ በድምጽ ካሴትም ሆነ በምስል ካሴት ተቀርፆ እንደሆነ ጊዜ ወስዳችሁ የራሳችሁን ስብከት በመመልከት ብርቱ ጎናችሁ የትኛው፣ ደካማ ጎናችሁ ደግሞ የትኛው እንደነበረ ራሳችሁን እየገመገማችሁ ለሌላ ጊዜ ለማሻሻል ነጥቦችን አውጡ፡፡

4. በመስበክ እና በማስተማር የብዙ ጊዜ ልምድ ያላቸው አገልጋዮች ስብከታችን ምን ይመስል እንደነበረ በመጠየቅ ገንቢ አስተያየቶቻቸውን በቅንነትና በአክብሮት እንቀበል፡፡

5. ከስብከታችን ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ማበረታቻዎችም ሆነ ወቀሳዎች/ማሻሻያ ሃሳቦች በጥንቃቄ ተቀብለን ክብር ለሚገባው ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ራሳችንን እንደማይጠቅም ነገር ግን ማድረግ ያለበትን ብቻ ለማድረግ እንደሞከረ ባሪያ አድርገን እንቁጠር፡፡ የተነገሩንንም ማሻሻያ ሃሳቦች አሻሽሎ በተግባር ለማዋል እንትጋ፡፡

6. ስንሰብከው የነበረውን በተግባር ኖረነው እንድንገኝ መልሰን እንፀልይ ራሳችንንም እናስለምድ፡፡

2.1 አንድ ክፍል ላይ የተመሰረተ ስብከት (Textual Sermons)

በአንድ ክፍል ላይ ተመርኩዞ የሚሰበክ ስብከት ማለት በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ (ክፍል) ላይ ተመስርቶ ክፍሉን በተሌየ መንገድ ከፋፍሎ መስብክ ማለት ነው። ቀጥለን የተወሰኑ በአንድ ክፍል ላይ የተመርኩዞ የስብከት ናሙናዎችን እንመልከት።

የእግዚአብሔር ሃይል ደካሞችን ያግዛል! ኢ.ሳ. 40:28-31

I. እግዚአብሔር ምን አይነት አምላክ ነው! -- 40:28

1. ተስፋ የማይቆርጥ!

2.የማይደክም የማይታክት!

3. ማስተዋሉም አይመረመርም!

II. እግዚአብሔር ምን ምን ነገሮችን ያደርጋል! -- 40:29,30

1. ለደካሞች ሃይልን ይሰጣል!

2. ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል!

III. እግዚአብሔር ሊደርግልን የሚፈልጋቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው! -- 40:31

1. ከችግራችን በላይ መኖር የምንችልበትን ጉሉብት ይሰጠናል! (እንደ ንስር እንደሚል)

2. በጉዛችን እንዳንጨናገፍ ያግዘናል!

3. ከድካም ያወጣናል ያበረታናልም!

በአንድ ክፍል ላይ ተመርኩዞ የሚሰበክ ስብከት ለማዘጋጀት የሚረዱ መርሆች

1. የምንሰብከው ክፍል አከፋፈል በመሀከላዊ የክፍሉ አሳብ/ መልዕክት ላይ ማጠንጠን አለበት

ለምሳሌ ሮሜ 12፡1፣2 መስበክ የሚፈልግ ሰው ለክፍሉ ሰውነታችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ የሚል ርዕስ ሰጥቶ በሚከተለው መንገድ መከፋፈል ይችላል

I. ለምን መስዋዕት ማቅረብ አስፈለገ?

II. መስዋዕት አድርገን የምናቀርበው ምንድን ነው?

III. የመስዋዕቱ አቀራረብ

IV. የመሰዋቱ ግዴታ.

2. አከፋፈላችን ክፍሉ የሚያሳየንን የመልዕክት አሳብ መግለጥ የሚችል መሆን አለበት (መዝ.32 ወይንም 51 በማየት ይህን መረዳት ይችላሉ)

3. አንዳንድ ጊዜ ከአንድ በላይ አሳብ የሚያስተላልፉ ክፍሎችን ከመረጠን በየአሳቡ ላይ የተለያዩ አከፋፈሎች በመከፋፈል እያንዳንዱን አሳብ ማብራራት ይችላሉ (ዩ.ሐ.3:16 ይመልከቱ)

4. ዋና ዋና ክፍፍሎቹ ተኣማኒነት ያላቸውና ቅድም ተከተልን የጠበቁ መሆን አለባቸው

5. አንዳንድ ክፍሎች ሁለት ነገሮችን ሊያነጻጽሩ ይችላሉ ያን ጊዜ ያንን ክፍል በሁለት ንጽጽር መካከል አድርገን ልንከፋፈል ይገባናል (ለምሳሌ ማቴ.7 እና መዝ.1 ይመልከቱ)
6. አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይንም ሶስት ጥቅሶች ከተለያየ ቦታ መጥተው ተመሳሳይ አሳብ የሚያስተላልፉ ከሆነ አንድ ላይ አድርገናቸው የስብከት ክፍፍላችንን ልንሰራ እንችላለን።

ትርጉሙ

- በአንድ ነጠላ ጥቅስ ላይ ብቻ የሚደረግ የስብከት አይነት ነው
- በአንድ አሳብ ላይ ብቻ ሚያጠነጥን የስብከት አይነት ነው
- በአብዛኛው ጊዜ ብዙ ጥቅሶችን የማያጣቅስ የስብከት አይነት ነው

ጥቅሙ

- ሰባኪ በአንድ ነጠላ አሳብ ላይ ብዙ መናገር እንዲችል ማድረጉ
- ሰሚውን ለማሳሰብ፣ ለማደፋፈርና ለማስጠንቀቅ ይጠቅማል
- ለዝግጅት በጣም ቀላል መሆኑ(በተለይ ሰባኪው የመናገር ችሎታ ካለው)

ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች

- ለሚያስተምሩ ሰዎች ብዙም የሚጠቅም አለመሆኑ
- ርዕሰ ጉዳዩን እንደሚገባ የማብራራት አቅም አይኖረውም
- መጽሐፍ ቅዱስ ሊለው የሚፈልገውን ሳይሆን ሰባኪው ሊለው የሚፈልገውን ማለት እንዲችል ነጻነት መስጠቱ
- ጠለቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አለመፍጠሩ እና መሰረተ ቢስ ስለሚያደርግ
- በአጥጋቢ ሁኔታ የእግዚአብሔርን መንጋ እንድንመግብ አለማድረጉ

2.3 ርዕሳዊ ስብከት (Topical Sermons)

ርዕሳዊ ስብከት ማለት ከሚነበበው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውጪ በሆነ መልኩ በሰባኪው በተያዘው ርዕስ ላይ በተመረኮዘ የርዕሱ ክፍፍል የሚደረግ የሰብከት አይነት ነው። ይህ ማለት ደግሞ፡-

ሀ. ርዕሳዊ ስብከት የሚጀምረው በርዕስ ሲሆን የግድ ጥቅስን መሰረት ያላደረገ አይነት ስብከት ማለት ነው።

ለ. ዋና ዋና የስብከት ክፍፍሎቹ የሚወሰኑት ከሚነበበው የእግዚአብሔር ቃል አንጻር ሳይሆን ከተያዘው ርዕስ አንጻር ነው ማለት ነው።

ሐ. ይህ ርዕሳዊ ስብከት የሚይዘው ርዕስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን ሲሆን ምናልባት ርዕስ የማይወጣቸው ጥቅሶችን የግድ ርዕስ እንሰጣቸዋለን ማለት ግን አይደለም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ርዕሶች መካከል ለምሳሌ አንዱን እንመልከትና እንዴት ርዕሳዊ ስብከት እንደምናዘጋጅ እንመልከት።

ርዕስ፡ የሰይጣን ጥቃት በቤተሰብ ላይ

አላማ፡ የተለያዩ የጠላት ጥቃቶችን ሕዝቡ እንዲረዳ ለመርዳት ዋና ጥቅስ፡ ኤፌ.6፡10-18

ለዚህ ርዕስ የሚከተሉትን አራት ዋና ዋና አሳቦች መናገር ይቻላል፡

ሀ. የሰይጣን ጥቃት ግብ ማጥፋት ነው (1ጴጥ.5፡8-9)

ለ. የሰይጣን ጥቃት መሻቱ አማኞችን እንደስንዴ ማበጠር ነው (ሉቃ.22፡31-32)

ሐ. ጥቃቱን የሚያደርስበት ስልት አለቆችንና ስልጣናትን በማደራጀት ነው (2ቆሮ.10፡3-5)

መ. የጥቃቱ አላማ ሰዎች የሓጢያት እስረኛ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ ነው (2ጢሞ.2፡24-26)

በርዕሳዊ ስብከት ላይ የአሳብ አንድነትና ፍሰትን ለመጠበቅ ርዕሱን የሚያንጸባርቅ አንድ ግብ እና ያንን ግብ ለመድረስ ተያያዥነት ያላቸውን ርዕሱን የሚያብራሩ ክፍፍሎች ልናዘጋጅለት ይገባናል ማለት ነው።

የአማኞች ተስፋ

ርዕስ: የአማኞች ተስፋ ባህሪያት!

I. ህያው ተስፋ ነው, 1ጴጥ.1፡3

II. የሚያድን ተስፋ ነው, 1ተሰ. 5:8

III. ጽኑ ተስፋ ነው, ዕብ. 6:19

IV. መልካም ተስፋ ነው, 2ተሰ. 2:16

V. የማይታይ ተስፋ ነው, ሮሜ. 8:24

VI. የተባረከ ተስፋ ነው, ቲቶ 2:13

VII. ዘላለማዊ ተስፋ ነው, ቲቶ. 3:7

ትርጉሙ

- ርዕስ መርጦ ገለጻ የሚያደርግ የስብከት አይነት ነው
- ዶክትሪን፣ ግለሰብ፣ ቦታ ወይንም አንዳንድ ነገሮች ላይ አጽንኦት
- ሰጥቶ የሚያብራራ የስብከት አይነት ነው
- ብዙ ክፍሎችን የሚያጣቅስ የስብከት አይነት ነው

ጥቅሙ

- ርዕሱን እንደሚገባ ለመዳሰስ የሚረዳ ነው።
- በአንድ ውስን ርዕስ ላይ ያለውን ጠቅላላ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮ እና የእግዚአብሔርን አሳብ መረዳት ያስችለናል።

ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች

- ሰባኪው በቀላሉ ሊያስተው በሚችል መልኩ ቃሉን በትክክል እንዳይፈታው ያደርገዋል
- ሰባኪው የሚመቸውን ርዕሰ ጉዳይ ብቻ አጽንኦት እንዲሰጠው እና የእግዚአብሔርን የጊዜውን አሳብ ለማወቅ በጸሎት እንዲያሳልፍ ሊያዳክመው ይችላል
- በሚያነሳቸው ጥቅሶች ላይ ያሉትን ድብቅ ጉዳዮች ሳያስተውል ለርዕሱ እንዲጠቀምበት ሊያደርገው ይችላል

2.4 ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት (Biographical Sermon)

ግለ-ታሪክ ማለት የአንድ ግለሰብን ታሪክ የሚያመላክት ሲሆን ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ የስብከት አይነት አንዱ ነው ብለን በዚህ የስብከት ዘዴ ትምህርት ላይ ስናቀርበው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ታሪክ ማዕከል ባደረገ ሁኔታ አሁን ላሉ ክርስቲያኖች

የምንሰብክበት መንገድ እንደሆነ ለመረዳዳት ነው። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለዳዊት ሕይወት እና ኑሮ በስፋት ይናገራል ይህን የዳዊት ታሪክ ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንስተን ለስብከት ስናዘጋጅ ይህ ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት እንለዋለን ማለት ነው። እስቲ ከዚህ በመቀጠል አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር እንመልከት።

ትርጉሙ

አስቀድመን በመግቢያችን ላይ ለማለት እንደሞከርነው ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸውን የምንመለከታቸውን የሰዎችን ታሪክ ማለትም የህይወት ታሪካቸውን በመተረክ ከእነርሱ የሕይወት ታሪክ አሁን ያለነው ሰዎች ምን መማር እንዳለብን የምንሰብክበት የስብከት አይነት ነው። ለምሳሌ የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ፣ የአብርሃም ታሪክ፣ የሙሴ ታሪክ፣ የዳዊት ታሪክ…ወዘተ እያልን በሕይወት ታሪካቸው ዙሪያ ራሳችንን አዘጋጅተን የምናገለግልበት የስብከት አይነት ነው።

ጥቅሙ

ይህ አይነት ስብከት ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካቸው ከተጻፈላቸው ግለሰቦችና ከተሞች ጠንካራና ደካማ ጎን መማር የሚችሉበትን አጋጣሚ የሚፈጥር መንገድ ነው። በጥቅሉ ይህ አይነት ስብከት የሚከተሉትን ጥቅሞች ለሰባኪውና ለሰሚው ይፈጥራል። እነዚህም፣

- ሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀቱን ያሰፋለታል ምክንያቱም የአንድን ሰው ታሪክ አውጥቶ ለማጥናት የተለያዩ የመጽ ሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማጥናት ስለሚኖርበት ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀቱን ያሰፋለታል
- ሰባኪው ስብከቱን በሚያዘጋጅበት ወቅት ከሚያጠናው ደካማና ጠንካራ የግለሰቦች ሕይወት አሁን ላለቸው ቤተክርስቲያን ጥንካሬ የሚበጁ መንገዶችን ለማሳየት ከፍተኛ ዕድል ይፈጥርለታል።
- ግለ-ታሪክ ስብከት የሰውን ልክ/አቅም እንድናውቅ እና ራሳችንን መቀበል እንድንችል መንፈሳዊ ጥንካሬና በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን ይፈጥርልናል።

ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች

መቼም ማንኛውም አይነት መንገድ የራሱ የሆነ በጎ ጉን እንዳለው ሁሉ የራሱ የሆነ ደግሞ ደካማ ጉን ይኖረዋል ሰባኪም ይህን ተረድቶ አጠቃቀሙን ሚዛናዊ ማድረግ አለበት። ግለ-

ታሪክን በምንሰብክበት ወቅት እና በምናዘጋጅበት ወቅት ሊኖሩ የሚችሉ ነገሮችን ለመመልከት እንዲህ አይነት ስብከት ማዘጋጀትና ማቅረብ ጉዳቱ ምን ሊሆን ይችላል የምንለውን ደግሞ እስቲ ቀጥለን እንመልከት።

- አንዳንድ ጊዜ ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት በምንሰብክበት ወቅት የእግዚአብሔርን ከሁሉ በላይነት ሰዎች እንዲዘነጉና ታሪኩን በሚሰሙት ሰው የሕይወት ታሪክ ልክ ለዛ ሰው የተለየ ቦታ በልባቸው እንዲሰጡት ሊያደርጋቸው ይችላል

- አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከግለ-ታሪክ በሚያዩት ደካማ ጉን ከመማር ይልቅ ለራሳቸው ድካም ምክንያት የሚያደርጉበት ዕድል ሊፈጥርላቸው መቻሉ

- አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳችን በተረካቸው የግለሰብ ታሪኮች በስተጀርባ ያለውን የታሪክ ባለቤት እግዚአብሔርንና እርሱ ሊያስተምረን የፈለገውን ሳይሆን በግለሰቦች ታሪክ ጊዜያችንን ሰውተን ከዋናው መልዕክት እንድናፈነግጥ ማድረጉ በተወሰነ ደረጃ ደካማ ጉኑ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው።

2.5 ምሳሌያዊ ስብከት (Allegorical Sermon)

ምናልባት በዚህ ዘመን ከምንሰማቸው አብዛኛው ስብከቶች ይህን እንደሚመስሉ ወይንም ከዚህ እንደሚመደቡ ማሰብ አዳጋች የሚሆንብን አይመስለንም ምክንያቱም ይህን በየመድረኮቻችን፣ በመገናኛ ዘዴዎች በሀገር ውስጥ እንዲሁም በውጭ የምናስተውለው ነውና። እስቲ ጥቂት እንበል ስዚህኛው አይነት ስብከት።

ትርጉሙ

በመጀመሪያ ምሳሌያዊ ስብከት ምን ማለት ነው ብለን ራሳችንን እንጠይቅ። ምሳሌ አንድን ነገር ለማብራራት ወይንም ለመግለጽ በቅጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ የምንናገረውን የሚተካልንን ንግግር ወይንም መግለጫ ምሳሌ እንላለን። ምሳሌያዊ ስብከት ስንል ደግሞ የምንናገረውን ወይንም ለመናገር የፈለግነውን እንዲናገርልን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን እንደ ምሳሌ አድርገን የምንጠቀምበት መንገድ ማለት ነው። ይህ አይነቱ ስብከት እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን እንግዳና ዘመን አመጣሽ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

ጥቅሙ

- በሰዎች ልብ ለረዥም ጊዜ መቀመጥ መቻሉ ምክንያቱም ምሳሌያዊ ባህሪ ስላለው በቀላሉ የሰዎችን ልብ ሊቆጣጠር ይችላል
- መልክታችንን አዝናኝ እና አስደሳች የማድረግ አቅም ስላለው ጠቃሚ መንገድ ነው
- ሰባኪው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ከተለያዩ ጥቅሶች ላይ በማጣቀስ እንዲያቀርብ ያስችለዋል

ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮች

- ጥቅሶችን ያለቦታቸው በማስገባት የሚሉትን ሳይሆን ልንል የፈለግነውን እንድንል ልናስገድዳቸው መቻላችን
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መልዕክታቸውን እንዲለቁ እና ሰዎች የስህተት አስተምህሮችን እንዲያዳብሩ ማድረጋቸው
- መጽሐፍ ቅዱስ ፊት ለፊት ካለው መልዕክት ይልቅ ሌላ ድብቅ መልዕክት ያለው መጽሐፍ አድርገው ሰዎች እንዲያስቡ እና ሌላ ሚስጥር ፍለጋ ብቻ ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ጋር ሰዎች እንዲታገሉ ማድረጋቸው ከብዙ በጥቂቱ ይህን አይነት ስብከት ደካማ ጉን አለው ለማለት እንችላለን።

ምዕራፍ ሦስት፡ የተሳካለትና ውጤታማ ሰባኪ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቁልፍ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

አስቀድመን በትምህርቱ መግቢያ ላይ እንደተነጋገርነው አንዳንድ ሰዎች ስብከታቸው የማይጠገብ ሆኖ መቼ ጀምረው እንደጨረሱ ሳይታወቅ የሚሰብኩ እንዳሉ ሁሉ ከመቼ መቼ ያልቃል ተብሎ ደግሞ ስብከታቸው አሰልቺና አታካች የሆኑ ብዙዎች ናቸው። ታዲያ ስብከታችን አስልቺ እንዳይሆንና ተደማጭነት ያለው የሰውን ሕይወት የሚለውጥ እንዲሆን ምን ማድረግ አለብን የሚለውን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን። ሰባኪ በስብከቱ የተሳካለትና በሰው ሕይወት ላይ ተጽእኖ የሚያመጣ እንዲሆን በሕይወቱ ላይ፣ በመልዕክቱ ላይ፣ እና

መልዕክቱን ከየት እንደሚቀበል ሊያስብበት ይገባል። እነዚህ ሶስት መሰረታዊ እውነቶች እስቲ በተናጠል እንመልከታቸው።

3.1 የሰባኪ ሕይወት

የስብከት መሰረታዊ ነገሮች ከጎደሉት እጅግ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀና የተሰበከ መልዕክትም ቢሆን እንኳን ባዶ ጩኸት ይሆናል። የስብከት አዘገጃጀት ዘዴዎችንና መሰረታዊ ነገሮችን የሚያገናኛቸው ቁልፍ ነገር የሰባኪው መንፈሳዊ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል በማመን እያደገ የሚሄድ መሰረታዊ ግንኙነትን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መቀጠል ያለበት ነው የሚሆነው። ሰባኪ ከስብከቱ ባሻገር ስለራሱ ሕይወት ማሰብ መጨነቅና መጠንቀቅ አለበት ምክንያቱም በሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥን ለማወጅ እስከተጠራ ድረስ ያልተለወጠ ለዋጭ መሆን ስለማይቻል ከሕይወቱ ለውጥ መጀመር አለበት።

3.2 የሰባኪ መልዕክት

አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ያሉ ተማሪዎች ስብከትን እንዴት እንደሚያዘጋጁ ይማራሉ ይለማመዳሉም ነገር ግን አብዛኛው ሰባኪ (እኔንም ጨምሮ) በቤተክርስቲያን በሚያደርጉት ስብከት ላይ ፈጽሞ ከመርህ ውጪ ይሰብካሉ። ስለዚህ በምታማሩት መልክ ለመስበክ ቢያንስ በቀን ሶስት ስብከት የሆምሌቲክስ ዕግን ተከትላችሁ ማዘጋጀት መለማመድ ይኖርባችኋል።

3.2.1 ስብከትን እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል?

1. ስብከት ሶስት ክፍሎች እንዳሉት አውቆ በሶስቱም ክፍል ላይ ያለውን አሳብ ለማጠናከር በቂ ጊዜ መመደብ

መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ የስብከት ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው። መግቢያ ምን መያዝ አለበት፣ ሀተታስ፣ መደምደሚያስ?

2. ስብከት የራሱ የሆነ ይዘት ስላለው ይህን አውቆ የምትሰብከውን ክፍል አጥንቶ አስፈላጊውን የስብከት ይዘት/ቅርጽ እንዲኖረው ማድረግ

የስብከት ቅርጽ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይንም ሁለቱንም አይነት የሚይዝ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ይህን ወስኖ ስብከትን ቅርጽ ማስያዝ

3. ስብከት outline ሊኖረው ስለሚገባ አስቀድሞ ማዘጋጀት

በይዘቱ መሰረት outline ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

3.3 የመልዕክቱ ባለቤት (መንፈስ ቅዱስ)

መልዕክት ከማን ይመጣል? ካነበብነው? ሌሎች ሲሰብኩ ከሰማነው? ከኢንተርኔት መርብ ካገኘነው? ከቪዲዮ ካየነው? ወይንስ ከቃሉ ባለቤት ከተማርነውና ሕይወታችንን ከለወጠው ቃል? ይህ ሊታሰብበት ይገባል አለበለዚያ መረጃ ከሚያቀርብ ጋዜጠኛ የተለየን አንሆንም። ሉዊስ ስፔሬይ ቼውፈር የተባሉ የስነ-መለኮት ሰው ግልጥና ጥልቅ በሆነ አገላለጥ እንዲህ ብለዋል፡- "ክርስቲያን ክርስቲያን የሆነው ከክርስቶስ ጋር ካለው ትክክለኛ ግንኙነት የተነሳ ነው። መንፈሳዊ ሰው ግን መንፈሳዊ የሚሆነው ክክርስቶስ ጋር ካለው የድነት ግንኙነት በተጨማሪ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖረው ትክክለኛ ግንኙነት ነው።" መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ለክርስቲያኖች የተሰጡ አራት የአዲስ ኪዳን ትዕዛዛት አሉ። በመጀመሪያ በዋናነት የሚመለከቱት ግን ሰባኪውን ነው።

1. *ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር እራስዎን ያስገዙ። ኤፌሶን* 5፡18 *ውስጥ የተጠቀሰው ትዕዛዝ በመለኮታዊውና በሰብአዊው በኩል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ሚዛናዊ*

ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስን የማያቋርጥ ቁጥጥር መፍቀድ ሰባኪው ሃላፊነት ነው። ጀልባ ቀዛፊ ጀልባውን ይገፋለት ዘንድ ከንፋስ አቅጣጫ ጋር እንደሚያስተካከል (ዮሐ.3፡6-8 ውስጥ መንፈስና ነፋስን አስመልክቶ የተገለጠውን ምሳሌ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ) እኛም እራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር እናስረክባለን። ወደ ሕይወታችን እንጋብዘዋልን ራሳችንን ለቁጥጥሩ እናስገዛለን በየዕለቱ ያለማቋረጥ እና በፍላጎት።

2. መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነውን ነገር ሁሉ ከሕይወትዎ ያስወግዱ (ኤፌ.4፡30)። “የእግዚአብሔር መንፈስ” ሚለው ሙሉ ርዕስ ትዕዛዙን መንፈስ ቅዱስን አለማሳዘን ከሚለው አሳብ ጋር ያዋህደዋል። ሰባኪው መንፈስ ቅዱስ ጥሩ መጥረጊያ ይዞ ብሩህ ብርሃኑን በሕይወቱ ስርቻ ላይ እንዲያበራ በመጋበዝ የራሱን ጉድፍና ቆሻሻ ይመለከታል። በዚህ ሁኔታ የተመሰቃቀለ ሕይወቱን ይመለከትና ከእግዚአብሔር የሃጢያት ይቅርታን ከማግኘት ባሻገር ቅድስና ከጎደለው ነገር ሁሉ ለመንጣት ንስሃ ይገባል(1ዮሐ.1፡9)

3. ለመንፈሳዊነት ጥንካሬዎ ድጋፍ የመንፈስ ቅዱስ ሃይልን ያነሳሱ። “መንፈስን አታጥፉ” 1ተሰ.5፡19ን ያንብቡ። ግለሰብን የሚመለከትና ለሁሉም የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። እግዚአብሔር የእርሶን መንፈሳዊ ዕድገት እርስዎ ከሚፈልጉት በላይ ይፈልገዋል። ሙገሳን ወይንም ልዩ ሽልማትን የመፈለግ ዓላማ በሌላው ሁኔታ የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የሚያገኙበትን መንገድ ይከታተሉ። ይህን ማድረግዎ መንፈሳዊ እሳት እየተቀጣጠለ እንዲቀጥል ያደርገዋል። በመሆኑም ከስላሴ ጋር ይበልጥ ይቀራረባሉ፣ ከሃጢያት፣ ከሰይጣንና ከዓለም አስተሳሰብ ይለያያሉ። ስብከት

አገልግሎት ውስጥ ከመግባትዎ በፊትም ከእግዚአብሔር አጀንዳና ቀዳሚ ጉዳዮች ጋር ይሰለፋሉ።

4. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚራመዱበት ጊዜ ተጠግተው ይከተሉት። በመንፈስ ተመላለሱ (ገላ.5፡16) እራሱን ችሎ የማይንቀሳቀስ መኪና በሃይለኛ ኀታች ካሚን እንደሚሳብ በመንፈሳዊ ሕይወት እኛም እንዲሁ ነን። ሃይል ስለሌለን መንፈሳዊ እድገትን ልናፋጥነው አንችልም። ነገር ግን ወደ ሌላ አቅጣጫ በመንዳት ወይም በመለያየት ሂደቱን ልናዘገየው እንችላለን። ከዚህ ይልቅ የስጋን ፈቃድ እንዳንፈጽም መንፈስ ቅዱስ ወደፊት እንዲስበን እንፍቀድ።

በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አማካይነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጠንካራ ግንኙነት የሌለው ሰባኪ ስራውን ከሚያስፈልግ ነገር ጋር ይቀይጠዋል። ይህ እንዳይሆንበት የተቀደሰ ሃላፊነቱን ለማከናወን ወደ መናገሪያው መድረክ ለመውጣት ሚዘጋጅበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ሃይልን ማግኘት አለበት። ያን ጊዜ እንደ መንፈስ ቅዱስ እሱም ኢየሱስ ክርስቶስን በማክበርና እውነትን በጥራት በመግለጥ ተግባር ላይ ያተኩራል (ዮሐ.16፡13-15)

ሰባኪው በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት የሚታመነውና የሚይዘው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጠቃሚ ነጥቦች የተነሳ ነው።

1. **እስትንፋሰ-መለኮት**፡ 2ጴጥ.1፡21 ውስጥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር “በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ” ይላል። መንፈስ ቅዱስ የሚሰብኩትን መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከረጅም ጊዜ በፊት ባመጣ ጊዜ እርስዎ ጥናትዎና ስብከትዎ በአእምሮ እንደነበራችሁ ያውቃሉ? ካወቁ የስብከትዎን ክፍል ያመጣው ያው መንፈስ ቅዱስ ባለዎት አቅም የተቻለዎትን በማድረግ ኢየሱስ ክርስቶስን ያከበሩና ቃሉን

በጠራ ሁኔታ ለአድማጮች ያቀረቡ ዘንድ እንደሚያስችልዎ በመተማመን ነው የሚያቀርቡትን ክፍል የሚያጠኑት። ይህ ሃይል ነው እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በገጠመን ጊዜ ከእግዚአብሔር የሆነኤመረዳት እርግጠኛነትን የሚሰጠን።

2. **አፈታት ወይም አተረጓጎም፡** የእግዚአብሔርን ቃል ለመፍታት ወይም ለመተርጎም ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አብሮዎት ይሰራል። ለዚህ ነው ሰባኪው የመልዕክቱን ክፍል ሲያጠና ሲያዋቅርና የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ሲፈልግ መንፈሳዊ ጥንካሬ ሊኖረው የሚገባ። የጎሉና ግልጥ የሆኑ ሃጢአቶችን ይናዘዛሉ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለዎትን ፍቅር ይገልጣሉ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ… መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን" (1ቆሮ.2፡12-130 በሚለው መሰረት የስብከቱን ክፍል በመረዳቱ ረገድ መንፈስ ቅዱስ እንደሚገልጥልዎ ይተማመናሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናትዎና ስለፊቹው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍዎ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለተጻፈው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ያለዎትን ቅርበት ያረጋግጣል።

3. **አብርሆት፡** መንፈስ ቅዱስ ሰባኪውን ከግምት ግልጥ ወደ ሆነ ግንዛቤ ያሸጋግረዋል። የተጻፈውን የእግዚአብሔር መገለጥ ወደ መረዳት ያደርሰዋል ከዚያም አልፎ "የጌታ ቃል ወደኔ እንዲህ ሲል መጣ…" ወደሚያሰኝ እምነት ያሸጋግረዋል። ቃሉ እንዲተገበር የሚፈልገውን ነገር ለሰባኪው ግልጠ በማድረግ በግሉ እንዲገነዘበውና እንዲታዘዘው የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ ነው። ማለትም ጠቅላላው የስብከት ክንውን ከስብከቱ በፊት፣ በስብከት ጊዜና ከስብከት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ የታጀበ መሆን አለበት ማለት ነው።

መልዕክትን ማዘጋጃ መንገዶች

ሰባኪ መልዕክቱን እንዴት ያዘጋጃል? በምን በምን መንገዶች መልዕክቶች ሊዘጋጁ ይችላሉ? የሚሉትና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በዚህ ክፍል ይመለሳሉ። መልዕክትን ለማዘጋጀት ወሳኝ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥንቃቄ ማጥናት፣ የስነ-አፈታት መርሆችን ተግባራዊ ማድረግ፣ እና የስነ-አሰባበክ ሕጎችን ተግባራዊ ማድረግ ከብዙ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

3.4 ንባበ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ማድረግ

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለመስበክ ወይንስ ለሕይወታችን ለውጥ እናነባለን? መጽሀፍ ቅዱሳችንን የምናነበው በነሲብ ወይንስ በአንክሮ? ጊዜ ሰጥተን ከማጥኛ መረጃዎች ጋር ጥሩ ቦታና ጊዜን አስበን ወይንስ በድንገት፣ እነዚህንና የሚመሳሰሉ ጥያቄዎችን በዚህ ክፍል ላይ እንዳስሳለን።

3.5 የስነ-አፈታት ሕጎችን ተግባራዊ ማድረግ

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለመተርጎም ወይንም ለመፍታት የራሱ የሆነ የስነ-አፈታት ዕጎች አሉት ስለዚህ ማንኛውም ሰባኪ እነዚህን ህጎች አውቆ ተግባራዊ ማድረግ አለበት። ቃሉ ምን ይላል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ እስካልቻለ ድረስ ሰባኪ በመድረክ ላይ ወጥቶ የራሱን መላምት በቅዱስ ቃሉ ላይ መለጠፍ አግባብነት የሌለው እንደውም ሰዎችን ለስህተት የሚዳርግ መሆኑን ተረድተን አስቀድመን በተማርነው የስነ-አፈታት ትምህርት (*ኮርስ*) *መሰረት ተግባራዊ ልናደርግ ይገባናል።*

በዚህ ኮርስ ላይ የምናያቸውን የትኛውንም የአሰባበክ መርሆዎች በጥንቃቄ በየትኛውም ስብከታችን ላይ ተግባራዊ ልናደርግ ይገባናል። ለምሳሌ ከሰባኪው ሕይወት ጀምሮ ስብከቱን በመድረክ ላይ ከውኖ ሲወርድ እስከሚኖረው ሕይወት ድረስ ምን አይነት

ጥንቃቄዎች ሊያደርግ ይገባል የሚለውን ማንኛውም ሰባኪ አውቆ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

3.6 መልዕክትን በሚገባ ለአድማጭ (ለአንባቢ) ለማድረስ የሚረዱ መርሆች

የሰባኪ ተቀዳሚ አላማው መልዕክቱን በሚገባ ለአድማጮቹ ማድረስ ነው። ታዲያ ይህንን አላማውን ለመፈጸም የሚከተሉትን የስነ-አሰባበክ መርሆች በስብከቱ ወቅት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። በነገራችን ላይ እነዚህ አስር መርሆች ሁሉንም አይነት ስብከቶች በምናደርግበት ወቅት ተግባራዊ ልናደርጋቸው የሚገቡ ናቸው እንጂ በዝርዝር እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም።

3.7 የቃላት አነባበብ (Pronunciation)

ቃላትን እንደአገባባቸው ለመጠቀም በትክክል እንዴት መነበብ እንዳለባቸው ልናውቅ ይገባናል። ለምሳሌ፡- "ሳይገባው" የሚለው ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልዕክት ላይ የሚነገረው በትክክል ቃሉ ሊነበብ ይገባል አለበለዚያ ቃሉ የሚለው እና እኛ የምንሰብክበት መንገድ ይተላለፋል ማለት ነው። በሌላ መንገድ ደግሞ የቃላት አነባበብ አንድም የመጀመሪያ ቋንቋችን ባልሆነ ቋንቋ በምንሰብክበት ወቅት የሚከሰት ነገር ነውና ተጠንቅቀን ልናነብበው ይገባናል።

3.8 ግልጽነት (Articulation)

በምንሰብክበት ወቅት ለማለት የፈለግነውን ነገር አድማጮቻችን እንዲገምቱ በሚያደርግ መልኩ መስበክ ወይንም በቅኔ መናገር በእውነት ከሰባኪው የስብከት አላማ ጋር ፈጽሞ የሚጣረዝ ነውና ልናወግዘው ይገባናል። በሌላ አገላለጽ ለማለት የፈለግነውን ሁሉ ማለት (መናገር) መቻል አለብን እንጂ ለአድማጮቻችን መተው የለብንም።

3.9 የሰዋሰው ዕግን ማክበር (Grammar)

አንድ ሰው በሚሰብክበት ወቅት የሰዋሰው ዕግጋትን ማወቅ ብሎም ማክበር አለበት። ይህ ማለት ባለቤት ና ድርጊት ስምምነት (subject verb aggrement) *በንግግሩ ውስጥ ሊኖር ይገባል።*

3.10 ድምጸት- ድምጽ አወጣጥ (The Voice)

የድምጽ ከፍ ዝቅ-ማድረግ ፣ ወፈር ቀጠን-ማድረግ እና በድምጽ ቃና ላይ የተለያዩ ነገሮችን መጨመር ከምናስበው በላይ መልክዕክትን በማስተላለፍ ታላቅ ሚና ይጫወታል። የድምጽን ቃና አለመቀያየር መልዕክታችንን አታካች ሊያደርግብን ስለሚችል ልታስብበት ይገባል። በድምጽ አወጣጥ ላይ የሚከተሉትን ነገሮች ልብ ማለት ያስፈልጋል።

- *ድምጽህ የመልዕክትህን ቶን መግለጡን ማረጋገጥ*
- *ድምጽህ አድማጮችህ በሚገባና በማያውክ መልኩ እንደሚሰሙት ማረጋገጥ*
- *ማይክራፎን የምትጠቀም ከሆነ አግባብ በሆነ መልኩ መጠቀም*

3.11 የአይን እንቅስቃሴ (Eye Contact)

አድማጮችህን ከግራ፣ ከቀኝ፣ ከፊት ለፊት እንዲሁም በየአቅጣጫው በአይንህ መቃኘት በአይን ከእነርሱ ጋር ለመግባባት ቁልፍ ነገር ነው። ይህን ስታደርግ የምትጠቀማቸውን መልካም ጎኖች እና በአይን ከአድማጮችህ ጋር በምትገናኝበት ወቅት ማድረግ የሌለብህን ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

በአይን ከአድማጮችህ ጋር በምትገናኝበት ወቅት ለሚከተሉት ነገሮች ግምት ሰጥተሃል ማለት ነው ስለዚህም ተጠቃሚ ነህ ማለት ነው።

- *አድማጮችህ ትኩረታቸውን መረዳት ትችላለህ* (*እየሰሙህ መሆኑና አለመሆኑን መለየት ትችላለህ*)

- እያንዳንዱ ሰው ለእርሱ እየተናገርክ መሆኑን እንዲረዳና ልቦና እንዲሰጥህ ታደርገዋለህ
- ነገር በአይን ይገባል እንደሚሉት ብሂል በእነርሱ ውስጥ መልዕክትህን ማስተላለፊያ አንዱ መንገድን መጠቀምህ እንደሆነ ያሳስብሃል

ይህን የአይን ግንኙነት በምታደርግበት ወቅት ግን መጠንቀቅ ያለብህ ነገሮች አሉ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ልብ በል።

- በአንድ ሰው ላይ በተደጋጋሚ አይንህ ማረፍ የለበትም ምክንያቱም ያንን ሰው በተለየ አጽንኦት የምትከታተለው ሊመስለውና ሊጨነቅ ስለሚችል
- በአንድ አቅጣጫም ላይ ብቻ ትኩረትህ ሊሆን አይገባም ምክንያቱም በሌላ አቅጣጫ ያሉ ሰዎች ፊት ለፊት አንተን ማየት አለማቻላቸው ለሌላ ነገር ሊዳርጋቸው ስለሚችል።

ስለዚህ በአይን ከአድማጮችህ ጋር በምታደርገው ግንኙነት ልክ ያለው እና አግባብ እንደሆነ ተረዳ።

3.12 የሰውነት እንቅስቃሴ (Gestures)

አይ ን በተፈጥሮ የሚንቀሳቀስ ነገርን የሚከተል ስለሆነ የሰውነት እንቅስቃሴን ያማከለ አሰባበክ በተሻለ የአድማጮችን ቀልብ ይገዛል። ስለዚህ ሀዘንን፣ ደስታን፣ ንዴትን፣ ቅሬታን ወዘተ ሊገልጽ የሚችል የሰውነት እንቅስቃሴ ስብከታችንን በሰዎች ህሊና ውስጥ በመቅረጽ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህን ስንል ግን ለሰው አይን ግራ በሚያጋባ መልኩ ከመድረክ ጫፍ እስከ ጫፍ የሚደረግ እንቅስቃሴ መልእክታችንን ሳይሆን እንቅስቃሴያችን

ላይ ብቻ የሰውን አትኩረት ሊያደርግብን ብሎም ቶሎ ሊያደክመንና ትንፋሻቸንን ቁርጥ ቁርጥ ሊያደርግብን ስለሚችል ልንጠነቀቅ ይገባናል።

3.13 አሳምሮ መግለጽ (Dramatizations)

አንድን እውነት ለመናገር እውነትነቱን በማያዛባ መልኩ ነገር ግን አድማጭን በሚያዝናናና በማያሰለች መልኩ ለማቅረብ አንዱ መንገድ ንግግራችን ለዛ እንዲኖረው ለማድረግ ማሳመር ነው። ይህን የማሳማር ስራ ስንሰራ ግን ሰዎች ቁም ነገራችንን እንዳይዘነጉትና በአገላለጻችን ብቻ እንዳይማረኩ ልናስብ ይገባናል።

3.14 በምልከታ መሳሪያዎች መጠቀም (Visual Aid)

አንዳንድ ለስብከታችንን ማብራሪያ የሚሆኑ የምልከታ መሳሪያዎችን መጠቀሙ አንዱ አስፈላጊ የሆነ ዝግጅት ሲሆን በሰዎች ህሊና የማይጠፋን መልካም ትውስታን በመቅረጽ መንገድ ታላቅ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። መቼም ይህን አይነት ልማድ እምብዛም በአገራችን ያልተለመደ ቢሆንም ሰዎች ከሚሰሙት ይልቅ የሚያዩትን በአይምሮአቸው ከመያዛቸው ረገድ ይህን አይነት ልማድ ሊኖረን ይገባል። በምልከታ መሳሪያዎች በምንጠቀምበት ወቅት ግን ምልከታዎቹ በትክክል መልዕክታችንን የማስተላለፍ አቅም ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን በተጨማሪም አድማጮቻችን ስለምንጠቀምበት ምልከታ እኩል የሆነ አስተሳሰብ እና ፍቺ ሊኖራቸው ይገባል። ምክንያቱም ለተለያዩ ህብረተሰቦች የተለያዩ ምልከታዎች የሚሰጡት ትርጉም ለየቅል የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ። አሁንም ግን አድማጮቻችን ከመልዕክታችን ይልቅ የምንጠቀምባቸውን ምልከታዎች የየራሳቸውን ትርጉም በመስጠት በአሳብ ጭልጥ ብለው እንዳይሄዱብን ልናስብላቸው ይገባል። በተረፈ ግን የምልከታ የስብከት ዘዴ ጥሩ የማብራሪያ መንገድ ነው።

ማጠቃለያ

ወደ ማጠቃለያችን ስንመጣ ስብከት ከሰባኪው ሕይወት ጋር መገናኘቱን፣ ሕይወታችንን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መገራትና መመራት እንዳለበት በተጨማሪም ስንሰብክ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን በተገቢው መንገድ ለሕዝቡ ማቅረብ እንዳለብን እንድናስብ በማስመር ይህን ትምህርታችንን እናጠቃልል።

ስብከት ከተለወጠ ሰው ሕይወት የሚወጣ እስካልሆነ ድረስ የሰዎችን ሕይወት ይለውጣል ማለት ስለማንችል አስቀድመን በሕይወታችን ላይ ልንሰራ ይገባናል። ሕይወታችንን ሊለውጥ የሚችለው ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ፣ በምንሰብክበትም ወቅት የሚረዳንና ቃሉን የሚገልጥልን እርሱ መሆኑን ሳንዘነጋ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ልንጣበቅ ይገባናል። በመጨረሻም ከዚህ በላይ በተለያ መልኩ አጽንኦት ለመስጠት እንደተሞከረው የስብከት ዘዴን በአግባቡ በመጠቀም ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን መልእክት ለዘመኗ ቤተክርስቲያን ልናስተላልፍ ይገባናል ይህንም በፍጹም ፍቅርና አክብሮት ልናደርገው ይገባናል።

ምዕራፍ 4፡ የሰባኪው ህይወት

ሰባኪው ከእግዚአብሔር ምርጥ *መሣሪያዎች* አንዱ ነው 2ጢሞ. 1፡9 የሰባኪውና በስብከቱ ውስጥ እስከተካተተ ድረስ ፊልጳ ብሩክስ እንተናገሩት «ስብከት እውነትን ከሰው ወደሰዎች ማስተላለፍ ነው፡፡» (በዘሪሁን ለገሰ 1999 ዓ.ም) ስብከት በውስጡ ሁለት ዋና ዋና አስፈላጊ ቁምነገሮች አሉት እነሱም እውነትና ስብእና ናቸው፡፡ አንዳቸውን ትተን በአንዱ ብቻ የሚከናወን አይሆንም ስብከት በስብእና ውስጥ አልፎ እውነትን ማምጣት ነው፡፡ በአካላዊ ሁኔታው ሰባኪው ጥሩ ተክለ ሰውነት ከትህትና ተገቢና ቀለል ካለ አለባበስ ጋር ሊያማላ ሲገባው በአቀራረቡ የሰሚዎች ባህልና አኗኗር የሚመጥን መሆን አለበት፡፡ የአፍና የሰውነት ጠረን በማስወገድ

ጥሪት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከሰውነት ጥንካሬ የተነሳ የሰራ ቅልጥፍና ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ ሣይኮሎጂ ሰባኪው ትክክኛ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሣዊ ታሪካዊ ማሕበራዊ ሣይንሣዊና ሌሎችንም ከሰው ጋር የተያያዙ የእውነት ጭብጦችን መግለጽ አለበት፡፡ እውቀትነም በትምህት ማዳበር አለበት፡፡

በሌላ በኩል ድግሞ የሰባኪን ሕይወት ከስብከቱ መለየት አዳጋች ነው፡፡ ጆን. ኤፍ ማካርተር የተባለው የመፅሐፍ ቅዱስ ሰባኪ 1ጢሞ 6፡11-14 በመጠቀም ስለ ሰባኪ አራት መሰረታዊ ባህርያት ይተነትናል፡፡ በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ሠው የሚለው ስያሜ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ወይም ቃል ለሚናገር ሠው መጠርያ ሆኖ በተለያዩ ስፍራዎች ያገለገለ በመሆኑ ይህን መጠርያ /ቃል/ ሠባኪ በማለት መተርጎም ይቻላል፡፡ /ሙሴ፡-ዘዳ 33፡1፣ ሳሙኤል 1ሳሙ 9፡6፣ ኤልያስ 1ነገ 17፡18፣ ኤልሳ 2ነገ 4፡8-9/

4.1 ሰባኪ / የእግዚአብሔር ሠው/

1. ሕይወት እና አገልግሎቱን ከሚጎዱ ነገሮች የሚርቅ /የሚሸሽ/ ቁ 11

   /ምሳ 7፡1-27፣1ቆሮ6፡18፣ 1ቆሮ 10፡17፣ 1ጢሞ 6፡20፣ 2ጢሞ 2፡22፣9-10፣ 2ቆሮ 2፡27/

2. ዘወትር ፅድቅን እና ቅድስናን የሚከታተል፡፡ ቁ11

   ግማሽ ቅድስና ማለት ከክፉ መሸሽ እና ወደ እግዚአብሔር አለመቅረብ ማለት ነው፡፡/መዝ15፡1፣ 1ቆሮ 9፡22

3.ለጠላት የማይረታ፡፡ ቁ12 በጠላት ሀሳብ የማይታለል እና የማይሸነፍ

4. ለጥሪው ታማኝ የሆነ ቁ12-14

አንድ ሠው ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት የሚያደርግ ከሆነ ሁል ጊዜ በሕይወቱ እና በአገልግሎቱ የተነቃቃ ከመሆኑም ባሻገር ለጥሪው ታማኝ ለመሆን የሚያስችለውን ሐይል ከእግዚአብሔር መቀበል ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ሰባኪው፡-

- ከእግዚአብሔር የተላከ መሆን አለበት መዝ. 10፡15
- ህይወቱ እንደፈሪሣዊ ያልሆነ ማቴ. 23
- ህሊናው የማይወቅሠው
- ምሣሌ መሆን የሚችል የሚታዘዝ ሮሜ. 2፡21-24 የተተገበረ እውነት አቅም ስለ አለው
- የሚያቀርበውን መልዕክት ጠንቅቆ የሚያውቅ 1ኛ ጴ 3፡15
- የመልዕክቱን ማቅረቢያ መንገድ ጠንቅቆ የሚያውቅ

4.2 የሰባኪነት ጥሪ

ይህ ስጦታ ያለው አገልጋይ ምን እንደሚመስል ለምሣሌ ጥሪው ባህሪይ ብቃቱና ተግባሩ ምን እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

1. በተፈጥሮ ሲወለድ የተሰጠው የተፈጥሮ ችሎታ ሊሆን ይችላል፡፡

2. በመንፈሳዊ ሕይወቱ በዳግም ልደት የሚሰጠው መለኮታዊ ስጦታ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ገልጦ በማስተማር ክርስቲያኖችን ደቀመዛሙርት የሚያደርግ ስር ሰደው እንዲያድጉም

የሚረዳ ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ በተፈጥሮ ከነበረው ችሎታ ጋር አንድ ላይ በሚገናኝበት ጊዜ በመንፈሳዊ አገልግሎትና አስተምህሮ ውጤታማ ያደርጋል።

«ጥሪ» የሚለው ቃል በመሠረቱ ከብዙ መንገድ ልተረጐም ይችላል። ለምሣሌ «ድነት» በኢየሱስ አምኖ መዳን የድነት ጥሪ ነው። በዚህ ክፍል ስንመለከት የአስተማሪነት ጥሪ ማለት ለአንድ ዓላማ ተጠርተው በተጠሩበት ዓላማ መለየት ወይም መቀደስ ነው። «የአገልግሎት ጥሪ በመስፈርት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ይከናወናል።» (ከበደ በከሬ ገጽ 8 ና 9)።

- 1 ሳሙ 3፡4-14 ሳሙኤልን እግዚአብሔር የዔሊን ቤት ኃጢአት እንዲነግር ጠራው
- ሙሴን እግዚአብሔር የእስራኤላዊያንን ጩኸት ሰምቶ ጠራው ዘጸ. 2።
- ዛሬም አስተማሪ በቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በእግዚአብሔር የተጠራ ነው። ኤፌ 4፡11

4.3 ክርስቲያን ሰባኪ

ክርስቲያን ሰባኪዎች ክርስትያኖች ለኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንዲያደርግ ከዓለም ሁሉ ታላቅ ሥራ የተሰጠው በመሆኑ ምእመኖቻቸውን የተማሩትን እውነት በየዕለቱ ኑሮአቸው እንዲተገብሩና የሕይወት ለውጥ እንዲያሳዩ ሁኔታ ማመቻቸት ነው። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐ 15፤15) የሚለውን እውነታ በተማሪዎች ሕይወት ተግባራዊ እንዲሆን ሁኔታ ያመቻቻል። በተጨማሪም ሰባኪ ማለት «እውነትን ከስህተት ለይቶ የሚነግር፣ አቅጣጫን የሚያሣይና የተነገረውን እውነት የሚያስጨብጥ፤ አልፎም ሌሎች እንዲማሩ የሚያደርግ ነው።» (የማነ ብርሃን እንዳለ ገጽ 190።) አንድ መምህር በተማረበት ትምህርት ተማሪውን በሚገባ በማሰልጠን ወደተፈለገው አላማ ብቁ ዜጎችን ማፍራት የሚችል አላማ

ያለው መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ትልቁ ምሣሌ ኢየሱስ ነው፡፡ ደቀመዛሙርትን ከሰለጠናቸው በኋላ ወደዓለም ሁሉ ላካቸው ዓላማው አሰልጥኖ መላክ ስለሆነ ላካቸው ማቴ. 28፡18-20፡፡

4.4 የስብከት ተግባር

- ወንጌልን ላልሰሙ ሰዎች ማካፈል
- ደቀመዛሙርትን ማፍራት

ኢየሱስ በሐዋርያት ታላቁን ተልእኮ ሲሰጥ «ያዘዝሁዋችሁን እንድትጠብቁ እያስተማርካችሁ ደቀመዛሙርት አድርጓቸው ፡፡» (ማቴ. 28፡18-19)፡፡

ያመኑትን ደቀመዛሙርት ማድረግ የአንድ ሰባኪ ተግባር ስለሆነ አገልግሎቱ በይበልጥ የማስተማር ስጦታ ያለው አስተማሪ ይፈለጋል፡፡

- ያመኑት በመንፈሣዊ ሕይወት እንድያድጉ መርዳት

«ወንጌላዊ ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲመጡ ሲያደርግ «የማስተማር ስጦታ» ያለው ደግሞ አማኞች በጌታ ቤት ፀንተው እንዲቆሙና በመንፈሳዊ ህይወታቸው እንዲያድጉ የሚረዳ ነው፡፡» (መለሡ ወጉ ከገጽ 125) የማስተማር ስጦታ ያለው አስተማሪ አማኞች በእግዚአብሔር ቃልና በእምነታቸው ፀንተው እስከ መጨረሻ እንዲቆሙ የሚረዳ ነው፡፡

በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ቃል ለመንጋው ማስተማር፣ መጠበቅ፣ መምራትና መንከባከብ ነው፡፡ አዳዲስ አማኞችንም ደቀመዛሙርት ለማድረግ፣ የሚያስተምረውንም ትምህርት በቅደም ተከተልና በስርዓት አደራጅቶና አዘጋጅቶ ስለሚያስተምር የአድማጩን ቀልብ በመሳብ በንግግር በመጠቀም ተጨባጭ እውነቶችን በማስተላለፍ ተፅእኖ ያመጣል፡፡

በቲቶ መልእክት ምዕ 1፣ቁ 9 እንደሚገልፀው «ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ዳግም ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል ይፅና፡፡» አስተማሪው የስህተትን ትምህርት በመቃወም አስተማሪዎችን በማረም የትምህርታቸውን ስር አድርቆ እውነትን በመግለጥ ስራውን ያከናውናል፡፡

4.5 የወንጌል ሰባኪያን አላማ

የሰባኪው ወይም የሕዝቡን ወቅታዊ ጉዳይ ማጉላት ብቻ ሣይሆን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በማብራራት የቃሉን አቀነባበር እና አቀራረበ በችግር በመፍትሔ በመስጠት ስልት ላይ ያተኩራል፡፡ (በዘሪሁን ለገሰ በ1999) ፡፡

የስብከት አላማው ለሰው መንገር ማግባባትና የመልእክቱንና የትምህርቱን ባለቤት ለሆነው እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ኃይልና ህልውና ተናጋሪም ሆነ አድማጮች ግንዛቤ መሻት ነው፡፡ የማያምኑትን ሰዎች የወንጌል ቃል በመንገር ከክርስቲያን ጋር እንዲታረቁና ከሌሎች አማኞች ጋር ሕብረት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

4.6 የሰባኪ ባህርይ

- ትሁት መሆን አለበት
- ትህትና ለአንድ አገልጋይ አንዱ ባህሪይ ነው፡፡
- የሐዋርያትን እግር በማጠብ ኢየሱስ ትህትና አሰተማረ፡፡ ዮሐ.13፡12-15
- ኢየሱስ ለበጐት ትሁት ልብ ነበረው፡፡ ማቴ. 11፡29
- ትህትና የሚትገኘው ራስን ዝቅ ከማድረግ ነው፡፡

አንድ ሰባኪ ከኢየሱስ ህይወት በመማር ለተማሪዎቹ ምሣሌ የሚሆን የትህትና ሕይወት መኖር አለበት፡፡ ትህትና በእግዚአብሔር ለተጠራ አገልጋይ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አንዱ የመንፈስ ፍሬ ስለሆነ ሁልጊዜ በህይወቱ መታየት አለበት፡፡

- የፍቅር ልብ ያለው መሆን አለበት

አንድ ሰባኪ ለሚያገለግላቸው ሰዎች የፍቅር ልብ መኖር አለበት፡፡ ጳውሎስ ሲናገር «... እኛ ግን የክርሰቶስ ልብ አለን» 1 ቆሮ. 2፡16፡፡ ይህ የክርስቶስ ልብ ለልጆች የዋህና ትሁት ልብ ነው፡፡

«ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነው፡፡ » ሮሜ. 13፡10፡፡ አንድ አገልጋይ ከኢየሱስ ህይወት በመማር ለሚያገግልባቸው አገልጋዮች የፍቅር ልብ መኖር ያስፈልጋል፡፡

- ምሣሌ የሚሆን ህይወት ያለው መሆን አለበት

ምሣሌ ሁን እንጂ ማንም ተናሻነትህን አይናቀው፡፡» 1ጢሞ. 4፡12፡፡ አስተማሪ ለህዝቡ መልካም ምሣሌ መሆን አለበት፡፡

«ምሳሌ መሆን ማለት ሌሎች ሰዎች አይተው መከተል የሚገባቸው ዓይነት ሞዴል መሆን ነው፡፡» (ከከበደ በከሬ ገጽ 98፡፡)

ዛሬም አንድ ሰባኪ ወይም አስተማሪ እግዚአብሔርን በመምሰልና በመጽናት ምሣሌ መሆን ይገባዋል፡፡

ጳውሎስም እንዳለው «እኔ ክርሰቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» 1ቆሮ 11፡1፡፡

ሁለቱ የሰባኪዎች ምሳሌ

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአስተማሪነት ፀጋ ተገልጠው ሕዝቡን ያስተማሩ ብዙ ቢሆንም ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን አንድ አንድ ሰው በመውሰድ ከህይወታቸወና ከአገልግሎታቸው ትምርት ልወሰድ ይገባናል

1. የብለይ ኪዳን ምሣሌ ዕዝ. 7፡10

በዚህ ኪዳን ውስጥ የመረጥኩት ምሳሌ ሰው አስተማሪ የሆነው ዕዝራን ነው፡፡ ዕዝራ ለ70 ዓመት ያህል በምርኮ ኖሮ የተመለሰና ውስጡ የተዘረፈበትን ትውልድ አገልግሎ የሰማዎቹን ልብ መለወጥ መቻሉ በርግጥ አሰማሪ መሆኑ ባይካድም የመለወጡ ጉልበት የተገኘው ቃሉን ለመማር ለመታዘዝና ሕዝቡን ለማስተማር ይደረገው የነበረው የልብ ዝግጅት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ሰማዎች ለመስማር ያላቸው ጉጉት እንዲጨምር / የቀን ሩብ ያህል ቆመው ቃሉን መስማታዋው/ እና ቃሉን በመታዘዝ የህይወት ለውጥ እንዲያመጡ አድርጓል፡፡ ስለዚህ አስተማሪ ልክ እንደ ዕዝራ ቃሉን ለመማር ለመታዘዝ ሕዝቡን ለማሰተማር ከመነሳሳት ባሻገር ሰማዎቹ ደግሞ የህይወት ለውጥ በማግኘት የአገልለት ግቡን ማየት ይገባዋል፡፡

2. የአዲስ ኪዳን ምሣሌ

የአዲስ ኪዳን የአስተማሪ ምሣሌያችን ደምቆ የሚታየው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርሱ ምሳሌነት የምንማረው

- **ዋናው ስራው ማሰተማር ነበር**

ኢየሱስ በዚህ ምድር በስጋ በነበረበት ሰዓት ዋና አገልግለቱ ማስተማር እንደነበር የምንረዳው ካደረጋቸው ንግግሮች መሐከል 45 ጊዜ ያህል ሲያስተምር 11 ጊዜ መሰበኩን ሰናይ ነው፡፡

- **ትምህርቱ የሰውን ሁለንተናን አገልሎትን ያጠቃልል ነበር**

ኢየሱስ የተናገራቸውን ንግግሮች በምንመለከትበት ጊዜ ምተናገራቸው ንግግሮች ውስጥ አንድን ፅንፍ ብቻ ይዞ የሚሄድ ሳይሆን የሰወን ሁለንተና ያቀፈ ነበር።

- **ትምህርቱ እንደ ባለስልጣን ያስተምር ነበር። ማቴ.7፡29**

ኢየሱስ ትምርቱን እንደ ባለስልጣን ሆኖ የማስተማሩ ጉልበት ቃሉን ማወጡ ብቻ ሣይሆን ከህይወቱ የወጣ ወይም የታዘዘው ቃል መሆኑ ነበር።

- **የሰሚዎችን ህይወት ይለውጥ ነበር**

በኢየሱስ የማስተማር አገልሎት ውስጥ የሰዎች ህይወት የመለወጡ ምክንያት ሰዎች በትክክል እንዲረዱት ትምህርቱን የሚያዘጋጃቸው በሚዎቹ በቀላሉ እንዲሰሙት በተለያዩ ዘዴዎቹ በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉና በሚያውቁት ምሣሌ መጠቀሙ ነው።

- **ትምህርቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ሌሎችን ያስለጥን ነበር**

አገልጋይ የራሱን ጊዜ ካገለገለ በኋላ አገልግሎቱ የሚቆረጥበት ምክንያት በማያገለግሉበት ጊዜ ሌሎች በቀጣይነት እንዲያገለግሉ ሌሎችን አለማሰልጠን ወይም ስፍራ አለመስጠት ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ግን የራሱን ተልዕኮ ከተወጣ በኋላ ቀጣይነት እንዲኖረው ሌሎችን መርጦ ያሰለጥን ነበር በኋላም ሀዋሪያቶች ይኽንን ተልዕኮ በሚገባ ተወጥተውት እናያለን፡

- **የሰባኪዎች ኃላፊነት በቤተክርስቲያን**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሰጣት ታላቅ ተልእኮአ ግሉ ሰዎች የአየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝመር ማድረግ ነው ቤተክርስቲየን ይሃንን ተልእኮዋነ መወጣተ የምትችለው

እንደማታወቀው በማስተማር ነው። ስለዚህ ማስተማር በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ትልቅ ባታ አለው ማለት ነው። ይሁን እንጂ መንአልባተመ ከአለወ እድገተ የንፃር ትኩረት ተሰጥቶበት የተደረጃ በካሪኩለም የተቀዳ ወይም ትምህርት የበተክርሰቲያን ልዋውና ማስጠበቂያ መሣሪይ መሆኑ በወል ታውቆ በሚገባ የተደራጀ ላይሆነ ይችተላል ያም ሆኖ የማስተማር አገለሎተ በብዙ መልኩ በቤተከርሰቲያን ውስ ይከናወናል በሰብከተ ጊዜ የሰንበት ትምህርት ልጆችን በማስተማር የድህነት ወይም የእምነተ ማጽኞ ትምህርት በተጨማሪም ስልጠናዎችና ደቀማዛምርተ የማድረግ ተምርት እንዲሁም በመንፈሣዊ ትምርት ቤት በማብተማር የትምርት አገልሎት በሰፊው ይሰጣል በዚህ ሁሉ አስተማሪዎች አገልለታቸው ትኩረት ባይሰጠውም በቤተክረስቲያን ያላቸው ኃላፊነትና የስራ ድርሻ ግን በጣም ሰፊና ተለቅ ነው ብዙ ገዘ ለተለያዩ ፀጋዎተ ትኩረት ይሰጣል። የመስበክ አገልግለትን በዙ ትኩረት ባይሰጠም ያለው ኃላፊነተ ገነ በጣም ሰፊ ነው።

ሰባኪ መሪ እንደመሆኑ መጠን የሚከተሉትነና እርሱ የሚቀረፃቸው ብዙ ሰዎች ከበስተኃላወ አሉት የሰዎተን ሕይወት ጊዘ ወስደ አቅጣጫ የማስያዝ ትልቅ ኃላፊነተ ነው፡ የአስተማሪዎች አገለሎት ጠቅለል ባለ መልኩ የአስተማሪ ኃለፊነተ ነው። በቤተክርስቲያን በጣም ሰፊ ነወ ምዕምናን በስህተተ ትህርት እንዳይበከሉ በጥንቃቄ ያስተምራል። ያሣውቃል ይጠብቃል ለእግዚአብሔር ቤት አገልግለትም ምዕናን ያዘጋጀል ከአለበት ኃለፊነት አንፃር የሚከተሉተን በትጋት ያከናወናል።

- **ግብን ትኩረት ያደረገ ትምህርት ለማስተማር ዘወትር ይዘጋጃል**
- **የትምህርቱን ይዘት በሚገባ ባለመታከት ይገነዘባል ያወቃል**
- **የትመህርት መረጃዎችን እንዴት እንደሚጠቀመና የማስተማር ዘዴዎች እንዴት በስራ ላይ እንደሚያወል ያጠናል ያቅዳል**

- **የሚያስተምረውን ትምህርት በጊዜ ገደብ በመክፈል ማስተማር ያለበትን ያቀናጃል**
- **የሚማሩትን ተማሪዎች ችለታሃ ትመህርት አቀባበል ደረጃቸውን በማገናዘብ ያስተምራል**

4.6 የማስተምር ፀጋ እና የእረኝነተ አገልግሎት ተጓዳኝነት

ብዙ ጊዜ በብዙ ስፈራ አስተማሪንና እረኞችን በጣምራ እንደ አንድ ስጦታ በመውሰድ ይጠቀሙበታል ነገር ግን በተግባር ሰንመለከት አንዳንዶቹ የእረኝነት አገልግሎት ጎልቶ ሲታይባቸወ በአንዳንዶቹ ደገሞ የማስተማር አገለለት ጎልቶ ይታይባቸዋል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የማስተማር የእረኝነት አገልሎት ይያያዛል ወይም አንድ ነው የማባለው በኤፌ 4፡11 ላይ «እረኞችና አሰተማሪዎች አደረገ» የማለው አባባለ ሁለቱም የተጣመረ ናቸው በማለት ብዙዎች አነሳስቷል፡፡ በእርግጥም ነገሩ ሲታይ መንጋን መጠበቅ መመገብ የማቻለው በማሰተማረ ነው፡፡ የእርኛ ተልቁም ስራ መንጋውን መመገብ መቸል ነው፡፡ ስለዚህ አንዳንዶች በማስተማር ብቻ ቢተጉመአንዳንዶችም በእረኝነት ተተግባር ብቻ ቢተጉም የእረኝነት የአስተማሪነት ፀጋ ተጓዳኝነት አለው በአንዳንድ መጽሐፍት ላይ «እንደ ፀጋ ስጦታዎች » በተሰኙ መጽሐፍት ላይ የማስተማር እና የእረኝነት አገልሎት ተጊዳኝነት ሲገልፁት «እረኛ ወይም የመጋቢ አስተማሪዎች» በማለት ስለተጓዳኝነታቸው ይናገራሉ በተጨማሪም እረኛ የማለው ቃል ከመጋበ አስተማሪ ጋር በመያያዝ ነው የሚጠቀሰው በማለት ሀሣበቸውን ያጠናክራሉ ለእነዚህ አባባሎች የማገብዛቸው በይበልጥ የማስተማር አገልለት ወይም ፀጋ የሚኖረው መጋቢ ነው የሚለውወ ሀሣብ ነው፡፡ የእረኛ እና የአስተማሪ ተጓዳኝነት የመገልፀ ተገባሮች

- የአስተማሪውም የመጋቢውም አንዱ ሥራቸው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልሎት ማዘጋጀት ነው፡፡ አፌ. 4፡12

- አገልለታቸው በፍቅር ላይ የተመሠረተ መሆኑ ዮሐ. 21፡15-16 በአረግጥ ሁሉም አገልግሎት ያለፍቅር ከንቱ ነው። በግልጽ ደግሞ በእረኝነት በማስተማር አገለለት ውስ ፍቅር በፍሬያማነት ወሣኝ ነው።

- መጋቢም አስተማሪም ተጓዳኝ የማያደርጎቸወ ሥራ ሌላው መንጋን መመገብ ነው። መጋቢመንጋውን ተመጣጣኝ ተምርት በማዘጋጀት ይመግባል አስተማበም አስፈላጊውን ሁኔታ በማጤን ያሰተምራል

4.7 የማስተማርና የመማር መርሆዎች/ሕጎች/

4.7.1 የአስተማሪው ሕግ

- መምህር ሊሰጥ ያለው ትምህርት ወይም እውነት ወይም ጥበብ የሚያውቅ መሆን አለበት
- የማስተማሪያ ጊዜን ለመሸፈን የሚያስችል ብቻ ሳይሆን ከዚያ የላቀ ማወቅ ያስፈልጋል።
- ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉ ለመገንዘብና በአእምሮ ለመያዝ ተግቶ ማጥናትን ይጠይቃል።
- ትምህርቱን በሚገባ የሚያውቁ መምህራን በሚያስተምሩ ጊዜ ይቀላቸዋል።
- ያለተጠበቁ ጥያቄዎችንም መመለስ ያስችላል።

4.7.2 የተማሪው ሕግ

- ትክክለኛ ተማሪ የሚሰጠውን ትምህርት በፍላጎት የሚከታተል ነው። የተማሪዎችን /የልጆችን/ ቀልብ ሳይዝ የሚያስተምር መምህር ትርጉም የሌለው ከንቱ ልፋትን ያደርጋል።

- ቀልብ/ATTENTION/ አተኩሮ ማሰብ

- ትምህርት ቤት ያልገቡ ሕፃናት አተኩሮ የማሰብ ጊዜ በጣም ትንሽ ነው /1 ዓመት=1 ደቂቃ/
- እደሜያቸው ከፍ ሲል ከፍ ይላል፡፡
- KG ችሎታቸውን ማድነቅና በረዥም ውይይት መሳተፍ ይጀምራሉ፡፡
- 2ኛ ክፍል ሲደርሱ በደንብ ከሰለጠኑ አካላዊ እንቅስቃሴ ወደ የአእምሮ ሥራ ይዘዋወራሉ መዘዋወሩን ይወዱታል ስለሆነም አተኩሮ የማሰብ ጊዜ መጠናቸው ይጨምራል፡፡
- ተማሪዎች ወደ ክፍል እንደመጡ እንዲያስቡ በሚያነሳሳ ሁኔታ ውስጥ አስገባቸው፡፡ በመጀመሪያው ጊዜ ቀልባቸውን ከያዝክ በሂደቱም በተሻለ ልትጠብቀው ትችላላህና፣ ቀልብ/አተኩሮ ማሰብ/ አነሳሳ — ጠብቀውም — አተኩሮ ማሰብ ወደ ፍላጎት ይለወጥ፡፡

ፍላጎት

- ቀልብን/አተኩሮ ማሰብን/ መጠበቅ በፍላጎት ላይ ይደገፋል፡፡
- በትዕዛዝ ወይም በዓይን እንቅስቃሴ ቀልብን መሳብ ወይም መያዝ ይቻላል፡፡
- ሊጠበቅ የሚችለው ግን ፍላጎት ሲኖር ነው፡፡
- ፍላጎት እንዲፈጠርና እንዲጠበቅ የሚያደርጉ ምክንያቶች
- የተማሪውን የአስተሳሰብ አድማስ ማወቅ/plane of thought/
- የሚያውኩ ውጫዊ ነገሮችን ማስወገድ
- በተማሪዎች ችሎታ የተመጠነ ትምህርት ማቅረብ
- የተማሪዎችን ተሳትፎ ማስገባት
- ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተቃኘ ትምህርት ማቅረብ

4.7.3 የቋንቋ ሕግ

- በመምህሩና በተማሪው መካከል የሚሠራበት ቋንቋ ለሁለቱም ወገኖች የጋራ መሆን አለበት፡፡
- የመምህሩ የሚያስተምረውን ማወቅና የተማሪው በጥሞና መከታተል አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የተሳካ ግንኙነት/communication/ ከሌለ እጅግም መማር አይኖርም፡፡
- ለተማሪውም ላስተማሪውም ግልጽ የሆነ ቋንቋ መጠቀም ይገባል፡፡
- የቋንቋን ሕግ በሥራ ላይ ለማዋል የሚከተሉትን አስተውል፡፡
- ባለማቋረጥና በጥንቃቄ የተማሪዎችህን ቋንቋ አጥና፡፡
- በጉዳዩ ላይ የተማሪዎችህን እውቀት መዝን፡፡
- በተቻለ መጠን ራስህን በተማሪዎች ቋንቋ ግለጽ፡፡
- ማለት የምትፈልገውን የሚገልጽልህን በተቻለ መጠን ቀላልና ጥቂት ቃላትን ተጠቀም፡፡
- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ተጠቀም፡፡
- ቀለል ባለ በሌላ አባባል ሃሳብህን ደግመህ ግለጽ፡፡
- ቃላትን በምሳሌ ግለጽ፡፡
- አዲስ ቃል ማስተማር ስትፈልግ አስቀድመህ ኃሳቡን ግለጽ/ምሳሌ incarnation ተሠገዎ/፡፡
- የተማሪዎችን ቃላት ቁጥር ለመጨመር ሞክር የትርጉም ግልጽነትንም ለማሻሻል ሞክር፡፡
- ተማሪዎች በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታ፡፡
- የምትጠቀምባቸውን ቃላት ተማሪዎች መረዳታቸውን በየጊዜው ገምግም፡፡

- ትንንሽ ልጆች በቀጥታ በጥሬው/litrally/ ያስባሉ፡፡ ስለሆነም በሕፃናት አስተማሪዎች ሥዕላዊ ቋንቋ መጠቀም የለባቸውም፡፡ እነርሱ በሚያውቁት ሁኔታ ውስጥ ማስተማር ይገባል፡፡

4.7.4 የትምህርት ሕግ

- ሊማሩት ያለው ትምህርት ተማሪው በሚያውቃቸው እውነታዎች መግለጽ መቻል አለበት፡፡ የማይታወቀው በሚታወቀው አማካይነት መግለጽ አለበት፡፡

- ተማሪው በሚያውቀውና በተለማመደው ነገር ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ቀለል ባለ መንገድ ወደ አዲሱ ሃሳበ መሄድ፡፡

- ማስተማር ከመገናኛ ነጥብ መነሳት አለበት፡፡ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ አዲስ ከሆነ የሚታወቅ ነጥብ መፈለግ አለበት፡፡ ይህ የመገናኛ ሕግ ለአእምሮ እድገት መሠረታዊ ነው፡፡ አዲስ እውነታዎች ሊታወቁ የሚችሉት በቀደመው ላይ በመመስረት ነው፡፡

- ጌታ ኢየሱስ ይህን ተጠቅሞበታል፡፡ በሚታወቁ እውነታዎች ላይ በመመርኮዝ አዳዲሶቹን አስተምሮአል፡፡
    - የእርሱ ስቅለት — በበረሃ የነሃስ እባብ መስቀል
    - መቀበሩና መነሳቱ — የዮናስ ታሪክ
    - ዳግም ምፃቱ — እንደኖህና ሎጥ ዘመን

የትምህርት ሕግን በሥራ ላይ ለማዋል የሚተሉትን ዘዴዎች አስተውል፡፡

- የቀደሙ ትምህርቶችን ከአሁኑ ጋር አገናኝ

ቀድመው የተማሩት አሁን ሊማሩት ላለው ብርሃን በመስጠት እንደ መገናኛ ነጥብ ያገለግላል፡፡ ያፈውን መከለስ ለዚህ ይጠቅማል፡፡

- ደረጃ በደረጃ አስተምር

አንድ ዓላማ አተኩር። እዚያ ላይ ስትደርስ ወደሚቀጥለው ይወስዳሉ የምትላቸውን ሃሳቦች ደረጃ በደረጃ አስተምር።

- በምሳሌ በማስረዳት አብራራ

በመማር እርምጃ ውስጥ አብሮ ለመንዝዝ ቀድሞ የሚታወቁ ነገሮች ዓይነተኛ ብርሃንን ያበራሉ

ግንዛቤን ከአንዱ ወደ ሌላው ማዛወር

ተማሪዎች አባትና እናታቸውን ሲታዘዙ እግዘኢብሔርን ይታዘዙታልን? በአንድ ሁኔታ ውስጥ የተማሩትን ነገር በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ማዘዋወር።

- የማስተማር ሂደት ሕግ

ማስተማር ተማሪውን እንዲያስብ በማነሳሳት አእምሮውን ተጠቅሞ የተፈለገውን ሃሳበ ወይም ጥበብ እንዲጨብጥ ወይም እንዲካን ማድረግ ነው።

መልካም መምህር ተማሪው በራሱ እንዲማር ሁኔታዎቹን ያመቻቻል። መምህሩ እውቀትን መወርወር ወይም ማንቆርቆር ሳይሆን ተማሪው በራሱ ውስጥ እንዲፈጠርለት ማድረግ አለበት። ለዚህ ተማሪዎችን ማነሳሳት ያስፈልጋል። ተማሪው በራሱ እንዲያጠና ምሳሌ መሆንና ምንጮችንም ማቅረብ ይጠበቅበታል። ተማሪዎች በራሳቸው የሚማሩ ሲሆኑ የመማር ሂደት ይፋጠናል። ውጤቱም ዘለቄታ ይኖረዋል። የማስተማር ሂደት ሕግን በሥራ ላይ ለማዋል መምህሩ የሚከተሉትን ሊያደርግ ያስፈልገዋል።

ተማሪው በአግባቡ እንዲያስብ የሚያስችሉትን ጭብጦች አቅርብለት። ሰው ሊያስብ የሚችለው ቀድሞ ከተከማቹ ጭብጦች በመነሳት ስለሆነ ጭብጦችን ማስያዝ ያስፈልጋል።

የምርምር መንፈስን አነሳሳ። በመብሰል ላይ ያለ አእምሮ ከዓለም አቀፍ ችግሮች ጋር ይታገላል። /የሚወድቅ አካል ኒውተንን ስለ ግራቪቲ እንዲመራመር አድርጎታል/ ተማሪው ለማወቅ ጥያቄን እንዲጠይቅ ማነሳሳት ይገባል። አንዳንድ ነገሮችንም እንዲያብራራ ማደፋፈር ይገባል።

ተማሪው በሥራ እንዲረካ አመቻችለት፡፡ አንድ ሰው ጠቃሚ ውጤት ያለውን ነገር ሲሰራ በዚያው ለመቀጠል ይነሳሳል ስለሆነም ትምህርት ከሕይወትና ከፍላጎት ጋር ቢያያዝ መልካም ነው፡፡

የመማር ሂደት ሕግ

መማር አዲስ ሃሳብን በራስ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማሰብ ወይም ጥበብ /ክህሎት/ ወደ ልምድ እንዲለወጥ መሥራት /መለማመድ/ ነው፡፡

ትምህርት ከመምህሩ ይልቅ የተማሪው ሥራ ነው፡፡ ውጤታማ አስተማሪ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲንቀሳቀሱ ያነሳሳል፣ ይመራል፡፡ የተማሪዎችን ምላሽ ይገመግማል፡፡ ተማሪዎች አዲስ እውነታዎችን እንዲገመግሙና በመሠረታዊ ኑሮ ጥበብ እንዲተረጉሙት ይረዳል፡፡

ትምህርት የተማሪውን ቀልብ፣ ፍላጎት፣ ግልፅና ቀጥተኛ እንቅስቃሴ ይጠይቃል፡፡ የትምህርቱን ሃሳብ ለማግኘት ተማሪው አእምሮውን በአግባቡ ማሰራት አለበት፡፡

ትክክለኛ ትምህርት ከድግግሞሽ ይልቃል፡፡ ተማሪው አዲስ ነገር ማፍለቅ ወይም መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ የሌሎችን እውነታዎች ተጠቅሞ ከራሱ ልምድ ማዳበር አለበት፡፡

መማር ሦስት ደረጃዎች አሉ

1. በትክክል መገልበጥ

አንድን ትምህርት በትውስታ ውስጥ በማስገባት ቃል በቃል መልስ መትፋት ይቻላል፡፡ የሚያስታውሱትን ነገር በትክክል ያልተገነዘቡ ተማሪዎች ተማሩ ማለት አይቻልም፡፡ ትክክለኛ ትምህርት የተማሩትን ነገር በራስ ቃላትና ልምድ መግለጥን ይጠይቃል፡፡

2. መተርጎም

ተማሪው አንድን አዲስ ሃሳብ በራሱ ቃላት በመጠቀም የራሱንም ሃሳብ አክሎ መግለጽ ሲችል ትክክለኛ ትምህርት ተካሂዷል ማለት ይቻላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተማሪ የራሱንም ሆነ የሌሎችን ሃሳቦች ማስተናገድና ማገናዘብ ይችላል፡፡

ጥሩ መምህራን ተማሪው እንዲመራመር የሚረዳውን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ /ለምሳሌ ‹ለምን?›/

3. በሥራ ላይ ማዋል

ማንኛውም ትምህርት በሥራ ላየ እስከሚውል ድረስ ሙሉ ለሙሉ ተምረውታል ማለተ አይቻልም፡፡ እውቀት ኃይል ነው፡፡ ይሄ የሚሆነው ግን በቁጥጥር ስር ውሎ በሥራ ላይ ሲውል ብቻ ነው፡፡ አንድን ሃሳብ መግለጥ አእምሮን ያሰለጥናል፡፡ እውቀትን በሥራ ላይ ማዋል ግን በፈቃድ ላየ ተጽዕኖ በማረግ ሕይወትንም ይለውጣሉ፡፡ በሥራ ላይ ማዋል ቸል የተባለ እንደሆነ ተማሪዎች ‹ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉ› ይሆናሉ፡፡2ጢሞ3፡7፡፡ የአእምሮ እውቀት ብቻ የእግዚአብሔር ፀጋ የሕይወት ለውጥ እንዲያስገኝ አይፈቅድም፡፡

የመከለስና በሥራ ላየ የማዋል ሕግ

የትምህርት መፈተኛ እና ማስረጃ መከለስ፣ እንደገና ማሰበ እንደገባ ማወቅ፣ በትክክል መገልበጥ እና የተማሩትን በሥራ ላይ ማዋል መሆን አለበት፡፡

በየትምህርት ክፍለ ጊዜ አስቀድመው የተማሩትን መከለስና ከአሁኑ ጋር ማገናኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ዛሬ የተማሩትን ወደሚቀጥለው ትምህርት ማሸጋገር አስፈላጊ ነው፡፡

እያንዳንዱ ትምህርት በተማሪው ሕይወት ፋይዳ እንዲኖረው ማድረግም ይገባል፡፡

ክለሳ ያለፈውን ትምህርት ከማጠናከሩም በላይ ያለፈው ትምህርት ከአዲስ ሃሳቦች ጋር ተገባኝቶ ውጤቱ የላቀ እንዲሆን ያደርጋል ጉዳዩ በአዲስ መንገደ በሥራ ላየ የሚውልበትን ያስመርጣል፡፡ ስህተትንም ማረም ያስችላል፡፡

ይህ መርህ በሥራ ሲውል የሚከተሉት ሦስት ጥቅሞች አሉ፡-

- እውቀትን ማጠንከርና ፍፁም ማድረግ፣

ክለሳ ከድግግሞሽ ይልቃል፡፡ እውነታዎችንና መርሆችን እንደገና በአትኩሮት መመልከትነ ያካትታል፡፡ ከዚህም በላይ የጠለቀ ብርሃን ነው፡፡ ተማሪው አስቀድሞ ያልያዛቸውን ነገሮች ደግሞ ሲያነብ ወይም ሲመለከት ሊያስተውላቸው ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ደጋግሞ ማተዋልን ይጠይቃል፡፡

- እውቀትን ማስታወስና ማጽደቅ
- እውቀትን በሥራ ላይ ማዋልና መለማመድ
- የተሞላ ክለሳ እውቀት በሥራ ላይ እንዲውለ ያዘጋጃል፡፡

የማስተማሪያ መንገዶች

ጥሩ የማስተማሪያ መንገድ የትኛው ነው? የትምህርቱን ዓላማ ለመፈፀም ከሌሎች ይልቅ የሚያስችል አናጢ ምስማር ለመንቀል መጋዝ እንደማይጠቀም ሁሉ አስተማሪው አንድን የማስተማሪያ መንገድ ለሁሉም ዓይነት ዓላማ አይጠቀምም፡፡

- አንድን ዘዴ በቻ እንድንጠቀም የሚገፋፉን ሁለት ምክንያቶች
- አስተማሪው በተማረበት ዘዴ ማስተማርን ያዘነብላል፡፡

- የልምድ ጉዳዩ ይሆንና ለውጥን የመሸሽ ባህሪ ይታያል፡፡
- እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ዓይነተኛ ጥቅም ያላቸው ብዙ ውጤታማ የማስተማር መንገዶች መኖራቸውን መገንዘብ የማስተማር ውጤታማነትን ያሻሽላል፡፡
- ለውጥ የሚያስፈራ ሳይሆን የሚያበረታታ ሊሆን እንደሚገባ መገንዘብ ያሻል፡፡

መምህሩን ማዕከል ያደረጉ የማስተማሪያ መንገዶች

ሌክቸር - Lecture

መምህሩ ለተማሪዎች ይናገራል፡፡ ለተማሪዎቹ የሚሰጠውነ ኢንፎርሜሽን ይናገራል፡፡

በስፋት በሥራ ላይ የዋለ መንገድ ነው፡፡ በተለይም ለአዋቂዎችና አንዳንዴም ለወጣቶች እንጠቀምበታለን፡፡

ጥቅሞቹ፡-

- የተማሪዎቹ ቁጥር ብዙ ሲሆን
- ብዙ ኢንፎርሜሽን በሚቀርብበት ጊዜ
- ትምህርቱ አዲስ ቢሆንበት ጊዜ
- መምህሩ ችሎታ ያለውና የሚስብ ሲሆን

ተማሪዎች ሌሎች መንገዶችን ባልተለማዱበት ሁኔታ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሌክቸር መሰናክል ሊገጥመው ይችላል

- መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ በአእምሮው ካልያዘው፣ በደንብ ካልተዘጋጀና ቅደም ተከተሉን ባለማወቅ ወዲያና ወዲህ ከረገጠ

- የተማሪዎችን ተሳትፎ የመከላከያ መንገድ ከሆነ
- መምህሩ በግልጽ መናገር የማይችል እንደሆነ
- ሌክቸር በሚከተሉት መንገዶች ሊሻሻል ይችላል
- በትክክለኛው የማስተማሪያ ሁኔታዎች ብቻ በመጠቀም
- ተማሪዎች ቀደም ብለው በማንበብ የመስማት ፍላጎታቸው እንዲጨምር የንባብ የቤት ሥራ በመስጠት
- ግልጽ ቋንቋ እና ሁነኛ የድምጽ አወጣጥ በመጠቀም
- በቂ ምሳሌዎችና መረጃዎች በመስጠት
- የሚታዩ ነገሮችን በመጠቀምና ሌሎች የማስተማሪያ መንገዶችን ጣልቃ በማስገባት
- እንዲያስቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎችን በማዘጋጀት
- የተማሪዎችን ስሜትና ፈላጎት በመከታተል አስፈላጊ ለውጥ/መሻሻል/ በማደረግ
- ሌክቸርን በክለሳ፣ በማጠቃላያና የተማሪዎችን መረዳት በመገምገሚያ በማጠናቀቅ መዝጋት፡፡

ትረካ

ታሪክን በመንገር ማስተማር ብዙ ጊዜ ሕጻናትን ለማሰተማር እንጠቀምበታለን፡፡ ነገር ግን በየትኛውም ዕድሜ የሚገኙትን ለማስተማር ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይነተኛ ተራኪ ነበር፡፡

ጥቅሞቹ

- ያለፈውን ነገር ሕያው በማድረግና ተማሪዎቹም በአግባበየ እንዲለማመዱት በማስቻል የተማሪዎችን ቀልብ ይስባል፡፡
- እውነትን በድርጊት ያቀርባል፡፡

- የሚታወቀውንና የማይታወቀውን ለማገናኘት ይረዳል፡፡
- መሰናክል
- የአስተማሪው በአግባቡ መተረክ አለመቻልና ለመጠቀም ፈቃደኛ አለመሆን
- ጠንካራ የዶክርቲን ሃሳበ የያዙ ትምህርቶች ለትረካ አለመመቸት መቻል
- ታሪኩን በቃል ሳያውቁ ማንበብ

ትረካ በሚከተሉት መንገዶች ሊሻሻል ይችላል

- ድርጊት፣ ውዝግብና አጓጊነት ያለው ክፍል ምረጥ
- እንዳታነብ ታሪኩን በደንብ ተጠቀም
- በአፅንኦት፣ በድረጊት፣ በፊት ሁኔታና በተማሪዎች የመረዳት ችሎታ በመደገፍ ጠቂት ቃላትን ተጠቀም
- ቀደም ብለህ መተረክን ተለማመድ
- ተማሪዎች አንዳንድ ነገር እንዲያደርጉና ጥያቄዎችንም እንዲመልሱ አድርግ/መረዳታቸውነ ለማወቅ/፡፡

ለትረካ መዘጋጀት /ትረካን ማዘጋጀትና ማቅረብ/

ጥሩ ትረካ ለመተረክ ተግቶ መሥራ፣ መለማመድና ጸሎትን ይጠይቃል፡፡ ታሪክ የራሱ የሆነ ቅርጽ አለው፣ መግቢያ፣ ተከታይ ፍሬ ነገሮች፣ ቁምነገር እና መደምደሚያ፡፡ ለምሳሌ ሉቃ15፡11

ሀ. መግቢያ

ፍላጎትን የሚያነሳሳ፣ የታሪኩን ገፀ-ባህሪያት የሚያስተዋውቅና ድርጊትንም

የሚጀምር መሆን አለበት ሉቃ15፡11፣12

ለ. ተከታታይ ድርጊቶች growing actions /ፍሬ ነገሮች/

ከባህሪያቱ ድርጊቶች የተገኙ ውጤቶች፣ ጥያቄና መልስ፣ ችግርና መፍትሔ በመከታተል ሲቀርቡ ፍላጎትን ይጠብቃሉ፡፡ በአባካኙ ልጅ ታሪክ ዋናው ባህሪ ቤቱን ለቀቀ፣ ገንዘብን አጠፋ፣ ከሰረ … አስተዋለ፡፡

የሚከተሉትን መጠየቅ ይቻላል

ለምን ቤቱን መልቀቅ ፈለገ?

ገንዘቡን ካጠፋ በኂላ ጓደኞቹ የት ሄዱ?

ሐ. ቁምነገር/climax/

የድርጊቶቹ የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው?

ከድርጊቶቹ የተገኘ አጠቃላይ ውጤት

ለምሳሌ ልጁ በእርግጥ ይቅርታ ይጠይቃል? አባቱ አይቀበለው ይሆን? የሚያስገርመው አባቱ ሮ አቀፈውና ሳመው ሉቃ 15፡20

መ. መደምደሚያ/conclusion/

አጭርና ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ንስሀ የሚገቡትን እግዚአብሔር ይቅር ብሎ ይቀበላቸዋል /ሉቃ15/

አንዳንዴ ነጥቡ ግልጽ ላይሆን ስለሚችል ጥያቄ መጠየቅ ወይም በአጭሩ ማጠቃለል ያስፈልጋል ካላጠረ ድራማው ውበቱን ያጣል

አንዳን ጊዜ መጨረሻው ክፍት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ምን ታደርግ ነበር?/መልሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ይገመገማል/

በምሳሌ ማስረዳት/illustration/

በሥራው የተካነ አስተማሪ የማስተማር ዓይነተኛ መሳሪያ የሆነውን «በምሳሌ ማስረዳትን» ይጠቀማል፡፡

በምሳሌ ማስረዳት ተማሪው የቀደመውንና የሚያውቀውን በመጠቀም ወደ አዲስና ወደማያውቀው ነገር እንዲደርስ ያደርገዋል፡፡

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች/parables/ ዓይነተኛ የቃል ምሳሌዎች ናቸው

ጌታ ምሳሌዎችን በመጠቀም በተለመዱ ነገሮች አዳዲስ መንፈሳዊ እውነታዎችንና የቀደሞዎቹንም በአዲስ ብርሃን እንዲረዱ አድርጓል፡፡

በምሳሌ የማስረዳት ፋይዳዎች

አንድ መምህር የሚያውቀውን ነገር በማቅረቡ/በመዘርገፉ/ ብቻ ሥራውን ጨረሰ አይባልም፡፡ ተማሪዎች የተማሩትን እውነታ ጥቅም መረዳትና የተማሩትንም ማስታወስ አለባቸው፡፡ ስለሆነም እውነታዎቹ

- በፈቃዳቸውና በስሜታቸው ተጽዕኖ ማሳደርና
- አንድን ነገር እንዳያደርጉ ሊያነሷሷቸው ይገባል፡፡
- ስለሆነም በምሳሌዎች ማስረዳት
- የተማሩትን እውነታ ጥቅም ለመረዳት ያስችላል
- የተማሩትን ለማስታወስ ያስችላል
- በፈቃዳቸውና በስሜታቸው ተጽዕኖ ያሳድራል
- ከተማሩት አኳያ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ወይም ሕይወታቸውን ለመለወጥ ያነሳሳቸዋል
- በምሳሌ የማስረዳት ዓይነቶች
- ሁለት ዓይነት በምሳሌ የማስረጃ መንገዶች አሉ፡፡
- የሚታዩ በምሳሌ የማስረጃ መንገዶች አሉ፡፡

- በቃል የሚሰጡ ምሳሌዎች
- በቃል የሚሰጡ ምሳሌዎች

ምሳሌያዊ ታሪኮች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንግስተ ሰማይ በቀጥታ ሳይሆን በምሳሌዎች አስተምሯል፡፡

የንግግር ስዕሎች የሕይወት እንጀራ ነኝ /ስዕላዊ ንግግሮች/ በር ነኝ /የሚያመሳስሉ/

ሌሎች ጉዳዮችን መጥቀስ ታሪክ፣ ሳይንስ … ወዘተ

የምሳሌያዊ ማስረጃዎች ምንጮች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ

የሰዎች ታሪክ በእግዚአብሔር እይታ ተዘግቦበታል/ባፀጋ ምንጭ/

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን ለማስታወስ ይጠቅማል፡፡

ለ. የግል ልምምድ

በጣም ግልጽና አስገራሚ በሆነ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን ለማስታወስ ይጠቅማል፡፡

ሐ. ታሪክ፣ የግለሰቦች ታሪክ፣ ተፈጥሮ፣ ሳይንስ፣ ዜና … ወዘተ

ምሳሌዎች በየቦታው አሉ፡፡ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ምሳሌዎችን ማኘት ሳየሆን አስታውሶ መጠቀሙ ያዳግታል፡፡ ስለሆነም መጠራቀም መልካም ነው፡፡

ምሳሌያዊ ማረጃዎችን መጠቀም

ግልጽና ጠቃሚ የሆኑ ዓይነተኛ ምሳሌዎች /ምሳሌያዊ ማስረጃዎች/ የሚከተሉት ባህሪያት አላቸው፡፡

ሀ. ግልጽ

የሚተላለፈውን ሃሳብ የሚገልጽ/ግንኙነት ያለው/

ተማሪው በሚያውቀውና በተለማመደው ነገር ላይ የተመረኮዘ /ራሱ ማብራራትን የሚጠይቅ ከሆነ መልካም አይደለም/

ለ. አጭር

በእርግጥ እውነቱን በሚገባ ለማሳየት የሚችል መሆን አለበት፡፡

አጭር ሆኖ ተማሪው ሊተላለፍ የሚገባውን ነገር እንዲወስድ መፍቀድም አለበት፡፡ /ግማሹን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከወሰደ በጣም ረጅም ነው፡፡

ሐ. አዲስ እና ትኩስ

ጥሩ ምሳሌ እንኳን ብዙ ጊዜ ከተጠቀምንበት ይደበዝዛል

በቅርብ የሆነና ትኩስ ከሆነ ተማሪዎችን ይማርካል፡፡

መ. ጨዋነት የተላበሰ

በርግጥ የሚያስቁ ነገሮችን ሁሉ ጠራርጎ ማስወገድ አይገባም አንዳንዴ ይጠቅማሉና፡፡

ተማሪውን ማሳተፍ

መማር ከማዳመጥ ይልቃል፡፡ ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ሳያደርጉ ዝም ብለው ታሪክ ወይም ዲስኩር የሚያደምጡ ከሆነ የአእምሮ ስንፍና ይይዛቸዋል፡፡ የሚያገኟቸውን ሃሳቦች ሰለማያበላሏቸወ ግንዛቤያቸው ብዣ ያለና ያልተሟላ ይሆናል፡፡

ማዳመጥ ወደ ንቁ ተሳትፎ ሊመራ ይገባል፡፡ ጥሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ወደ ተሳትፎ ለመምራት የሚያገኙትን አጋጣሚ ሁሉ ይጠቀማሉ፡፡ ተማሪዎች የሚማሩትን በሚገባ እንዲገነዘቡ እና ከሕይወታቸው አኳያ በመተርጎም በሥራ ላይ እንዲያውሉት ከተፈለገ የእነርሱ ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጥሩ ትምህርት ተማሪውን ወደ ጉዳዩ ስቦ የሚያስገባ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ተማሪዎችን ለማሳተፍ በራሳቸው ማጥናት አለባቸው። አስቀድሞ ማጥናት የሚተሉት ጠቀሜታዎች አሉት

- ከትምህርቱ ጋር ወይም ከሃሳቡ ጋር ትውውቅ ለማድረግ
- መምህሩ ተማሪዎቹ ጉዳዩን ምን ያህል እንደሚያውቁ ለመገንዘብ ይረዳዋል።
- ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲያጠሩ ይረዳቸዋል።
- የማሰብ ስንፍና ያለባቸውን ተማሪዎች ለማነሳሳት።
- ድግግሞሽ ተሳትፎ አይደለም። ያነበቡትን ነገር ራሱን መልሰው እንዲያነበንቡ ማድረግ የማስታወስ ችሎታቸውን ከማዳበሩ በስተቀር ንቁ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ ከአእምሮ ስንፍና አያላቅቅም። ስለሆነም ተማሪዎች የተገነዘቡትን ሃሳበ በራሳቸው ሁኔታና በራሳቸው አባባል እንዲገልፁት መምራተ ያስፈልጋል።

ተማሪዎችን በሚገባ ለማሳተፍ ለሚከተሉት ትኩረተ መስጠት ያሻል

ሀ. የሚፈጸም ተግባር/የቤት ሥራ/

በተማሪው ችሎታ እና የጊዜ አቅም የተመጠኑ የቤት ሥራዎችን መስጠት ያስፈልጋል።ይህ ከሆነ ተማሪው የቤት ሥራውን መስራት ይችላል። ከዚህም በላይ ተማሪው የተሰጠውን ተግባር በሚገባ ሲፈጽም የሚያገኘውን ጥቅም

ካወቀ ሥራውን ለመሥራት ፍላጎት ይኖረዋል። ስለሆነም መምህሩ ይህን ማሳወቅ አለበት። ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎቹን ፍላጎት ማወቅ አለበት። ይህ ከሆነ ከተማሪው ሁኔታ ጋር የተቃናና ትርጉም ያለው የቤት ሥራ ማሰራት ይቻለዋል።

ለ. የተማሪው ዝግጅት

ተማሪዎች አመርቂ ተሳትፎ እንዲያሳዩ ከተፈለገ የቤት ሥራቸውን ለመሥራት በቂ የዝግጅት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

እንደዚሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም የሚነበቡ መጻሕፍት እንዲኖሩ ያስፈልጋል።

ሐ. የክፍል ተሳትፎ

ለተማሪዎች ተሳትፎ በቂ ጊዜ መስጠት ይገባል።

ሁሉም ተማሪዎች እነዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል።

አንዳንድ ተማሪዎች ተሳታፊ የማይሆኑት አይናፋር በመሆናቸው ወይም ባለመዘጋጀታቸው ነው። ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። ሰነፍ ተማሪዎችን ማበረታታት እንጂ በተማሪዎች ፊት ማፋጠጡ እጅግም አይጠቅምም።

መደምደሚያ

የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም መምህሩ ውጤታማ መሆን ይችላል።

- ዲስኩር፡- በደንብ ዝግጅት ከተደረገና በፍላጎት ከቀረበ ውጤታማ ነው።
- ትረካ፡- መምህሩ ታሪኩን በደንብ ካወቀና ከተለማመደ የተማሪዎችን ቀልብ ይስባል።
- በምሳሌ ማስረዳት፡- ብርሃን የሚሰጡ መስኮቶች ናቸው። የሕይወት ለውጥ ለማስገኘት በጣም ይረዳሉ።
- ተሳትፎ፡- ተማሪዎቹ በጉዳዩ ውስጥ እንዲገቡ ከማድረጉም በላይ የተማሪዎችን የግል ጥናትና ዝግጅት ይጠይቃል።

ምዕራፍ አምስት፡ መልክቱን ማዋቀር

መልክቱን በምናወቅርበት ጊዜ ሁለት ዋና ዋና ስራዎች መስራት ይጠበቅብናል

1. ሆሚሊቲካል ሀሳቡን ማስቀመጥ (Formulating the homiletical idea)

ይህ ሀሳብ ለመጀመሪያዎቹ የመልክቱ አንባቢዎች ክፍሉ ከሚሰጠው ሀሳብ (Exegetical idea) የሚቀጥል ሀሳብ ሲሆን በዚህ ወቅት መልስ ሊያገኝ የሚችለው ጥያቄ «ይህ ሀሳብ ለእኛ አድማጭዎች ምን ማለት ነው=» እና «እንዴት አድርጌ ነወ ለአድማጭዎች ማቅረብ ያለብኝ=» የሚሉት ናቸው። በአጠቃላይ በዚህ ወቀት መልእክቱ ለእነርሱ ከሚሰጠው ሀሳብ በመነሳት ለእኛ ወደሚሰጠው ትርጉም ወይም ትምህርት ይለወጣል ማለት ነው።

በዚህ ወቅት መገንዘብ የሚጠበቅብን ሁለት መሠረታዊ እውነቶች

1. መልዕክቱ የጊዜ ገደብ የሌለው ከሆነ እምብዛም ለውጥ አያስፈልገውም

ለምሣሌ፡- «ፃድቅ በእምነት በሕይወት ይኖራል» ዕንባ 2፡4

2. ሆሚሊቲካል ሀሳቡ በተሟላ መልክ መቀመጥ አለበት

ለምሣሌ፡- 1 ጢሞ 5፡ 1-2 የዚህ ክፍል የመጀመርያወ ሀሳብ (Exegetical idea))

ዮውሎስ ጢሞቲዎስን ሌሎችን እንደ አንድ ቤተሰብ አባላት በማክበር እንዲከባከባቸው (እንዲየገለግላቸው) ይመክረዋል፡፡

ሆሚሊቲካል ሀሳብ (homiletical idea) (የስብከቱ ዋና ሀሳብ)

እኛ ሌሎችን እንደ አንድ የቤተሰብ አባላት በማክበር ልናገለግላቸው (ልናስተናግዳቸው) ይገባናል፡፡

2. መልክቱን በማውጫ ማስቀመጥ (በቅደም ተከተል ማስቀመጥ)

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሰባኪው ከየትኛው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል መስበክ እንዳለበት የሆሚሊቲካል ሀሳቡን ርዐስ (Subject) እና ማሟያውን (Complement) በሚገባ አስቀምጦአል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የሰባኪው ተግባር መልእክቱን በማውጫ (በቅደም ተከተል) ማዋቀር ይሆናል፡፡

ለምሣሌ፡-1.

ሀ-

ለ-

ሐ-

2.

ሀ-

ለ-

1.

2.

3.

ሮቢንሰን ማውጫ በምናዘጋጅበት (መልእክቱን በቅደም ተከተል በምናስቀምጥበት) ጊዜ ልንተገብራቸው የሚገቡ ስድስት መመሪያዎች ይሰጠናል።

- ማውጫው መግቢያ ሰውነት (body) እና ማጠቃለያ (መደምደሚያ) ሊኖረው ይገባል
- ማውጫው እያንዳንዱን ዋና ዋና ሀሳቦች ማካተት አለበት
- ማውጫው ግልፆ እና የሀሳብ ቅደም ተከተልን በጠበቀ መልክ መዋቀር አለበት
- እያንዳንዱ በማውጫው ውስጥ የሚካተቱ ሐሳቦች በተሟላ አረፍተ ነገር መቀመጥ አለባቸው
- ማውጫው በስብከት ወቅት መነበብ የለበትም
- ማውጫው ከአንድ ሀሳብ ወደሚቀጥለው ሀሳብ ለመሸጋገር በሚስችል መልኩ መዋቀር አለበት። የመሸጋገሪያ ቃላትም ያካተተ መሆን አለበት።

3. ማውጫውን ማዳበር ወይም መሙላት (Felling in the outline)

ሮቢንሰን ይህን ደረጃ አጥንት በስጋ የሚሞላበት እና ሕይወት የሚዘራበት ወቅት ነው ይለዋል። ማውጫው ብቻውን ያለቀለት መልዕክት መሆን ስለማይችል ማውጫው የሚከተሉትን ዘዴዎች በመጠቀም መሞላት ወይም መዳበር አለበት።

መደጋገም (Repetition) አንድን ሀሳብ ምንም ሳይቀይሩ መልሶ ማስቀመጥ ወይም መድገም ማለት ነው።

አንድን አረፍተ ነገር የመጀመርያውን ሀሳብ ሳይለቅ በሌላ ቃላቶች በመተካት ማስቀመጥ (Restatement)

ማብራርያ (Explanation) የተለያዩ እምቅ ሐሳቦችን ማብራራት እና ለቃላቶች ትርጉም መስጠት

4. መልዕክቱን ማሽብረቅ ወይም መሙላት (Coloring the sermon)

ገለፃዎች፡- ምሣሌዎች እና ሌሎች ሀሳቦችን በመጠቀም መልክቱን ማራኪ ወይም መሳጭ ማድረግ

- መልእክትን የምናስውበት ምክንያቶች
- መልዕክቱን በጣም ግልፆ ለማድረግ
- የአድማጭን የመስማት ፍላጎት ለማነሳሳት
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ አድማጭ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ጊዜአዊ እረፍት ለአድማጭ ለመስጠት

መልእክትን የምናስውብባቸው መሳሪያዎች

- የተለያዩ ፅሁፎች (መፅሐፍቶች እና ጋዜጦች)
- የግል ታሪክ
- የተለያዩ አባባሎች

መልእክትን ለማስዋብ የምንከተላቸው መመሪያዎች

- የምንጠቀማቸው ማስዋቢያዎች ግልፅ መሆናቸውን እ ከመልእክታችን ጋር ተያይዥነት እንዳላቸወ በሚገባ ማረጋገጥ
- ማስዋቢያዎቻችንን በትክክልኛ ቦታ እና ጊዜ መጠቀማችንን እንዲሁም ዋናውን መልዕክት አለመሸፈናቸውን ማረጋገጥ

- ስለምንጠቀምባቸው ማስዋቢያዎች በቂ እውቀት ሊኖረን እና ማስዋቢያዎቹ ትክክልኛ መሆናቸውን መረጋገጥ
- በስፋት መተንተን ያለብን ዋናውን ሀሳብ መሆኑን አለመዘንጋት
- አንድ መልዕክት ሲዋቀር ሊያካትታቸው የሚገባው ዋና ዋና ክፍሎች

ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው አንድ መልዕክት ሲዋቀር ሦስት ዋና ዋና ክፍሎችን ይካትታል፡፡ እነርሱም መግቢያ መአከላዊ ክፍል (body) እና መደምደሚያ ወይም ማጠቃለያ ናቸው፡፡ ባለፈው ትምህርታችን ስለመአከላዊ ክፍል በሚገባ ስላብራራን በዚህ ክፍል አንመለከተውም፡፡ ስለአንድ መልክት ማዕከላዊ ክፍል በአጭሩ ለማጠቃለል የመልዕክቱ መአከላዊ አካል አንድ ትልቅ ሀሳብ ያለው ሲሆን ይህም አንድ ትልቅ ሀሳብ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ ርዕስ (subject) እና ሟሟያ (Complement)፡፡ ስለዚህ አንድ መልእክት ሲዋቀር እነዚህ ሁለት የአንድ ትልቅ ሀሳብ አካላቶች በግልፅ በመልክቱ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

መግቢያ

መግቢያ የአንድ መልዕክት የመጀመርያ ክፍል ሲሆን ተናጋሪው ስለመልዕክቱ የመንደርደሪያ ሀሳብ የሚያቀርበት ነው፡፡

የመግቢያ አላማዎች

1. የአድማጭዎችን ትኩረት መሳቢያ ነው

አህያ እና ሰው አስቀድሞ ጆሮአቸው ከተያዘ መላ ማንነታቸውን በቀላሉ መቆጣጠር ይቻላል፡፡

2. የመልዕክቱን መአከላዊ ክፍል ማስተዋወቂያ ነው

3. በተጨማሪም መግቢያ የመልዕክቱን ዳራ (Background) ለማብራሪያነት ያገለግላል

መግቢያን ስናዘጋጅ እና ስንጠቀም ልንተገብራቸው የሚገቡን መመሪያዎች

ይቅርታ አለመጠየቅ

መግቢያን በአጭሩ ማስቀመጥ

በማያስፈልግ ሀተታ ጊዜ እንዳይባክን መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በሌሎች ሀሳቦች ላይ ሰፋያለ ጊዜ መውሰድ ማለት ዋናው የመልዕክት ሀሳቦችን አንገብጋቢ አይደለም ማለት ነው፡፡

ለአድማጭዎችህ ልትሰጣቸው ከምትችለው በላይ ቃል አለመግባት

በመግቢያ መሐክል የመፅሐፍ ክፍል ማንበብ

አሻሚ ሚስጢዊ የሆኑና ተያያዥነት የሌላቸውን ሐሳቦች ከንግግርህ ማስወገድ ገና ከመጀመሪያው አድማጭህ ግራ ከተጋባ በትዕግስት በመቀጠል መልዕክትህን በፍጹም መከታተል አይቻልም፡፡

መግቢያ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት

መግቢያውን ከመጀመርህ በፊት በጣም ለተወሰነ ጊዜ ጸጥ ማለት ያስፈልጋል ይህን በመተግበር በቀላሉ የአድማጭህን አትኩሮት ማግኘት ይቻላል፡፡ በመጣደፍ መጀመር አደጋው ብዙ ስለሆነ በመጣደፍ አትጀምር፡፡ በሰላምና ጉባኤውን በማመስገን ጀምር፡፡

ፍርሃትን መቆጣጠር፡ በተቻለ መጠን የማስታወሻ ደብተርን ከመመልከት ይልቅ በተረጋጋ መንፈስ ሕዝቡን ቃኝት ማድረግ ተመራጭ ነው፡፡

መግቢያን ለማዘጋጀት የሚረዱ ምንጮች

የግል ታሪክ

ጥያቄ

ከመፅሐፍት የተወሰዱ ሀሳቦች

ወቅታዊ ሁኔጸ እና የስታስቲክስ ዳታ (Statistical data)

ሮቢንሰን ሦስት አይነት ሰባኪዎች አሉ ይለናል፡፡ የመጀመርያዎቹ ሊሰሙ የማይቻል አይነት ሰባኪዎች ሌሎቹ ልትሰሙዋቸው የምትችለአቸው አይነት ሰባኪዎች እና የመጨረሳቹ ደግሞ አልሰማችሁም ልትሉአቸው የማይቻላችሁ አይነት ሰባኪዎች ናቸው፡፡

አድማጭም የቱአይነት ሠባኪ እንደሆንክ የሚለየው እና ሊሰማህ ወይም ላለመስማት ውሣኔ የሚያደርገው ከመግቢያህ ንግግር በመነሳት ስለሆነ ከመነሻው ለመልክትህ መጠንቀቅ አለብህ፡፡

ይህን ርዕስ ለማጠቃለል ሦስቱን የስብከት አይነቶች በአጭሩ እናነፃፀር

ርዕሳዊ	አውደምንባባዊ	ትንታቲያዊ
ርዕስ ከመምረጥ ይነሳል	የተወሰነ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመምረጥ ይነሳል	ተከታታይነት (ተያያዥነት) ያለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሦችን በመምረጥ ያነሳል
ርዕሱን የሚደግፉ ጥቅሦች በሁለተኛ ደረጃ ይፈለጋል	መነሻው ከጥቅስ ነው	መነሻወ ከጥቅሦች ነው
የመልዕክቱ አወቃቀር (አከፋፈል) በርዕሱ የሚወሰን ይሆናል	ጥቅሱ ርዕሱን (Subject) እና ማሟያውን (Complement) ይሰጣል፡፡	ጥቅሶቹ ርዕሱን (Subject) እና ማሟያውን (Complement) ይሰጣል፡፡

ተጨማሪ ዝግጅት

1. **ስነ ልቦናዊ መመሪያ (ዝግጅት)**

የአንድ ሰባኪ የስብከቱ አላማ ሰዎችን በማግባባት እና በማሳመን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ፣ በፀጋ እንዲያድጉ፣ እና የተትረፈረፈ ሕይወት በክርስቶስ እንዲያገኙው መርዳት ነው፡፡ ስለዚህ አንድን ሰው ለማሳመን የሰውየውን አዕምሮ፣ ስሜት እና ፈቃድ በእግዚአብሔር ቃል መድረስ ያስፈልገናል፡፡

አዕምሮ ከዕውቀት ጋር የተገናኘ በመሆኑ ለማመን ስለንስህ እና ስለሚያምነው ነገር ግልፅ መረጃ ማግኘት አለበት፡፡ *ስሜት* ደግሞ ስላወቅነው ነገር የሚፈጠርብን ጠንካራ ስሜት ሲሆን ትክክል ነው ብሎ ያመነበትን ሀሳብ ወደ ልባችን ይልከዋል፡፡ *ፈቃድ* ውሳኔ ለማድረግ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ለመወሰን ግን የአዕምሮ ዕውቀት እና የስሜት መነሳሳት ያስፈልገዋል፡፡

እነዚህ ሶስት እውነታወች የስነ ልቦና እውነታወች ናቸው። አንድ የስነ ልቦና ሙሁር እንዲህ አለ አንድ ሠው ምን ማድረግ እንዳለበት ካላወቀ መዳን አይችልም። በተመሳሳይ ሁኔታ ላወቀው ነገር ስሜት ከሌለው ፈቃድው ውሳኔ ማድረግ ይሳነዋል። ምክንያቱም እነዚህ ሦስት የስነልቦና እውነታዎች ተያይዘው ሲሰሩ ነው ሠው ትክክለኛ ውሳኔ ለሰማው ነገር መስጠት የሚችለው።

2. የሰባኪ ስሜት

የሰባኪ ስሜት ሁል ግዜ ለመስበክ መነሳሳቱ ውጤታማ ስብከት ለመስበክ ከፍተኛ አስተዋፅዎ ያደርግለታል። ስብከትን ውጤት ከሚያሳጡት ምክንያቶች አንዱ እና ዋንኛው የስሜት መቀዝቀዝ ወይም መጎዳት ነው።

የስሜት መቀዝቀዝ ወይም መጎዳት አንድ ሰባኪ ካለበት የጤና ችግር፣ የግብረገብነት መውረድ፣ የስልጠና እጦት፣ በቂ ያልሆነ ትምህርት፣ እና በቂ ያልሆነ ተሰጦ በስብከት ላይ ከሚያመጡት ጉዳት የበለጠ ጉዳት የማምጣት አቅም አለቅው። ስለዚህ አንድ ሠባኪ የስሜት ብሰለት /Maturity/ ሊኖረው ያስፈልጋል። በመድረክ ላይ የሠባኪን ስሜት ከሚጎዱ ነገሮች ውስጥ ስሜትን ሊቀይር የሚችል ቁጣ እና የማንነት ግጭት በዋንኛነት ይጠቀሳሉ።

የስሜት መብሰል የሚከተሉትን በሀሪያት ያጠቃልላል፡- መልካም ፀባይ፣ ተጫዋችነት እና ኮስታራነትን አጣምሮ መያዝ፣ መነቃቃት፣ ማስተዋል ወይም ነገሮችን እንደራሳቸው ማንነት መረዳት መቻል፣ ውበትን የመረዳት እና የማድነቅ ችሎታ፣ ርህራሄ፣ እና ትዕግስት ናቸው።

እነዚህ የስሜት መብሰሎች በእድሜ መግፍት ብቻ የሚመጡ ሳይሆኑ አንድ ሰው በፀጋ ሲያድግ፣ ዕለት ዕለት ዕራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ለማስገዛት ፈቃደኛ ሲሆን እና በሕይወቱ ከሚነሱ መከራዎች ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ሲችል የሚመጡ ናቸው።

ገላ 5፡16-25፣ ሮሜ 8፡5-14

ስሜታዊ ብስለት መገንቢያ መንገዶች

አንድ ሠባኪ በመንፈስ ማደግ የግድ ያስፈልገዋል። ወደ ስሜታዊ ብስለት ሊያደርሱን ከሚችሉት መንገዶች ውስጥ አራቱን ከዚህ በመቀጠል እመለከታለን።

1. የራስን የግል ባሕርይ ማጥናት እና መለየት

የመጀመርያው ስሜትን የመገንቢያው መንገድ የራስ የግል ባሕሪን በማጥናት ስሜታዊ ጥንካሬን እና ድክመትን በመለያት ማንነትን አውቆ ለማሻሻል መጣር፡፡

2. መልካም የሆኑ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን መጠበቅ/መንከባከብ/

በአብዛኛው መልካም ስሜትን የሚጎዱት ነፃነት የሚያሳጣ ሸክም፣ እረፍት የሌለው ስራ እና ነፃነት የሌለው ማህበራዊ ግንኙነት ናቸው፡፡ መልካም ሰሜትን ለማጎልበት ቀጣይነት ያለው መንፈሳዊ ህብረት ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ማድረግ እና ይህ ሕብረት እንዳይበላሽ መጠበቅ፡፡

3. አካላዊ ሠውነትን በጤንነት መያዝ

አካላዊ ጤንነትን ስንገነባ ስሜታዊ ጤንነታችን አብሮ ይገነባል፡፡ አካላዊ ጤንነትን ለመጠበቅ በቂ እረፍት ፣ ስፖርት ፣ መዝናናት እና ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ ያስፈልጋል፡፡ ያልተስተካከለ ጤንነት መደበትን እና የተጠቃ ስሜትን በሠው ላይ ይፈጥራል፡፡

4. ዘውትር በነፃነት ጤናማ ስሜትን መግለፅ /መለማመድ/

በምንም ነገር ላለመጨነቅ መወሰን እና በነፃነት ጤናማ ስሜትን በማንኛውም ቦታ እና ጊዜ መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡

ሰባት ወሳኝ ስሜታዊ ባህሪያቶች

የሚከተሉት ሰባት ስሜታዊ ባሕርያቶች ለአንድ ሰው /ሰባኪ/ ማንነት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

1. ፍቅር

ሰዎችን የምንወድ ከሆነ ሰዎች ለእኛ ፍቅር ይኖራቸዋል ከዚያም ባለፈ ተወዳጅነትችን ይጨምራል፡፡

2. ለእውነት ያለን ፍቅር /Passion For truth/

ሰባኪ እውነትን ለማወቅ እና ያወቀውን እውነት በሠው ሕይወት ውስጥ ለመተግበር ታላቅ ፍቅር ያለው ሠው መሆን አለበት፡፡

3. መነቃቃት /Enthusiasm/፡- በመንፈስ መነቃቃት ወይም መነሳሳት

ይህ ቃል የመጣው ከግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም በመንፈስ መነቃቃት ወይም መነሳሳት እንዲሁም በእግዚአብሔር መወረስ /Being inspired, being possessed by God/ እንደ ማለት ነው፡፡

4. ቅንነት /Earnestness/

ወንጌል እና ሠው በተፈጥሮው ከሰበባኪ /ከሰው/ ማየት ከሚፈልጉት ዋንኛ ባህሪያት መሀከል ቅንነት አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ወንጌል ያለቅንነት በውጤታማነት ሊሰበክ አይችልም፡፡

5. ተጫዋች እና የጨዋታ ለዛ ያለው /Sense of humor/

ይህ ባህሪ /ጠባይ/ ከቅንነት የተቃረነ ባህሪ አይደለም፡፡ ይልቁን እነዚህ ሁለት ባህሪያቶች በሚዛናዊነት በአንድ ሠው ውስጥ ሊታዩ ያስፈልጋል፡፡ የስነ ልቦና ስነ ጥናት እንዳመለከተው ከአድማጮች ውስጥ 10% በምክንያታዊ ሁኔታ የሚያዙ ናቸው፣ 70% በተነቃቃ /inspiration/ ሁኔታ ይያዛሉ፣ 90% ደግሞ ጥሩ ለዛ ባለው ጨዋታ የመያዝ ዝንባሌ ይታይባቸዋል፡፡ ይህ ተጫዋችነት ግን በአስፈላጊው ቦታ እና ግዜ መከናወን አለበት፡፡

6. ግለት /ሐይል/ /Intensity/

የተዳከመ አዕምሮ ፣ የተዳከመ አካል፣ እና የተዳከመ ስሜት በንግግር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል፡፡ ስለዚህ ለተሳካ ስብከት /ንግግር/ የጋለ ስሜት እና የተነቃቃ ሠውነት ወሳኝ ናቸው፡፡

7. ግብረገብአዊ መነሳሳት/የፅድቅ ቁጣ ወይም ቅናት/ /Moral Motivation/

/ Rightness indignation/

- **አዎንታዊና አሉታዊ ስሜቶች /Positive and Negative Emotions/**

አዎንታዊ ስሜቶች ሰባኪው በሚሰብክበት ግዜ የተሳካ ስብከት እንዲሰብክ የሚያግዙት ናቸው። በሌላ በኩል አሉታዊ ስሜቶች የስብከት /የንግግር/ ስኬት ጠላቶች ናቸው።

- አወንታዊ ስሜት /Positive Emotions/

መረጋጋት ወይም ዝምተኝነት፣ ጓደኝነት ወይም ወዳጅነት፣ ታማኝ፣ ከፅድቅ እና ከፍትህ የመነጨ ኩራት፣ ግዴታን ማወቅ፣ በራስ መተማመን፣ ማፈር፣ ደግነት፣ የተሻለ ለመስራት መጣር፣ መታመን፣ ፍቅር፣ ምስጋና፣ ርህራሄ፣ ደስተኛነት፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ርህራሄ፣ ማክበር፣ ተስፋ፣ ሐዘኔታ፣ መደነቅ እና ማድነቅ፣ ቅንነት፣ እና መነቃቃት ናቸው።

- አሉታዊ ስሜት /Negative Emotions/

ቁጣ፣ ንቀት፣ እፍረት ማጣት ወይም አይን አውጣነት፣ ቅናት፣ ትዕቢት ወይም እብሪተኛነት፣ ማንቋሸሽ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ጥርጣሬ፣ ስጋት፣ መከፋት፣ አግባብነት የሌለው ጥለቻ፣ በችሎታው የሚኩራ፣ መፍራት ወይም መስጋት፣ ሁሌ መውቀስ ወይም ወቃሽነት፣ ጥላቻ ወይም ቂም፣ ጠላትነት፣ ክርክር፣ መደበት፣ ሰውን መፍራት ናቸው።

ከእነዚህ እወንታዊ እና አሉታዊ ስሜቶች መሃከል የትኛዎቹ በአንተ ላይ እንደሚታዩና እንደማይታዩ በመለየት አዎንታዊውን ለማዳበር እና ለመጨመር እንዲሁም አሉታዊውን ለመቀነስ እና ለማስወገድ መንቀሳቀስ አለብህ።

ስሜትን በስራ ላይ ለማዋል የሚጠቅሙ መመሪያዎች /Guidelines for Expressing Emotions/

በቂ የስሜት ዝግጅት ማድረግ /Enough Preparation/

አንድ ሰባኪ በቂ ዝግጅት መፅሐፍ ቅዱስ በማጥናት ፣ በመፀለይ እና በማሰላሰል ካደረገ በአግባቡ አድማጭውን መያዝ እና ማገልገል ይችላል።

የተናጋሪው ስሜት እውነተኛ መሆን አለበት /The preacher’s emotion must be genuine/

እውነተኛ ስሜት ማለት ሰባኪው ድንገት ያሚያሳየው እውነተኛ መሰል ስሜት ማለት ሳይሆን። ትክክለኛ ስሜት ዕለት በዕለት የሚገነባ እና የራስ ማንነት ማድረግ የምንችለው ባህርያት ማለት ነው። የዘፈን ተወዛዋዦች የሚያሳዩት አይነት ፈገግታ ማለተ አይደለም።

- ሰባኪ የተለያዩ አይነት ስሜቶችን ማንፀባረቅ አለበት።

ከመልዕክቱ ጋር የተያያዘ አይነት ስሜት ማንፀባረቅ እንጂ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሚያሳዝነው፣ በሚያስቆጣው፣ እና በሚያስደስተውም ነገር ሁሉ መቀለድና አንድ አይነት ስሜት ማሳየት አይገባም።

- የሰባኪው ስሜት በግልፅ ለአድማጭው መታየት /መገለፅ/ አለበት
- የሰባኪው ስሜት ከመልዕክቱ ጋር መዛመድ አለበት

  በሚያስቀው መሳቅ፣ በሚያሳዝነው ማዘን፣ እና በሚያስደስተው መደሰት ወዘተ

- ስሜት ስነ ምግባርን በጠበቀ መልክ መገለፅ አለበት

ስሜት በአሉታዊም ይሁን በአዎንታዊ መልክ ታላቅ ሀይል ስላለው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያሻዋል። ከስነ ምግባር አንፃር ተገቢ ያልሆነ ትርጉም ሊሠጡ የሚችሉትን ስሜታዊ እንቅስቃሴዎች እና ሁኔታዎች መቆጣጠር አስፈላጊ ነው።

- ስሜታዊነትን ማስወገድ

ስሜታዊነት ማለት ስሜትን ለግል ጥቅም ለማዋል የሚደረግ ጥረት፣ ስሜትን ከአመክንዮ /Reason/ ቁጥጥር ውጪ ማድረግ ወይም ምስጋናን ለመሰብሰብ የሚደረግ ጥረት ማለት ነው። ስለዚህ ግላዊ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ስሜትን ከመጠቀም መታቀብ አስፈላጊ ነው።

3. የንግግር መመሪያ /ደንብ/

በሐዋ 18፡24-25 ላይ አጵሎስ የንግግር ዕውቀት ያለው እና ተናጋሪ እንዲሁም በንግግር ውስጥ ስሜቱን አግባብነት ባለው ሁኔታ የሚጠቀም እንደሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ከጠቀሰልን መሳሌዎች ውስጥ አንዱ ነው።

በአጠቃላይ ስብከት የንግግር ደንብን የሚከተል ነው፡፡ ሆኖም ከሌሎች የንግግር አይነቶች የሚለይበትም የራሱ የሆነ ፀባይም አለው፡፡

መልዕክት የማቅረቢያ መንግዶች /ዘዴዎች/

ባለፉት ዘመናት ሶስት አይነት የመልዕክት አቀራረብ ዘዴዎች በአገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ እነርሱም፡- ንባባዊ ዘዴ /Reading method/፣ መነባንባዊ ዘዴ /Recitation Method/ እና ዝግጅት አልባ ዘዴ /Extemporaneous Method/ ናቸው፡፡

1. ንባባዊ አቀራረብ /Reading method/

ይህ ዘዴ አንዳንድ ግዜ ማኑእስክሪፕት ሜትድ "manuscript method" በመባል ይጠራል፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ በኢንግላንድ በጣም ታዋቂ የነበረ የስብከት ዘዴ አይነት ነው፡፡ ይህን ዘዴ የሚከተል ሠባኪ መልዕክቱን ሙሉ በሙሉ በወረቀት ላይ ያስፈራል፡፡ ከዚያም ለአድማጭው ቃል በቃል ያነብላቸዋል፡፡ ይህ ዘዴ በአብዛኛው በዋነኝነት በእንግሉዝ ፣ በስኮትላንድ እና በዩናይትድ ስቴትስ በስራ ላይ ውሎአል፡፡

2. መነባንባዊ አቀራረብ /Recitation Method/

ይህ ዘዴ አንዳንድ ግዜ ሚሞሪተር ሰብከት "Memoriter Preaching" በመባል ይጠራል፡፡ በ17ኛው ክፍለ ዘመን በፈረንሳይ በጣም ታዋቂ የነበረ የአሰባበክ ዘዴ ነበር፡፡ እንዲሁም በጀርመን እና በኢጣሊያ በስፋት በስራ ላይ ውሎአል፡፡ በአሁን ጊዜ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ የያዘ የስብከት ዘዴ ነው፡፡ ይህን ዘዴ ለመጠቀም ሰባኪው በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ መልዕክቱን በጥንቃቄ በወረቀት ላይ ይሰፍራል፡፡ ከዚያም ሙሉ በሙሉ በማሰላሰል ይሰብከዋል ማለት ነው፡፡

3. ዝግጅት አልባ ዘዴ /Extemporaneous Method/

የዚህ አይነት የስብከት አቀራረብ ዘዴ የተጀመረው በቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ወቅት ነው፡፡ ከሐዋሪያት ዘመን እስከ አሁን ድረስ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ዋንኛ የቤተክርስቲያን ማደግና መነቃቃት ወቅት ይህ ዘዴ በአገልግሎት ላይ መዋሉን ታሪክ ይጠቁመናል፡፡ በተሀድሶ ዘመን ማለትም በ16ኛው ክፍለ ዘመን እና በ18ኛው ክፈለ ዘመን የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን

መነቃቃት በእንግሊዝ እና በአለም አቀፍ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ክፍለ ዘመን ሁሉ ይህ አይነት የስብከት ዘዴ በስራ ላይ ውአል። ቢሆንም ሰባኪውቹ ድንገት ወረቀት እና ሌሎች መሳርያዎችን ሳይጠቀሙም ቢሰብኩም የሰበኩት ሀሳብ ግን ቀደም ብለው ለዚያን ቀን አይሁን እንጂ በሚገባ ያጠኑት እና የተዘጋጁበት እንደሆነ መሰመር አለበት።

በዚህ ዘመን ያሉ የንግግር እና የስብከት ፅሁፍ ፀሐፊዎች ኤክተምፖራኒዮስ “Extemporaneous” የሚለውን ቃል የሚጠቀሙበት በቂ ዝግጅት በማድረግ ማስታወሻ ከተያዘ በኃላ ለሚነገር ንግግር ወይም ስብከት አይነት ነው። ይህ ማለት ደግሞ በወረቀት የተፃፈውን ከማንበብ እና የተፃፈውን ሸምድዶ ከመስበክ ዘዴ የተደባለቀ /የሁለቱም አይነት ውህድ/ ስብከት አይነት ነው።

ጥናት እንደሚያመለክተው 80% የሚሆነው ሰባኪ የተወሰነ ማስታወሻ እንደሚጠቀም ነው። እንዲሁም አብላጫው አድማጭ ኤክተምፖራኒዮስ “Extemporaneous” አይነት ስብከት ዘዴን የሚጠቀምን ስብከት ለመስማት ይመርጣል፡ እንደኛ እምነት በማንበብ እና የተዘጋጀውን በሙሉ በመሸምደድ የወንጌል ስብከት ለማካሔድ አይቻልም። ስለዚህ በአሁን ሰዓት Extemporaneous ዘዴ ዝግጅት የሚጠይቅና ማስታወሻ በመያዝ ማስታወሻውን በተዋቀረ መልክ ማዘጋጀት ይጠይቃል። በዚህ እይታ ስንመለከተው የሚከተሉትን ጥቅም የሚሰጥ ይሆናል።

መንፈሳዊ መመሪያ

ለስብከት ሦስት ወሳኝ እና መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነርሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል /መልዕክት/፣ የእግዚአብሔር ሠው /መልዕክተኛ/ እና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው። በዚህ ክፍል በዋነኝነት መንፈስ ቅዱስ ታላቅ ችሎታን ለሠባኪ በመስጠት የሚጫወተውን ታላቅ ሚና እንመለከታለን። ለምሳሌ ሉቃስ ስለ ኢየሱስ በውሃ ተጠምቆ ወደ ምድረ በዳ በመሄድ ከተፈተነ

በኃላ ለአገልግሎት ለመውጣት ከምድረ በዳ ሲመለስ በታላቅ የመንፈስ ሙላት እንደነበር ግልፅ አድርጎ ፅፎልናል፡፡ ሉቃ 4፡1፣14 /የገሊላውን አገልግሎት ለመጀመር/፡፡ እንዲሁም ሉቃስ የኢየሱስን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ እና በሃይል እንደነበር አብራርትዋል፡፡/የሐዋ 10፡ 38/ ይህ መቀባት ታላቅ የሆነ ውጤትን ለኢየሱስ አገልግሎት አስገኘ፡፡

ሐ. በስብከት ጊዜ የሚያስፈልገው ብርቱ ጥንቃቄ

በአሁኑ ዘመን ሰዎች ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የነቁበት በኢንፎርሜሽን የተሞሉበት ጊዜ ነው፡፡ የሚሰብኩበትና የሚቀበሉት ሰው የሚመርጡበት ጥሩውን ከመጥፎ የሚለዩበት እውነትን ከሀሰት መለየት የተቸገሩበት ጊዜ ነው፡፡ ስልጣን በቀላሉ ተቀባይነት አያገኝም አንድ ሰባኪ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ሳይሰሙም ስልጣንን ማስተማር ወይም መስበክ አለበት፡፡ የስልጣን አገልጋዮች እግዚአብሔርን ከቃሉ ጋር ባላቸው ግንኙነት ይወሰናል፡፡ ምርጫ መወሰን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የነቁበት በኢንፎርሜሽን የተሞሉበት ጊዜ ነው፡፡ ለምሣሌ በቤታቸው ሆነ በዓለም ላይ ያሉትን ታላላቅ አስተማሪዎችን ሰባኪዎችን የማግኘት በቲቪ በኮምፒውተር በሬዲዮና በተለያዩ ካሴቶች በኦዲዮ ቪዲዮ ቀለል ብሎ የቀረበላቸው እያገኙ ያሉበት ጊዜ ነው፡፡ አንዱን ከአንዱ የሚያበላልጡበት የማያሳንሱበት ጊዜ ላይ ደርሰዋል ስለዚህ ስብከቱ ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ በስልጣን የመስበክ የመናገር ነገር የሚያደርግ እነደመሆኑ ሁሉ የሚቀጭጭና ጭራሹኑ ሊጠፋ የሚችል ነገር ነው፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙት ይወሰናል በስልጣን በመስበክ እግዚአብሔርን በተጠጋነው ልክ ሕዝቡን እንዴት መቅረብ እንዳለብን እንማራለን፡፡

በስብከት ሂደት ውሰጥ የማይነጣጠሉ ሦስት ነገሮች

ሀ. መልክታችንን ምንጭ የሆነ እግዚአብሔር

ለ. ተቀብሎ የሚያስተላልፍ ሰባኪ

ሐ. እወነትን ተቀብሎ በራስ ላይ የሚወሰን ሕዝብ

ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ሰባኪነት ማለት ምን እንደሆነ ከማወቅ ባሻገር ዓላማው የእግዚአብሔርን መልእክት ወቅታዊ በሆነው በሰዎች ጉዳይ መልስ መሆኑን አድማጩ ለሰማው መልእክት ምላሽ እንዲሰጥ የማያስገድድ ስልጣናዊ መሆኑን ይሄንን አገልግሎት የሚያገለግል የግል ጥሪ ያለው በብዙ ጥንቃቄ የሚቀርብና የማዘጋጅ ብርቱ ፀሎት የማያሰፈልገው አገልግሎት ነው በአሁኑ ዘመን ስብከት በእግዚአብሔር ቃል ሙላት በቂ ዝግጅት በትውልዱ መዳረስ ያለበት አገልግሎት መሆን አለበት የሰባኪነት ጥሪና የመልክቱ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር መልክቱን በግዚው ተቀብሎ ለአዳማጩቹ ለማድረስ የተጠራ ሰው ማስተዋል የሚባው እውነት ነው፡፡

እግዚአብሔር ለውጥ የሚናመጣ ሰባኪዎች

ያድርገን የሚበዙትንም እውነተኛ ሰባኪዎች ያስነሳል!!

አሜን፡፡

ውድ ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን የመልመጃ ጥያቄዎች በወረቀት ላይ በመስራት ለመምህሩ ይስጡ፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተማራችሁት መሰረት መልሱ

1. ስብከት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ስብከት ሳይንስ ነው የሚባልበት ምክንያት ምንድነው? ጥበብና ስጦታ የሆነበት ምክንያት ምንድ ነው?
3. ስነስብከት በውስጡ የሚያካትታቸው ነገሮች ምንምንድ ናቸው?
4. መስበክ ተብለው የተተረጎሙ አራቱ የግሪክ ቃላት የትኞቹ ናቸው?
5. ሁለቱን የገላጭ ስብከት ትርጉሞችን ጻፍ/ፊ፡፡
6. ገላጭ ስብከት መሰረት የሚያደርገውን ሶስት ነጥብ ዘርዝር፡፡
7. ከገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ደረጃዎች፡ ውስጥ አምስቱን ጻፍ፡፡
8. ርዕሳዊ ስብከት ማለት ምን ማለት ነው?
9. ግለ-ታሪክን መሰረት ያደረገ ስብከት (Biographical Sermon) ምን ዓይነት ስብከት ነው?
10. የተሳካለትና ውጤታማ ሰባኪ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቁልፍ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
11. ስብከት ሶስት ክፍሎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ እነዚህ ሶስቱ ክፍሎች ምን ምንድናቸው?
12. መንፈስቅዱስን በተመለከተ ለክርስቲያኖች የተሰጡ አራት የአዲስ ኪዳን ትዕዛዛት የትኞቹ ናቸው?
13. መልዕክትን በሚገባ ለአድማጭ (ለአንባቢ) ለማድረስ የሚረዱ መርሆች ምንምንድ ናቸው?
14. የብሉይ ኪዳን ስብከት የመጣው ከምንድነው? (ከየትኛው የአገልግሎት ክፍል ነው?)
15. የአዲስ ኪዳን ሰባኪዎች የስብከታቸው ማዕከል ምን የሚል ነበር?
16. መግቢያን ስታዘጋጅ ማወቅ የሚገባህ አምስት ነጥቦች ምንምንድ ናቸው?
17. የመግቢያና የመደምደሚያ ልዩነት ምንድ ነው?
18. ስብከት ሊኖረው የሚገባው ቅርጽ ምን ዓይነት ነው?
19. መልዕክትን ለማዘጋጀት ወሳኝ የሆኑ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
20. ከአድማጮች ጋር በዓይን መገናኘት ጠቀሜታው ምንድነው?

Bibliography

Anderson, G., ***Notes on Homiletics***, Boston: Rockwell & Churchill Printers, 1872.

Berkley, James D.: ***Preaching to Convince***. Carol Stream, Ill.; Waco, Tex.: CTi; Word Books, 1986.

Broadus, John A., ***A Treatise on the Preparation and Delivery of Sermons*** *(*37th edition Edited by Edwin Charles Dargan), New York: Hodder and Stoughton, 1898.

Evans, William. ***How to Prepare Sermons,*** Chicago: Moody Press, 1964.

Leander E. Keck, ***The Bible in the Pulpit: The Renewal of Biblical Preaching.*** Nashville: Abingdon, 1978.

MacArthur, John: ***Rediscovering Expository Preaching***. Dallas: Word Pub., 1997.

Shawn, Abigail, ***Introduction to Homiletics,*** 2006.

Timothy Tow, ***My Homiletic swimming pool,*** Far Eastern Bible College Press, Singapore, 1998.

አርኔል ሞዝ፣ ***ሕይወት ለዋጭ ስብከት፣*** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡ አሳታሚ- አይ ኢ ሲ በስ አይ ም ማተማያ ቤት የታተመ፣ 1999 ዓ.ም.

በዶ/ር ራሚሽ ሪቻርድ (ትርጉም በገበየሁ አየለ)፣ ***የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት፣*** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡ በላፐሰሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን የታተመ፣ 1995 ዓ.ም.

መለሰ ወጉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም መስከረም የመጀመሪያ እትም 1993 ዓ.ም.

Petts, David, Body buiders gifts to make God’s People grow England mottersey Hall 2002’

Braga.james, How to Prepared Bible Messages, Portland, Oregon, Multnomah press, 1981.

Mamusha Fanta, Introduction to Preaching (PTC) unpublished.

Moon,Jesse k. Principles of Preaching Colombia, ICI University, 1991.

Robinson,H. Expository Preaching - Principles and Practice. Leicester, Inter Varsity, 1896.